# 16

# ስፍጥረት መዳን ባስህ መሻት ሕይወትህን መዝን

እግዚአብሔር ዓለምን ሁሉ በመውደዱ፣ ለሰዎች የሚሆን እቅድ አለው፤ ይህም በምድር ላይ ለሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ልጁን እስከ ሞት ድረስ አሳልፎ መስጠቱ ነው። እናም ዛሬ በዓለም ላይ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ለድነታቸው ወደ እርሱ እንዲመጡ ይጠብቃል። (ዮሐ 3፥16) እግዚአብሔር ዓለሙን ሁሉ እንደሚወድ ያረጋግጥልናል። ኢየሱስ ሕይወቱን የሰጠው በዓለም ላይ ለሚገኝ ሕይወት ሁሉ ነው (ዮሐ 6፥33)። እርሱ የዓለም ብርሃን ነው (ዮሐ 8፥12)።

## ስመሳው ዓስም ፍቅር ይኑርህ

ፍቅርህ ከዓለማዊ ፍቅር ያነሰ ከሆነ፣ አንተ እጅግም ክብር የሌለህ ምናልባትም ጥቅም እንኳን የሌለህ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ። ፍቅርህ መላውን የዓለም ሕዝብ የማይጠቀልል ከሆነ፤ ጸሎትህም በየዕለቱ በዓለም ዙሪያ የማይዘልቅ ከሆነ፣ አንተ ታማኝ የሆንክ የኢየሱስ የጸሎት አጋር አይደለህም። መንፈሳዊ ሕይወትህ ዓለም አቀፋዊ እቅጣጫ ከሌለው በእርግጥ አንተ ተሰፋ አስቆራጭ የኢየሱስ ተከታይ ነህ።

ዓለምን በአገልግሎት መድረስ በቤተ ክርስቲያን ላሉ በተለይ ለተመረጡ ሰዎች የተተወ ቀላል ነገር አይደለም። ለመላው አብያተ ክርስቲያናት የተሰጠ ቅድሚያ ያለው ተልዕኮ ነው። ክርስቶስ ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመምጣታችን ጉዳይ ይልቅ ትልቅ ትኩረት የሰጠው ወደ ዓለም በመውጣታችን ጉዳይ ላይ ነው። በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት የምትቆም ከሆነና ሕይወትህ ወደ ዓለም የተዘረጋ ፋይዳ ያልነበረው ከሆነ፣ በእግዚአብሔር ጸጋ የምትድን



መሆንህን ብታውቅም እንኳን በፊቱ ሀፍረትን መከናነብህ አይቀሬ ነው። የምትሰጠው የፍቅር ምላሽ እጅግ የጠበበ፣ የታወረና እንደ ትእዛዙም ዓለምን የማትወድ ከሆነ የተቀበልከው የእግዚአብሔር መልካምነት ይበልጥ እንድታፍር ያደርግሃል።

እግዚአብሔር እንዳዘዘህ ዓለምን የምትወድ ከሆነ፣ መጀመር ያለብህ አሁን ነው። ከሞት በኋላ ጊዜው በጣም የዘገየ ይሆንብሃል። ለተከታዮቹ ሁሉ የተሰጠውን "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ" የሚለውን የክርስቶስን ቃል የምትታዘዝ ከሆነና ጸሎትህ እንዲሁም የምትዘራው ዘር ዓለም አቀፋዊ እንዲሆን የምትፈልግ ከሆነ ይህን ማድረግ ያለብህ አሁን ነው።

እስከ አሁን በነበረው ዘመንህ ይህን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከማድረግ ጎድለህ ቢሆን፣ የተቀጠለውን ጊዜ ለማካካስ ማድረግ የምትችለውን ሁሉ አድርግ። እግዚአብሔር ማንኛውም ክርስቲያን ስለ ዓለም ነገር የሚያገባው፣ ለዓለም ፍቅር ያለው ለዓለምም የተለየ የምልጃ ጸሎት የሚያደርግ እንዲሆን ይጠብቃል። መታዘዝህንም ይሁን መታዘዝ ያለመቻልህን እግዚአብሔር ለፈጠረው መላው ዓለም በዘራኸው ልብህና ሕይወትህ መዝነው።

ያለምንም ጥርጥር፣ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱንና እኛን ለማዘጋጀት ብዙዎቹን እውነቶቹን ደጋግሞ ያስተማረው ከእኛ ጋር በአካል አብሮ ስለማይኖርበት ስለዚህ ጊዜ ነው። በመጨረሻዎቹ ሰዓታት ጥልቅና እጅግ አስደናቂ ከሆኑት ትምህርቶቹ መካከል ስለ ጸሎት፣ ስለ መንፈስ ቅዱስና ስለእኛ ስላለው ፈቃድ ለማስተማር እንዴት ተጨናንቆ እንደነበር የዮሐንስ ወንጌል ያሳየናል። አራቱ ወንጌሎች የሀዋርያት ሥራ መጽሐፍ፤ እንደሚነግሩን ከሆነ ጌታ ኢየሱስ ወደ አባቱ ከማረጉ በፊት በነበሩት የመጨረሻዎቹ ቀናትና

የመጨረሻ ሰዓታት በልቡ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ሁለት ጉዳዮች ነበሩት::

የመጀመሪያው፣ ተከታዮቹ በምድር ላይ የእርሱ ተጠሪዎች እንደመሆናቸው፣ ኢየሱስ ለእነርሱ ያሰውን እቅድ ይተገብሩ ዘንድ የመንፈስ ቅዱስን ኀይል መልበስ (ሉቃ 24፥48)፣ መቀበል (ሉቃ 24፥28፤ ሐዋ 1፥8) እና መሞላት እንዳለባቸው የሰጠው ትኩረት ነው:: ያለ መለኮታዊ ትጥቅ የተሰጣቸውን ኃላፊነት መወጣት አይችሉምና::

ሁለተኛው፤ በመስቀል ላይ የሰጠውን ድነት ይዘው ወደ ዓለም ሁሉ መውጣታቸው፤ ጥያቄ ሊነሣበት የማይገባ ቀዳሚ ተግባር እንደሆነ የሰጠው ትኩረት ነው:: ምስክርነታቸውና ተልዕኮአቸው ዓለም አቀፋዊ ይዘትና አቅጣጫ ነበረው:: ወደ ሁሉም ሕዝቦች ሊወጡ (ማቴ 28፥19፣ ሉቃ 24፥47)፣ ወደ ዓለም ሁሉ ሊሄዱ (ማር 16፥15)፣ እስከ ዓለም ዳርቻ ሊዘልቁ (ሐዋ 1፥8) የግድ ነው::

እነኚህ ሁለት ቀደምት ጉዳዮች ኢየሱስ ወደ ምድር ተመልሶ እስኪ መጣ ድረስ ቀደሚ ጉዳዮቹ እንደሆኑ ተጠብቀው ይቆያሉ:: የተሰጡን ግዳጆች ቀደምትነት ያላቸው ናቸው:: ተልዕኮዎቻችን የማይለወጡ ናቸው:: ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ሊናገር እኔንና አንተን መናገሩ ነው (ሐዋ 2፥39):: እርሱ የሰጠንን ግዴታ በአግባቡ እንድንወጣ በመንፈስ መሞላት፣ የመንፈስ ቅዱስን ኀይል መቀበል የእኔና የአንተ ኀላፊነት ነው:: በምድር ላይ የሚገኝ የማንኛውም አገር ሰው የወንጌልን እውነት እስኪረዳ፣ ድነትን እስኪቀበልና አግባብነት ያለው እድል እስኪያገኝ ድረስ፤ በእርሱ የተሰጡንን ቀደምት ኀላፊነቶች ለመወጣት እኔና አንተ ተግባራችንን ልንቀጥል ይገባል::



እነኝህ ሁለት ቀደምትነት ያላቸው ኀላፊነቶች ለአንተ የተሰጡ መሆናቸውን ያለማቋረጥ በማሰብ ነው የምትኖረው? የሰጠንን ኀላፊነቶች ቸል ስንልበት በኢየሱስ ልብ ውስጥ የሚፈጠረው ሀዘን ይሰማሃልን? ምናልባትም በምድር ላይ ከሚኖሩ ሰዎች ሩብ ያህሉ ኢየሱስ የሚባለውን ስም ያልሰሙ ወይም ማንነቱን ያውቁ ዘንድ መስማት የሚገባቸውን ያህል ባለመስማታቸው ኢየሱስ ልቡ እያዘነ መሆኑን ታምናለህ? ያልዳኑ ሰዎች ይድኑ ዘንድ እድል እንዲያገኙ በእግዚአብሔር ፊት ከፊሉን ኀላፊነት እንደተሸከምክ ታስተውላለህን?

ሐዋርያው ጳውሎስ የማንመልሰው ጥያቄ ይጠይቀናል:: “የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና፤ እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ?” (ሮሜ 10፥13-14):: እያንዳንዱ ክርስቲያን፣ እኔንና አንተን ጨምሮ የተጠራነው ዓለምን በወንጌል የመድረስ ያልተጠናቀቀ ተልዕኮ ወደ ፍፃሜው እንዲመጣ ነው:: እውነተኛ ለሆነ አንድ ክርስቲያን ከዚህ አገልግሎት ጋር መቀላቀሉ እንደ አማራጭ የሚቀርብለት ጉዳይ አይደለም:: ዓለም በወንጌል እንድትደረስ ከመጸለይ ወይም በገንዘብ ከመርዳት ውጭ የምንሆንበት አንዳችም ሰበብ ሊኖር አይችልም:: ለመቤዡት የሚያስፈልገውን ዋጋ ኢየሱስ ክርስቶስ ከፍሎ ጨርሷል፤ ነገር ግን ይህ ለመቤዡት የተከፈለው ዋጋ በሁሉም ሰዎች እንዲታወቅ የሚከፈለው ዋጋ የሚጠበቀው ከእኔና ከአንተ ነው::

## ሁሉንም ሰዎች ውደድ

ፍቅር ሞልቶ የተትረፈረፈበት ልብ ብቻ አይደለም የሚያስፈልገን:: ፍቅራችን በተወሰነ ነገር ላይ ያረፈ እንዲሆን ግድ ነው:: እግዚአብሔር ፍቅርህን የሚመዝነው ፍቅርህ ሁሉንም ዐይነት ሰዎች ባካተተበት መጠን ነው:: በእስር ቤት ስላሉ ሰዎች እውነተኛ ፍቅር ያስማቋረጥ ይሰማሃል? ወላጅ ስሌላቸው ልጆችስ? ወዳጆቻቸው በሞት ስተለዩዋቸውስ? ስታመሙስ? ስርጣት ተማሪዎችስ? በዓለም ውስጥ ስላሉ ልጆችስ? ስአረገውያንስ? እንደነዚህ ካሉት መካከል የተለየ ትኩረት የምትሰጥበት ፍቅር ሊኖርህ ይገባል:: የተለያየ ዐይነት የሥራ ባሕርይ ወዳላቸው ወደ መርከበኞች፣ የማዕድን ሠራተኞች፣ መምህራን፣ ሐኪሞች፣ የቤት እመቤቶች፣ ገበሬዎች፣ ሚኒስትሮች ፍቅርህ ዐልፎ የሚሄድ ነውን? በየአጋጣሚው የሚያገለግሉህን ፖሊሶች፣ ነጋዴዎች፣ በሌሎች መንገዶችም አገልግሎት የሚሰጡህን ሰዎች ትወዳቸዋለህን?

ፍቅርህ የሁሉንም አገር ሕዝቦች የሚዳስስ ሊሆን ያስፈልገዋል:: እንግዲያውስ እግዚአብሔር ፍቅርህን በዚህ የሚመዝን ከሆነ እንኳንስ ልትጸልይላቸው ቀርቶ አስበሃቸው የማታውቅ ቡድኖች ይኖሩ ይሆን? ስቲቤታውያን፣ ስቻይናውያን፣ በኔፐልስ ምድር ስሚኖሩ፣ በአፍጋኒስታን፣ በሜክሲኮ፣ በኮሎምቢያ፣ በፔሩ፣ በሩሲያ፣ በፓላንድና በጀርመን ስሚኖሩ ድነትን ላላገኙ ሰዎች ፍቅርህ ምን ያህል ትልቅ ነው? በምድር መናወጥ፣ በውሃ መጥለቅለቅና በሕዝባዊ ዐመጽ የተጎዱ በየትኛው ውም የዓለም ክፍል ስላሉ ሰዎች ስትሰማ ፈጥነህ ትጸልያለህን? ፍቅርህን በዓለም ዙሪያ ባስፋህበት መጠን ሕይወትህን መዝነው::



እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያው ቶማስ ልብ ውስጥ የነበረውን ጥርጥር በበዓለ አምሣ ቀን እሳት ባነጻውና ባቃጠለው ጊዜ፤ ለክርስቶስ የነበረው ፍቅር የተገለጸው ለወንጌል አገልግሎት በተለጠ ልብ ነበር:: መንፈስ ቅዱስ ባነጻንና በሞላን ጊዜ ብዙውን ጊዜ የሚሆነው የቀደመ ድካማችንን ከላያችን ላይ አንሥቶ ጥንካሬዎቻችን ያደርጋቸዋል:: ምናልባትም ጳውሎስን ሳይጨምር ቶማስ ከሁሉ የላቀ ቅናት ያለው፣ ፍርሃትን የማያውቅና ንቁ ሐዋርያ ሆኗል::

ቶማስ የወንጌል አገልግሎት ዘመቻውን የጀመረው በምስራቅ አቅጣጫ ነበር:: የቀደመችይቱ ቤተ ክርስቲያን አባቶች የነበሩት ኢሶቢዮስና ጀሮም ሁለቱም የቶማስን የወንጌል አገልግሎት እንቅስቃሴዎች ዘግበዋል:: በዚህም ጉዞው በፓርቲያና በፐርሺያ አቋርጦ ምናልባትም እስከ ሕንድ ምድር ድረስ እንደዘለቀ ይናገራሉ:: ዛሬ ባላቸው የአገራት ስያሜ ቶማስ ሶርያን፣ ኢራቅን፣ ኢራንን፣ ደቡብ ሩሲያን፣ አፍጋኒስታን፣ ፓኪስታንንና ሕንድን አዳርሷል::

በደቡብ ሕንድ ያሉ ቀደምት አብያተ ክርስቲያናት የተመሠረቱት በቶማስ እንደሆነ ይጠቅሳሉ:: እስከ ዛሬም ድረስ የደቡብ ህንድ ግዛት በሆነችው በኬራላ ከተማ በብዛቱ ከቶማስ ስም ይልቅ የተለመደ ሌላ ክርስቲያን ስም የለም:: በአፈታሪኮች እንደሚነገረው ቶማስ ለክርስቶስ ሠማዕትነትን የተቀበለው በደቡብ ሕንድ በምትገኘው ተራራማ ግዛት በማድራስ ውስጥ ፊቱን ወደ ቻይና ምድር ትይዩ አድርጎ በመጸለይ ላይ ሳለ ነበር:: ዓለም አቀፋዊ ይዘት የነበረው የቶማስ ልብ፣ በምስራቅ አቅጣጫ እስከ ሕንድና በሕንድ ውቅያኖስ የባህር ዳርቻ እስከምትገኘው እስከ

ቤንጋል ድረስ ዘልቆ እንዲሄድ አድርጎታል:: እንደ ቶማስ ሁሉ ዓለም ዓቀፋዊ ይዘት የነበረው የጳውሎስ ልብ ደግሞ በምዕራብ አቅጣጫ ምናልባትም እስከ እስፔንና አትላንቲክ ውቅያኖስ ድረስ እንዲዘረጋ አስችሎታል::

ሕይወትህን፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ታላቅ ተልዕኮ ለሆነው በምድር ላይ የሚገኙ ሰዎችን ሁሉ በወንጌል የመድረስ ተልዕኮ በግልህ በታዘዝክበት መጠን መዝነው:: ሕይወትህን፤ አንተ ለክርስቶስ ከመታዘዝህ የተነሣ ወደ መንግስተ ሰማይ ሊገቡ ባሉት ሰዎች ቁጥር መዝነው:: ሕይወትህን፣ ዓለም አቀፋዊ ይዘት ባለው መታዘዝህ መዝነው::

ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰጠህ የወንጌል አገልግሎት ተልዕኮ ላይ በዘራኸው ዘር ረክቷልን? ሳልዳነው ዓለም አንተ በምታደርገው ጸሎትስ ረክቷልን? ህይወትህን በየዕለቱ በምትፀልይላቸው ህዝቦች ቁጥር መዝነው:: ሕይወትህን፣ በየዕለቱ በወንጌል አገልግሎት ዘመቻ ውስጥ ለሚጋደሉ ቢያንስ ለአንድ ወይም ከዚያ ለበለጡ ቡድኖች በምታደርገው እውነተኛ ጸሎት መዝነው::

አንተና እኔ ምናልባትም ለክርስቶስ በመታዘዛችን ረገድ በግል ለመጓዝ ውስኖች ልንሆን እንችላለን:: ነገር ግን ለወንጌል ዓለማቀፋዊ የሆነ ልባችንን የምንገልጽባቸው ሌሎች መንገዶችም አሉልን:: ዊልያም ካሪይ የተባለው ዓለም ዓቀፋዊ ይዘት ያለውን መታዘዙን የጀመረው፤ ገና ወጣት በነበረበት ጊዜ ጫማ እየሠራ በኢንግላንድ የምትገኝ አንዲት ትንሽ ቤተ ክርስቲያን የምታካሂደውን የወንጌል አገልግሎት በመደገፍ ነበር:: ሥራውን ከሚሠራበት አግዳሚ ወንበር ፊት ለፊት የዓለምን ካርታ በግድግዳው ላይ ሰቅሎ ነበር:: እንዲህ ዐይነቱን ካርታ ለመግዛት ግን



አቅም ያልነበረው እጅግ ደሃ ሰው ስለነበር ካርታውን የሠራው የራሱን ወረቀቶች አገጣጥሞ በመለጣጠፍ ነበር:: የእያንዳንዱን አገር ድንበር ይስላል፤ በድንበሮቹ ውስጥም የአገሪቱን ስም፣ የሕዝቡን ቁጥር፣ የቆዳ ስፋቱን፣ የሀገሪቱን ሀይማኖትና ስለሃገሪቱ ያገኛቸውን ማናቸውንም አንኳር የሆኑ መረጃዎች ይመዘግባል:: እናም ጫማዎቹን እየሠራ በዓለም ዙሪያ ስላለው ነገር ሁሉ ይጸልያል:: እግዚአብሔር ይህንን ሰው በጊዜው የዘመናዊ የወንጌል አገልግሎት መስራች፣ በህንድ ምድር በምትገኘው በካልካታ ብዙዎችን ያዳነ፣ በሠላሳ ስድስት ቋንቋዎች ለተተረጎሙ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች አርታኢና ተቆጣጣሪ አደረገው:: ልቡን ዓለም አቀፍ ይዘት በነበረው አገልግሎት ላይ የዘራ በመሆኑ ምክንያት እግዚአብሔር ለዚያ ጫማ ሰፊ ዓለም አቀፍ ይዘት ያለውን አገልግሎት ሰጠው::

ቻርልስ ካውማን የዓለምን ካርታ በመጠቀም የሚታወቅ ሚሲዮናዊ ነው:: ካርታዎቹ ግን በቢሮው ግድግዳዎች ላይ ተሰቅለው የተቀመጡ ብቻ አልነበሩም፤ በወንጌል አገልግሎት የደረሳቸውን ስፍራዎች ሁሉ በካርታው ላይ ምልክት ያደርግባቸዋል:: ስለአገራቱ በየተራ ይጸልያል፤ አንዳንድ ጊዜ በካርታው ላይ ወዳለ ስፍራ እያመለከተ፤ "አንድ ቀን ያችን አገር እንደርሳታለን" በማለት ይናገራል:: ታላቅ በሆነ የወንጌል አገልግሎት ዘመቻ ያምን ነበር፤ በ1924 እ.ኢ.አ ሕይወቱ ከማብቃቱ በፊት በኦ.ኤም. ኤስ አገልግሎቱ ሊደርስ የቻለው ጃፓንንና ኮርያን ብቻ ነበር:: ሆኖም ለሃያ አራት ዓመታት ያህል ለቻይና ያለማቋረጥ ጸልዮአል:: ዛሬ ኦ.ኤም. ኤስ በዐስራ አምስት አገሮች ውስጥ ተመሥርቷል:: ብዙዎቹ የኦ.ኤም.ኤስ መሪዎች በየቢሮቻው

ግድግዳ ላይ ወይም በጸሎት ክፍሎቻቸው ወስጥ የዓለም ካርታ አላቸው:: አንተም እኮ የዓለም ካርታዎችን በመጠቀም ዓለም አቀፍ ይዘት ያለውን የፀሎት አቅጣጫህን ልታሰፋው ትችላለህ:: ይህን ታደርገዋለህ?

በሕንድ አገር በነበሩኝ የመጀመሪያዎቹ ዓመታት፣ ሰዎች ያምኑ ዘንድ በሕንድ ካርታ ላይ የየአንዳንዱን ከተማ ስም እየጠራሁ እጸልይ ነበር:: በኋላ ላይ የሕንድን ምድር ስፋትና ልዩነት ስገነዘብ፣ እንደ ጀማሪ ሚስዮናዊ የነበረኝ የልምድ ማነስ አስቸጋሪ ሆኖብኝ ነበር:: ከዚያ በኋላ ግን የጸሎቴን የትኩረት አቅጣጫ አገልግሎት በምሰጥባቸው ስፍራዎች ላይ እንዲሆን አደረኩ:: ዛሬ ከአምሳ ዓመታት በኋላ እግዚአብሔር በአገልግሎቴ የኦ.ኤም.ኤስን ሥራ እንዲሰፋ በማድረጉ ከረዥም ዓመታት በፊት እንጸልይላቸው በነበሩ በየአንዳንዱ ከተማ ላይ አብያተ ክርስቲያናትን ለመመሥረት ችለናል:: እግዚአብሔር እነዚያን ጸሎቶች አልረሣቸውም:: ዛሬ በዓለም ዙሪያ ላሉ እጅግ በርካታ ከተሞችና ክፍለ ከተሞች እጸልያለሁ:: በመዝሙር 2፥8 ያለውን የተሰፋ ቃል ለመውረስ እፈልጋለሁ::

አንተ ወይም አንቺ ተማሪ፣ የቤት እመቤት፣ መጋቢ ወይም ምንም የተለየ ችሎታ የሌለህ ሰው ነህን? የሙያ መስክህ ምንም ይሁን ፍቅርህ ሰፊ ከሆነ፣ ጸሎትህና በተለይ ለወንጌል አገልግሎት በምትሰጠው ገንዘብ ሕይወትህን ዓለም አቀፋዊ ይዘትና አቅጣጫ ያለው ማድረግ ትችላለህ:: ልብህ የሚፈልገውን ያህል ትልቅ ከሆነ ዓለምን የምትደርስበት መንገድ አታጣም::

እግዚአብሔር ለኢየሱስ የሰጠው ትእዛዝ፣ "ለምነኝ፤ አሕዛብን ለርስትህ፣ የምድርንም ዳርቻ ለግዛትህ እሰጣለሁ" (መዝ



2፥8) የሚል ነው:: ዛሬ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ወኪልነታችን ይህንን የመጠየቅ ኀላፊነት የሚወድቀው በእኔና በአንተ ላይ ነው:: ለየትኛው አገር ነው አዘውትረህ የምትጸልየው? በጥያቄህ እንዴት ታማኝ ልትሆን እንደምትችል ጥቂት ሃሳቦችን ልሰንዝር:-

1. በጸሎት ዝርዝርህ ውስጥ ቢያንስ ሌሎች ሦስት አገሮችን አስቀምጥና በየዕለቱ ስለእነርሱ ለምን::
2. ከእነዚህ አገራት መሪዎች መካከል ቢያንስ ለአንዱ በየዕለቱ በስሙ ጸልይለት::
3. በእነዚህ አገሮች ባሉ አብያተ ክርስቲያናት የተሀድሶ እንቅስቃሴ እንዲቀጣጠል በየዕለቱ ጸልይ::
4. በእነዚህ አገሮች ያለውን የወንጌል አገልግሎት እንዲባርክና እንዲያሰፋ እንዲሁም በርካታ የወንጌል ሠራተኞችን እንዲያስነሣ (ማቴ 9፥37-38) በየዕለቱ ፀልይ::
5. በእነዚህ አገራት ወንጌል በነጻነት እንዲሰበክና መከሩንም እንዲያበዛው ወደ እግዚአብሔር ጸልይ::
6. በእነዚህ አገራት ውስጥ ማንኛውም ዐይነት ክርስቲያናዊ የወንጌል አገልግሎት ላላቸው ድርጅቶች ጸልይ::
7. በእነዚህ አገራት የሚኖሩትን ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔር እንዲባርክና ምሕረትን እንዲያደርግ ጸልይ::
8. በእነዚህ አገራት ላሉ በወንጌል ላልተደረሱ ሰዎችና ቡድኖች ጸልይ::

እግዚአብሔር በልብህ ውስጥ ላስቀመጣቸው አገራት አብልጠህ በጸለይክ ቁጥር፣ ለድነታቸው ያለህ ረሃብ ጥልቅ እየሆነ ይሄዳል:: ያንንም ርሃብ መንፈስ ቅዱስ ራሱ ይሰጥሃል:: ስለምትጸልይላቸው አገራት ሕዝቦች የምትችለውን ሁሉ እወቅ:: ካወቅከውም ነገር

ተነሥተህ ስለሚያስፈልጋቸው ነገር ጸልይ:: ዓለም አለምቀፋዊ ይዘትና አቅጣጫ ያለውን የጸሎት ህይወትህን፤ ለእነዚህ አገራት ኢየሱስ በሰጠህ ፍቅር መዝነው::

በወንጌል አገልግሎት ያለህን ተሳትፎ፤ በዕለታዊ የጸሎት ርዕስ ዝርዝርህ ወስጥ ባካተትካቸው በሌሎች አገራት ያሉ ሚስዮናውያን፣ መጋቢዎች ወይም ወንጌላውያን ቁጥር መዝነው:: ብዙዎቹ ሚሲዮናውያን፤ ለእነርሱ በምትጸልይበት ጊዜ ምስላቸውን አያየህ መጸለይ እንድትችል ፍቶግራፋቸው ያለበትን የጸሎት ካርድ በደስታ ይሰጡሃል:: ምናልባትም የዓለምን ወይም በተለይ የምትጸልይላቸውን አገራት ካርታ በግድግዳህ ወይም በጸሎት ማስታወሻ ደብተርህ ላይ ማስፈር ያስፈልግህ ይሆናል:: በዚያም ለሚገኙ ትልልቅ ከተሞችም ተራ በተራ ልትጸልይላቸው ትችላለህ::

ለዓለም ያለህን ፍቅር በጸሎት ማስታወሻ ደብተርህ በተለይ ለመዘገብካቸው እነዚህ አገራት በምትጸልይበት ጊዜ ዐልፎ ዐልፎ ለመጾም ባለህ ፈቃደኛነት መዝነው:: ፍቅርህንም በጸሎት ደብተር ዝርዝርህ ላይ ተጨማሪ አገራትን፣ በወንጌል ያልተደረሱ ህዝቦችን፣ ሃይማኖቶችን፣ ሚስዮናዊያንን፣ አገልጋዮችንና በተቻለህ መጠን ደጋግመህ ልትፀልይላቸው አቅድ የያዝካቸውን ጉዳዮች ለማካተት ባለህ ፈቃደኛነት መዝነው:: አንደ ልብህ ፈቃድ በርካታ ከሆኑት የዓለም አገራት መካከል ልትመርጥ ትችላለህ፤ እናም ፍቅርን በተሞላ ጸሎትህ ከዓለም ክፍል አብዛኛዎቹን ልትደርስና ልትሸፍን ትችላለህ::

ዓለም አቀፋዊ ይዘትና አቅጣጫ ያለውን ፍቅርህን፣ ወንጌል ወዳልሰሙት ሰዎች ይደርስ ዘንድ በምታደርገው ገንዘብ ነክ ተሳትፎህ መዝነው:: ምን ያህል ጊዜ ነው ራስህን በመካድ ዓለም



አቀፋዊ ለሆነ የወንጌል ዘመቻ የተለየ የፍቅር ስጦታ የሰጠኸው? ያለህበት አጥቢያ ቤተክርስቲያን በአንድ ወይም በብዙ አገራት ያሉ የወንጌል ዘመቻዎችን እየደገፈች እንደሆነ ተስፋ አደርጋለሁ:: ገንዘብን በመስጠት በዚህ እንቅስቃሴ ተሳተፍ:: ምናልባትም በወንጌል አገልግሎት ግዳጅ ላይ ስለተሣተፉና ወንጌላውያንን በማሰልጠን ላይ ስላሉ ስለ ሌሎች ሚስዮናዊ የአገልግሎት ድርጅቶች ለምተህ ይሆናል:: ለእነዚህ ተጨማሪ ስጦታዎችን እንድታደርግና በገንዘብህ እንድትደግፋቸው እግዚአብሔር ሊመራህ ይችላል::

ከምትደግፋቸው ሚስዮናውያን ጋር ከጊዜ ወደ ጊዜ መጻጻፍ ጠቃሚ ሆኖ ታገኘዋለህ:: ፍቅርህን የጠለቀ ለማድረግ ሌሎች መንገዶችን ለምሳሌም የቤተሰብ ፎቶግራፎችን የገናና የልደት ካርዶችን በመለዋወጥ መጠቀም ትችላለህ:: በምትችላቸው ሌሎች መንገዶች ሁሉ ፍቅርህን ግላዊ አድርገው::

ሕይወትህን፣ የጸሎት ትኩረት ለሰጠሃቸው ህገሮች እግዚአብሔር በሚሰጥህ እያደገ በሚሄድ ፍቅር መዝነው:: ሕይወትህን፣ ሚስዮናዊ ለሆኑ ዘመቻዎች ጊዜ መድበህ ለመጸለይ ባለህ ፈቃደኛነት መዝነው:: ሕይወትህን፣ በሌላው የዓለም ክፍሎች ላሉ ሕዝቦች መሥዋዕትነት ለመክፈል ባለህ ፈቃደኛነት መዝነው:: በወንጌል ዘመቻ አገልግሎት ባለህ ተሣትፎ ሕይወትህን መዝነው:: ፍቅርህን ዓለም አቀፋዊ ፍቅር አድርገው፤ ጸሎትህ ዓለም አቀፋዊ የምልጃ ጸሎት ይሁን፤ የገንዘብ ስጦታህንም ለክርስቶስ የቀረበ ዓለም አቀፋዊ የፍቅር ስጦታ አድርገህ አቅርብ:: ዓለም አቀፋዊ ክርስቲያን ሁን::

## ዓለም ሁሉ

ዓለም ሆይ አድምጥ፤ ማድረግ ከሚገባህ አጉድለህ እንዳታደርግ ተጠንቀቅ። ዓለም ሁሉ ሆይ አድምጥ፤ የእግዚአብሔርን የልብ ሐሣብ እንደ አዲስ ስማ! የእግዚአብሔር ታላቁ ሥራ ገና አሁን እንደጀመረ ተመልከት። በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሊደረሱና ለክርስቶስ ሊሸነፉ ይገባል። ፍቅርህ ወደ ሁሉም ሰው ይድረስ - በምድር ስፋት ሁሉ ይዘርጋ።

የእግዚአብሔርን ቅዱስ ጥሪ አድምጥ፤ አነሆ እንደ አዲስ ያስተጋባል። እግዚአብሔር ይፈልግሃል፤ አዎ ሁለንተናህን ይፈልጋል። ማድረግ ከሚገባህ አጉድለህ እንዳታደርግ ተጠንቀቅ። ወደ እያንዳንዱ ሕዝብ ልንራመድ የክርስቶስን ወንጌል ልንሰብክ ግድ ነው። ለእያንዳንዳችን ጥሪና ዕቅድ ተዘጋጅቷል። እግዚአብሔር አሺ እንዳልክ ይቁጠርህን?

ታይ ዘንድ እግዚአብሔር ዐይንህን ይግለጥ፤ ወደ ቀራኒዮ ተመልከተህ አዲስ እርምጃ ልትጀምር የግድ ነው። በጌታ እግሮች ሥር ወድቀህ ሕይወትህን፣ ነፍስህንና ሁለንተናህን አስረክብ። ያን ጊዜ የእግዚአብሔርን ጥሪና ፈቃድ ታውቃለህ። ያለማቋረጥ ፊቱን ፈልግ።

በእግዚአብሔር ዘንድ ለአንተ የሚሆን እንባ አና፤ ጸሎት አለው። ታጭዳቸው ዘንድ ያዘጋጀልህ



ነፍሳት አሉት። ዛሬ እግዚአብሔር ይፈልግሃል። አንተ የምትገኘው እግዚአብሔር ለፍጥረተ ዓለሙ ሁሉ ባቀደው ዕቅድ ውስጥ ነው። መክፈል የምትችለውን ያህል ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ ነህን? ዛሬ ማፍራት የምትችለውን ፍሬ ሁሉ አፍራ።

ዊስሌይ ዱዌል

# 17

# በመሥዋዕትነትህ ሕይወትህን መዝን

ብዙውን ጊዜ እኛ ራሳችንን ለመመዘን ከምንገለገልባቸው ነገሮች ይልቅ እግዚአብሔር እኛን ለመመዘን የሚጠቀምባቸው መመዘኛ ዎች እንዴት የተለዩ ናቸው! እግዚአብሔር ሕይወታችንን ሲመዝን ያለማቋረጥ ከሚጠቀምባቸው መመዘኛዎች መካከል አንዱ መሥዋዕትነት ነው:: ሕይወትህን በመሥዋዕትነትህ መዝነው::

ሌሎችን በመሥዋዕትነታቸው እንዴት እንደምትመዝናቸው ልብ በል:: መሥዋዕትነት የሚጀምረው እግዚአብሔር ብቻ ሌላ ማንም ለው ሊያየው በማይችለው የልብ ዓለም ውስጥ ነው:: እርግጥ ነው በተለያዩ የሕይወትህ አቅጣጫዎች የሚገለጥ ቢሆንም፣ ግን ወደተሳሳተ ድምዳሜ ሊያመራ ይችላል:: ጥልቅ የሆኑት መሥዋዕቶች ብዙውን ጊዜ በለው እይታ ጎልተው የሚታዩት ነገሮች አይደሉም:: የራስህን መሥዋዕትነት መዝነው፤ ይሁን እንጂ የሌሎችን መሥዋዕት እግዚአብሔር ብቻ እንዲመዝን ተውለት::

የተሰጠ (የተሠዋ) ሕይወት የመንፈሳዊ ሕይወት ዘይቤአችን አካል ሊሆን እንደሚገባው ሐዋርያው ጳውሎስ አበክሮ ያበረታታል:: እርሱ የሚሰጠው ምሣሌያዊ መግለጫ ምናልባትም በዚህ ዘመን ከምንኖር ለዎች ይልቅ እጅግ ጮኾ የሚናገረው በእርሱ ዘመን ለነበሩ አይሁዳውያን ነው:: እያንዳንዱ አይሁዳዊ በቤተመቅደስ ውስጥ መሥዋዕትን የማቅረብ ልምምድ ነበረው:: መሥዋዕት ሆኖ በፍጹም መስጠት ለቀረበው ለዚያ እንስሳ መሥዋዕት ማለት ሞት እንደሆነ ጳውሎስ ያውቃል:: በዚህ ዘመን ራሳችንን ሕያው መሥዋዕት አድርገን ልናቀርብ ይገባናል (ይህም ሲባል ያለ ምንም



ጥርጥር ሁለንተናችንን ያጠቃልላል):: ለመሥዋዕት የሚቀርበው እንስሳ ለሞት ታልፎ ይሰጥ እንደነበረ ሁሉ፣ ለእግዚአብሔር አንኖር ዘንድ ሙሉ ለሙሉ ልንሰጥ ያስፈልገናል:: ልዩነቱ ያለው እኛ ራሳችንን የምናቀርበው በፈቃዳችን ሲሆን፣ እንስሳው ግን በሌላ ሰው ፈንታ የሚቀርብ መሆኑ ነው::

". . . እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ! እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው::" (ሮሜ 12፥1):: በዚህ ጥቅስ ውስጥ ያለውን የአተረጓጎም ለፋት ልብ በል::

1. ከልጁ ከክርስቶስ ኢየሱስ የመስቀል ሞት የተነሣ ድነትህን በእርሱ ምሕረት ስለተቀበልክ የእግዚአብሔር ባለዕዳ ነህ:: ማለቂያ የሌለው ምሕረቱ ተቀባይ በመሆንህም እንዲሁ ባለዕዳ ነህ:: ለእግዚአብሔር ፍጹም በሆነ መስጠት - መሥዋዕትነትን የሚጠይቅ መስጠት፣ ምንም ያህል ዋጋ ያስከፍል ያንን ዐልፎ የሚሄድ መስጠት - የሚጠበቅብህም በዚህ ታላቅ በሆነ ባለዕዳነትህ የተነሣ ነው::

2. መስጠትህ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት:: በነጻነት ራስህን የመስጠትህ ምክንያት እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ካደረገልህ ነገር የተነሣ ሊሆን ይገባዋል::

3. መስጠትህ፤ ከእግዚአብሔር ከተቀበልከው ምሕረት የተነሣ በውስጥህ ከተፈጠረ ፍቅር የሚመነጭ ሊሆን ያስፈልገዋል:: ፍቅር ለሚወደው መሥዋዕት ለመሆን ደስተኛ ነው::

4. መስጠትህ ሙሉ ለሙሉ እንደሚቃጠል መሥዋዕት ቅዱስና ፍጹም፣ ሙሉ መስጠትና አምነት የተሞላበት፣ ምንም ያህል ዋጋ

ያስከፍል ፍጹማዊ መሰጠት ሊሆን ይገባዋል:: በእግዚአብሔር ዘንድ ያለብህ ዕዳ ከሁለንተናህ ይበልጣል::

5. መሰጠትህና ከዚህም የሚገኝ ፍቅርን የሚተገብር ሕይወትህ ያ መንፈሳዊ የሆነ አምልኮህ ነው:: "መንፈሳዊ" የሚለው ቃል "ማስተዋል" ተብሎ ሊተረጎምም የሚችል ከመሆኑም በላይ ሁለቱንም ትርጉሞች አካቶ የሚይዝ ሐሳብ ያለው ነው::

አስተዋይና ጥበበኛ አመለካከት ካለህ ኢየሱስ ክርስቶስ ለአንተ ከተሰጠበት መሰጠት ያነሰ ነገር ልታደርግ አትችልም:: እግዚአብሔርን ይህን ያህል መውደድ፣ ራስህንና ሁለንተናህን ፍጹማዊ በሆነ ሁኔታ ለእግዚአብሔር መስጠት አምልኮ ነው::

6. "መሰጠት" ወይም "ማቅረብ" የሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ ኀላፊ ጊዜን ያመለክታል ሰዋሰዋዊ በሆነ አጠቃቀም ይህ ማለት ዘላቂ ለሆነ ውጤት ወቅታዊ የሆነ ፈጣን ምላሽ መስጠትን የሚያሳይ ነው:: ይህ ሊለወጥ የሚችል ራስን መሰጠት አይደለም:: የታሰበበትና የፍጻሜ ግብ ያለው ተግባር ከመሆኑም በላይ ከተጀመረበት ጊዜ እንስቶ እስከመጨረሻው ድረስ መንፈሳዊ የሆነ የሕይወት እንቅስቃሴህን የሚወስን ነው:: ራስህን ያለማቋረጥ መሥዋዕት አታደርግም፤ ነገር ግን ዘላቂና ያለማቋረጥ በሆነ መሰጠት መንፈስ ቅዱስ እንደመራህ መሥዋዕት ሆነህ ለመቅረብ ዝግጁ መሆን ትችላለህ:: ይህ አዋንታዊ ገጽታ ያለው ታላቅ መሰጠት ነው::

ይህ ሙሉ የሆነ መሥዋዕት አድርጎ ራስን የማቅረብ ዝንባሌ የሚተገበርባቸው በርካታ መንገዶች አሉ:: ራስህን፣ ቤተሰብህን፣ ጊዜህን፣ ገንዘብህን ለአገልግሎት መሰጠትን ሊያካትት ይችላል:: ይህ ራስን የመካድ ዝንባሌም ነው:: መሰቀልህን መሸከም ነው:: ኢየሱስ



እንዲህ አለ፤ "በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር፣ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ" (ሉቃ 9፥23)::

ራስን መካድ፣ መሰዋእትነት ለሚለው ቃል ተለዋጭ ቃል ሊሆን፣ ይህም የክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር አንድ አካል ነው:: ደቀ መዝሙር የትኛውንም ዋጋ እየከፈለ ሊከተል ዝግጁ ሊሆን ይገባል:: መስቀሉን መሸከም ማለት በአዲስ ኪዳን አንድ ነገር ማለት ብቻ ነው:: መስቀል የሞት ፍርድ የተፈረደበት ሰው ተሸክሞት ወደ መገደያው ስፍራ የሚወሰደው የመግደያ መሣሪያ ነው:: መልካም ጌጥ ወይም የፍቅር ምሳሌ አይደለም:: መስቀሉን ተሸክመህ መከተል ማለት ወደ መገደያህ ስፍራ እንድትወጣ የሚመራህ ነው::

ኢየሱስ "የእኔ ደቀ መዝሙር መሆን ማለት ለእኔ ለመሞት ፈቃደኛ መሆን ማለት ነው" ማለቱ ነው፡ በተጨማሪም አንድ ነገር ልብ በል፣ መስቀሉ በራሱ መጥቶ አንተ ላይ አይቀመጥም:: አንተ ራስህ ነህ በፈቃደኝነት አንሥተህ የምትሸከመው:: ይህ በበሽታ መድቀቅን የሚመለከት አይደለም:: አንተ ለመታመም ፈቃደኛ በመሆን በሽታን በራስህ ላይ አታመጣምና:: ተገደህ የምታደርጋቸውን ነገሮች ሁሉ የሚያካትት አይደለም:: ጎንበስ ብለህ በፈቃደኝነት መስቀልህ በማንሣትና በመሸከም ኢየሱስን ዕለት ዕለት መከተልን የግድ ይላል:: አዎ ይህ ማለት አንተን በግል ከፍተኛ የሆነ ዋጋ የሚያስከፍልህ፣ ለክርስቶስ በነፍስህ እንድትወራረድ የሚጠይቅ ጉዳይ ማለት ሊሆን ይችላል::

በዚህ ዘመን ያሉ ክርስቲያኖች ደቀ መዝመር ለሚለው ቃል ያላቸው ግንዛቤ ቀለል ያለ ነው:: ዛሬ አብዛኛው የክርስትና ሕይወት ልምድ አንዳችም ዋጋ የሚከፍል አይደለም:: ኢየሱስ ተከታዮቹ በፈቃደኝነት ዋጋ እንዲከፍሉ፣ አስፈላጊ ሆኖም ሊገኝ ለእርሱ

መከራን ለመቀበል ፈቃደኞች እንዲሆኑ ይፈልጋል:: የመንፈሳዊ ሕይወትህ ዕለታዊ ባሕርይ ይሆን ዘንድ እርሱ የሚፈልገውና የሰጠህም የተቀደሰ ግዳጅ ይሄው ነው::

ሕይወትህን፣ ስለ ክርስቶስ ብለህ ራስህን ለመካድ ባለህ ፈቃደኝነት መዝነው:: ምንም እንኳን በግልህ ዋጋ የሚያስከፍልህ ቢሆንም እግዚአብሔርን ትታዘዝና ታከብር ዘንድ የሚፈጠሩልህን አጋጣሚዎች በጥንቃቄ ተመልከት:: ለኢየሱስ ያለህን ፍቅር፣ መንፈስ ቅዱስ በመራህና ለእግዚአብሔር ክብር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መከራን ለመቀበል ባለህ ፈቃደኝነት መዝነው::

ሕይወትህን፣ አስበህበትና ቆም ብለህ መስቀሉን ለመሸከም በመረጥክባቸው ሁኔታዎች ብዛትና ስለ ኢየሱስ ብለህ መስቀሉን ለመሸከም ባለህ ብቃት መዝነው:: ሕይወትህን፣ ለኢየሱስ መሥዋዕት ለመሆን የሚፈጠሩልህን አጋጣሚዎች ነቅተህ በመጠበቅ ዝንባሌህ መዝነው::

መሥዋዕትነት ምናልባትም ገንዘብ ነክ ነገሮችን ሊያጠቃልልም ላያጠቃልልም ይችላል:: ገንዘብ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የምታደርገው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለኢየሱስ በጣም ጠቃሚ ነው:: አሰጣጥህን የሚያስተውለው በአትኩሮት ነው:: በኢየሩሳሌም፣ ሰዎች ለእግዚአብሔር ሥራ የሚሰጡትን ስጦታ ይመለከት ነበር (ማር 12፥41):: እንደዚያ ያለው የዐሥራት አወጣጥ መበረታታት እንዳለበት ያስተማረ ቢሆንም፣ በመሥዋዕትነት መንፈስና ጽድቅን በተሞላ ሕይወት መደረግ እንዳለበት ተናግሯል (ማቴ 23፥23):: ዐሥራት ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ስጦታ ተደርጎ በጭራሽ መወሰድ የለበትም:: ዐሥራት ለእግዚአብሔር ያለብህ ዕዳ ነው:: ማንም ያለበትን ይህን የዐሥራት



ዕዳ መክፈል ቸል ቢል እግዚአብሔርን እንደሰረቀ ይቆጠራል (ሚል 3፥8-9)፤ ብዙ ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን መስረቅ በመቀጠላቸው ከፊል "እርግማን" ወይም ቢያንስ ቢያንስ ታላላቅ ባርኮቶች ወደ ሕይወታቸው እንዳይመጡ ሆኖባቸው ይሆን? እግዚአብሔር በአንተ ላይ ያለውን ዕዳ እስክትከፍል ድረስ መሥዋዕትነት ያለበት ስጦታህ በፊቱ የሚታሰብ አይደለም:: ሕይወትህን፣ በገንዘብ አሰጣጥህ መዝነው::

ሕይወትህን፣ የክርስቶስ መንግሥት እንዲሰፋ ቅንጦትህንና ምቾትህን ትተህ የበለጠ ነገር ለእግዚአብሔር ለመስጠት ራስህን በመካድህ መዝነው:: አመለካከትህ ላይ ጥንቃቄ ልታደርግ ከሚገቡህ ስፍራዎች አንዱ እዚህ ጋ ነው:: እኔ ቅንጦት ብዬ የምቆጥረው ነገር፤ ምናልባት አንተ እንደምትኖርበት አካባቢና እንደምትሠራው ሥራ ሁኔታ ለአንተ ለሕይወትህ መሠረታዊ ነገር ሊሆን ይችላል:: ጤነኛ ለሆነ ሰው የቅንጦት የሆነ ነገር፣ ለታማሚና ለደካማ ሰው አስፈላጊው ነገር ሊሆን ይችላል:: ለወላጆች የቅንጦት የሆነ ነገር፣ ለልጅ እጅግ አስፈላጊው ሊሆን ይችላል:: ሌሎች ራሳቸውን የካዱበትን ሁኔታ ለመመዘን አትሞክር:: ራስህን ብቻ መዝን::

በሚቀጥለው ጊዜ ለምትለብሳቸው ልብሶች፣ ራስህን ለማስዋብና ለቤትህ ወጭዎችን በምታወጣበት ጊዜ እግዚአብሔር ለአንተ የተለየ ሐሳብ እንዳለው ጠይቀው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቀለል ያለ ኑሮ ከመንፈሳዊነት ጋር ተያይዞ እናገኘዋለን:: ብዙ ነገሮች ኀጢአት ላይሆኑ ይችላሉ፤ ይሁን አንጂ መሥዋዕትነት ያለው መንፈስ እንዳይኖርህ እንቅፋቶች ሊሆኑ ይችላሉ:: ንጽሕናችን፣ በአግባቡ መልበሳችንና ቀለል ያለ መስህብ ያለው ገጽታችን ለእግዚአብሔር ያለንን ምስክርነት ያጠናክረዋል:: ነገር

ግን በአለባበስህ፣ በጠባይህ፣ በመዝናናትህና በቤትህ ውስጥ ስላለው ነገር እግዚአብሔር በሹክሹክታ ድምፅ የሚናገረው ነገር ይኖር? እርሱን ጠይቀህ እስክትረዳ ድረስ አጅግ እርግጠኛ አትሁን:: ሕይወትህን፤ መሥዋዕትነት በተሞላበት የዕለት ተዕለት የሕይወት እንቅስቃሴህ መዝነው::

ወላጆቼ ትህትና በተሞላበት፣ ቀለል ላለ የሕይወት (የኑሮ) ዘይቤና ለኢየሱስ ክርስቶስ ባላቸው የመሥዋዕትነት መንፈስ መልካም ምሣሌዎች ነበሩ:: ግላዊ ለሆኑ ፍላጎቶቻቸው በተቻላቸው መጠን ጥቂት ወጭዎችን ብቻ ያወጣሉ:: ቀላል ነገር ይመገባሉ፣ በቀላሉ ይኖራሉ፤ የቻሉትን ሁሉ ለሚሲዮናዊ ተልዕኮዎችና ለሌሎች የወንጌል እንቅስቃሴዎች ይሰጣሉ:: ከእነርሱ ምንም ዐይነት በገንዘብ የሚለካ ነገር አልወረስኩም ማለት ይቻላል፤ ይሁን እንጂ የባርኮትንና የጸሎትን ሀብት ወርሼአለሁ::

እ.ኤ.አ በ1893 ቻርልስ ካውማን የተባለ ሰው ወደ ጌታ ከመጣ ከዘጠኝ ወራት በኋላ እርሱና ባለቤቱ በሙዲ የመጽሐፍ ቅዱስ ተቋም ውስጥ በአንድ የሚስዮናውያን ጉባኤ ላይ በመሳተፍ ላይ ነበሩ:: የጉባኤው መሪና የክርስቲያንና የወንጌል ተልዕኮ ኅብረት መሥራች የነበሩት ኤ.ቢ. ሲምፕሰን፣ ወጪዎቹን በሚመለከት በእግዚአብሔር ላይ በመታመን ከሚስቱ ጋር ለወንጌል አገልግሎት ወደ አፍሪካ ለመሄድ ስለወሰነ አንድ ክርስቲያን ነጋዴ ሲናገሩ ቻርልስ ካውማን በተመሰጦ ያደምጥ ነበር:: ካውማን የወር ደመወዙን ተቀብሎ በኪሱ ይዞ ነበር:: ስጦታው በሚሰበሰብበት ወቅት በኪሱ የነበረውን ቦርሳ አውጥቶ የነበረውን ሁሉ በመሰብሰቢያው ሳህን ውስጥ አራገፈ::



ጥቂት ቆይቶ ደግሞ ዶክተር ሲምፕሰን ለሌላ ተግባራዊ ግዳጅ የሚውል መባ ጠየቁ:: አሁን ደግሞ ምን ሲፈጠር ይሆን? ሚስተር ካውማን ድንገት በእጁ ላይ የነበረውን ባለ ወርቅ ሰንሰለት ሰዓቱን አውልቆ በእጁ ያዘ:: ወደ ሚስቱ ዘወር ብሎ ዐይኖቿን ተመለከተና ፈገግ አለ:: ወደ እርሷም እጆች ቁልቁል ተመለከተ:: አንቆቅልሽ ሆነባት:: ቻርልስ ምን ለማለት ፈልጎ ነው? አንደገና ቀና ብሎ ዐይኖቿን ተመለከተና ፈገግ አለ:: እንደገናም ቁልቁል ወደ እጇ ተመለከተ:: ነገሩ ገባት! አ ! በጭራሽ አይሆንም ስትል አሰበች:: ነገር ግን የወርቅ ሰዓቱን በእጁ እንደያዘ እጠገቧ ተቀምጧል:: ከአልማዝ የተሠራውን የጋብቻ ቃል ኪዳን ቀለበቷን አወለቀች:: የመባ መሰብሰቢያው ሳህን ዞሮ እነርሱ ዘንድ በደረሰ ጊዜ ሰዓቱን፣ የወርቁን ሰንሰለትና የአልማዙን ቀለበት ይዞ አብስ አለ::

ከዚያ ጊዜ በኋላ ጥቂት ቆይቶ፣ ነጋዴው ቻርልስ ካውማን ግላዊ ለሆኑ ጉዳዮቹ ከሚያስፈልገው ወጪ በስተቀር ከንግዱ የሚያገኘውን ትርፍ ሁሉ በየወሩ ለእግዚአብሔር ለመስጠት ወሰነ:: አንድ ቀንም ሚስቱን እንዲህ አላት፤ "እኛ ልጆች የሉንም:: አሁን የምንኖርበት ይህ ትልቅ የመኖሪያ ቤት ለእኛ የሚያስፈልገን አይደለም:: ለሌሎች እናከራየውና እኛ አነስተኛና ቀላል ወደሆነ በጋራ የመኖሪያ ሕንፃ እንዘዋወር:: ከቤቱ የሚገኘውንም ኪራይ ለወንጌል አግለግሎት እንላክ":: እናም እንደምክራቸው አደረጉ::

ይሄው የመሥዋዕትነት መንፈስ ነበር "ሁሉም ነገር ለኢየሱስ" በሚለው ተግባራዊ ተልዕኮ ለመሣተፍ እ.ኤ.አ በ1901 ባልና ሚስቱ እስከዘለቄታው ለሆነ የዕለት ተዕለት የመሥዋዕትነት ግዳጅ ራሳቸውን እንዲሰጡ ያስቻላቸው:: ብዙ ለመስጠት ቀለል ያለ ኑሮ ብቻ አልነበረም የኖሩት፤ ይልቁን ለጥንካሬያቸውና

ለጤንነታቸው አስፈላጊ የነበሩ ነገሮችን እንኳን ቸል እስከማለት ደርሰዋል:: የትኛይቱም ትርፍ ጊዜያቸው ከጌታ የተሰጣቸውን ተግባራዊ ግዳጅ ለመፈጸም ለጸሎት፣ የጌታን ቃል ለማጥናት፣ ለምስክርነትና መንግስቱን ለማስፋት ጠቃሚ የሆነ ማንኛውንም ሥራ ለመሥራት ትውላለች:: ለእርሱ ይሠሩ የነበሩ ሰባ አምስት የሚያህሉ የቴሌግራፍ ኦፕሬተሮቹን ጌታን ባገኙ በመጀመሪያዎቹ የስድስት ወር ጊዜያት ውስጥ ለጌታ ቢማርክ የሚያስደንቅ ነገር አይደለም:: እነዚህን ሰዎች በመጠቀም የቴሌፎን ኦፕሬተሮችን የጸሎት ቡድን አቋቋመ:: እንግዲህ ዛሬ እ.ኤም.ኤስ ዓለም አቀፍ ሲሆን የበቃው ይህ ቡድን ነው:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እ.ኤም.ኤስ በእግዚአብሔር ሕዝብ መሥዋዕትነት እየሰፋ ሊሄድ ችሏል::

ስታንሌይ ክርስግ እና ሚስቱ ዶሮቲ በቅርብ ጊዜ ሽልማታቸውን ወደሚቀበሉበት ዐልፈዋል:: ፤ የክርስግና ኬ.ማርት መጋዘኖች ባለቤት የሆነው ሚስተር ክርስግ ሁልጊዜም መጽሐፍ ቅዱሱን ይዞ የሚንቀሳቀስ ክርስቲያን ነበር:: ይህ ሰው ለብዙ ክርስቲያን የሥራ ባልደረቦቹና የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጆቻቸውን ሕንፃ ለመገንባት ለሚፈልጉ ተቋማት መጠነ ሰፊ የሆነ ድጋፍ በማድረግ ብቻ የተወሰነ አልነበረም፤ ይልቁንም በርካታ ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች ለሕንፃ ግንባታ የሚያስፈልጋቸውን ወጪ በመሸፈንም ጭምር ይረዳቸው ነበር:: የእርሱ ድርጅት ከሚሰጠው በሚሊዮን ከሚቆጠር ገንዘብ በላይ፣ ከራሱ ወጪ ላይ በመቀነስ በልገሳ እንደሚሰጥ እኔ በግሌ አውቃለሁ::

ክርስግስና ባለቤቱ ይህንን ያህል ገንዘብ መስጠት የቻሉት እንዴት ነው? በሚችጋን ግዛት በምትገኘው በገጠሪቱ ትሮይ በሚገኝ ቀለል ባለ ገንዘብ በተሠራ ቤት ውስጥ በመኖር ነው::



የቤት ውስጥ ሥራዎችን የሚያከናውኑትና ራሳቸው ወ/ሮ ክርስግ ሲሆኑ፣ ልባቸውና ነፍሳቸው ጭምር ከባለቤታቸው ጋር አንድ ነበር:: ቀለል ያለ ሕይወት ይመራሉ፤ ሞዴላቸው ያረጀ መኪናዎችን ይነዳሉ:: አንድ ጊዜ ከአስበሪይ ኮሌጅ ወደቤታቸው ሲመለሱ 400 ማይሎች ያህል መኪናቸውን እየነዱ መጓዝ እንደነበረባቸውና አብዛኛውንም ጊዜ መኪናዋን የሾፈሩት ባለቤታቸው ዶሮቲ እንደነበሩ ክርስግ ጽፈዋል::

ሚስተር ክርስግ ለልብሶቻቸው የሚያወጡት ዋጋ ቀለል ያለ ነው:: በቤት ወጪአቸውም ላይ የሚከተሉት ይህንኑ መርሕ ነው:: በተለያዩ አጋጣሚዎች በቤታቸው ለማደር ዕድል አጋጥሞት የነበረ ሚሲዮናዊ እንደተናገረው በቁርስ የገበታ ወንበር ላይ ተቀምጦ፣ ወ/ሮ ዶሮቲ ለመጋል አክል ከገጠመው የሥጋ መጥበሻ ጋር በብርቱ ሲታገሉ ተመልክቷል:: የመጥበሻ ቁሳቁሱን ጎንና ጎን በእጃቸው እየቀጠቀጡ መሥራት እንዲጀምር ብዙ ጥረት አድርገዋል:: ለእኔም እንዲህ አሉኝ፤ "በአሳቤ የታዩኝ በመላ አገሪቱ በሚገኙ የወይዘሮዋ የሸቀጣ ሸቀጥ መደብሮች ውስጥ በረድፍ የተደረደሩት አዳዲስና እንጸባራቂ የመጥበሻ ቁሳቁሶች ናቸው:: እዚህ ግን እርሳቸው ባረጀና ዘመኑን በጨረሰ ቁሳቁስ ይጠቀማሉ":: ነገር ግን ይህ ቀለል ያለ መንፈስ ነው መስጠት ይችሉ ዘንድ ብዙ ገንዘብ እንዲኖራቸው ያደረገው::

ባልና ሚስቱ ለመጓጓዣ ብዙ ገንዘብ አያወጡም:: በሴኡል የሚገኘውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በክርስግ የአስተዳደርና የመማሪያ ክፍሎች ግንባታ በጎ ፈቃድ ተገንብቶ ሲመረቅ ከእርሳቸው ጋር አብሬ በነበርኩበት ጊዜ፣ ከሀገራቸው ሲወጡ ያ የመጀመሪያ ጊዜያቸው እንደሆነ ተረድቻለሁ:: ሲጓዙም

በቀላሉ ነው፤ ግላዊ የሆኑ ቁሣቁሶቻቸውን መከተቻ ሻንጣ እንኳን አይዙም:: በምረቃ ሥነ ሥርዐቱ ላይ ንግግር እንዲያደርጉ ሲጠየቁም፤ ከመቀመጫቸው ተነስተው እጆቻቸውን ወደ ሰማይ በመዘርጋት፤ በቀላሉ ግን በፍጹም ደስተኝነት፤ "ሁሉንም ባርኮቶች ለሚያፈስልን ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን" ብለው ተቀመጡ:: ነገር ግን 1800 የሚያህሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ሁሉ ለእግዚአብሔር ሥራ እየተዘጋጁ ናቸው - ስለ ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን:: እኚህ ሰው አንድም ጊዜ መሥዋዕት እየከፈሉ መሆናቸውን ተናግረው አያውቁም፤ ነገር ግን በእርሳቸው ታማኝነት በሺዎች የሚቆጠሩ ተባርከዋል::

አር. ስታንሌይ ታም፤ ከአሃዮ ግዛት የሲማ ተወላጅና ለዓመታት ያህል የኦ.ኤም. ኤስ ዓለም አቀፍ ቦርድ ምክትል ፕሬዝዳንት በመሆን ያገለገሉ ሲሆን፣ እኚህ ሰው መሥዋዕትነት በተሞላበት ስጦታቸው እግዚአብሔርን አክብረዋል:: ንግዳቸውን የጀመሩት በባዶ እጅ ነው ለማለት ይቻላል፤ ከአንድ ቤት ወደ ሌላው ቤት፣ ከአንድ አገር ወደ ሌላው በመዘዋወር:: አንዳንድ ጊዜ በምሽት ወደ ቤታቸው ተመልሰው ለመሄድ የሚያስፈልጋቸውን የነዳጅ ወጭ ለማግኘት ወደ እግዚአብሔር ይጸልዩ ነበር:: ገና በንግዳቸው መነሻ ላይ እግዚአብሔርን የንግድ ሥራቸው አጋር በማድረግ ከትርፋቸው አምሣ አንድ በመቶውን መስጠት ጀመሩ:: ደረጃ በደረጃም እርሳቸውና ባለቤታቸው ጁኒታ ቀላልና ከባድ በሆኑ ጉዳዮች ላይ እየጸለዩ በመወያየት ጀመሩ:: ከብዙ ጸሎት በኋላ ሕጋዊ በሆነ መንገድ ጌታ የካምፓኒው ባለቤት እንዲሆን አሳልፈው ሰጡ:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በእግዚአብሔር ካምፓኒ ውስጥ እንደተቀጠረ አንድ ሠራተኛ የወር ደመወዝ ብቻ በመውሰድ



መሥራት ጀመሩ:: የሚገኘው ትርፍ ሁሉ ለወንጌል አገልግሎት ሥራና በ150 አገራት ኦ.ኤም.ኤስ ዓለም አቀፍ በሚተክላቸው አብያተ ክርስቲያናት ለሚሠሩ ቡድኖች ይላካል:: ከዚህም በተጨማሪ በግል ከሚያገኙት ደመወዛቸው ላይ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸውን፣ ቤተ እምነታቸውንና ሌሎችንም በቸርነት ይደግፋሉ:: በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ እንዲሰብኩ ያለማቋረጥ ይፈለጋሉ፤ የነጋዴዎችና የከንቲባዎችን ኅብረት የማለዳ ጸሎት ይካፈላሉ፤ እጅግ ብዙዎችንም በስልክ ያማክራሉ:: ለበርካታ ዓመታትም በግል ምስክርነታቸው፣ በስብሰባዎች፣ በሥነጽሑፍና ስልክ በመጠቀም በቀን በአማካኝ አራት ሰዎችን ለክርስቶስ ይማርካሉ::

ቤተሰቡ አሁንም የሚኖረው ቀለል ያለ ኑሮ ነው፤ ሰውዬው በየዕለቱ ምሳቸውን በወረቀት ቦርሳ ውስጥ አድርገው ይሄዳሉ:: ረዥም ሰዓት ይሠራሉ፤ እርሳቸውና የልጃቸው ባል ለወንጌል አገልግሎት አንድ ዶላር ለማትረፍ ሲሉ ማድረግ የሚችሉትን ሁሉ ያደርጋሉ:: ድርጅታቸው የአድራሻ ለውጥ ባደረገ ጊዜ የጭነት መኪና በመከራየት የማጓጓዝ ሥራውን የሠሩት ራሳቸው ነበሩ:: ብዙውን ጊዜ እስከ ውድቅት ድረስ አምሽተው ይሠራሉ፤ የመጻሕፍት መደርደሪያዎችን በአግባቡ ስፍራቸውን ለማስያዝ አንድ ሳምንት ፈጅቶባቸዋል፤ ቀለሙን የቀቡትም እነርሱው ናቸው:: ይህ ሁሉ ፍቅር የተሞላበት መሥዋዕትነት የተከፈለው ለኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ገንዘብ ለመስጠት ሲባል ነው:: ሙሉና የተጠናቀቀ ዘገባ ያለው እግዚአብሔር ቢሆንም ኦ.ኤም.ኤስ ዓለም አቀፍ ወደ ዘጠኝ መቶ የሚጠጉ የአብያተ ክርስቲያናት ማህበረ ምዕመናን መመሥረታቸውን ከ200,000 የሚበልጡ አዲስ አማኞች በእነዚህ

አብያተ ክርስቲያናት አባላት መሆናቸውን ይህም የሆነው መሥዋእትነት በተሞላበት የእርሳቸው ተግባር ቀላል የአኗኗር ዘይቤ፣ በዘሩት ጊዜያቸው፣ ፍቅራቸው፣ ሕይወታቸውንም ለክርስቶስና ለነፍሳት በመስጠታቸው ምክንያት መሆኑን ያውቃል።

ሕይወትህን፤ መሥዋዕትነት በተሞላበት የጊዜ አጠቃቀምህ መዝነው። የጊዜን ያህል እጅጉን የሚባክን ነገር የለም። ልብህ የሚመዘነው ልትተገብራቸው ጊዜ ባገኝህላቸው ነገሮች ነው። ብዙ ሰዎች ጊዜ የሚያገኙት በእርግጥ መሥራት ለሚፈልጓቸው ነገሮች ነው። አንተ በእርግጥ መጸለይ የምትፈልግ ከሆነ ማኅበራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ያለህን ተሳትፎ ትቀንሳለህ፤ የጠዋት ቁርስህን በመጾም በቁርስ ጊዜህ ትጸልያለህ፣ በማለዳ ትነሣለህ ወይም ደግሞ ከሌላ ጉዳይ ቀንሰህ ጊዜህን መሥዋዕት ታደርጋለህ። በእርግጥ የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት የምትፈልግ ከሆነ፣ ጋዜጦችን ለማንበብ የምታቃጥለውን ጊዜ ትቀንሳለህ ወይም ለሌላ ጉዳይ ከመደብከው ጊዜ ላይ ትቆርጣለህ። መሰዋእትነትን በመክፈል በየዕለቱ አምስት ምዕራፎችን ለማንበብ ፈቃደኛ ነህ? እንዲህ በማድረግህስ ከዘፍጥረት ጀምሮ እስከ ራዕይ ያሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በአንድ ዓመት ውስጥ መጨረስ መቻልህንስ ታውቃለህ? ልታደርገው ደስ ለሚልህ ነገር መሥዋዕት የምታደርግለትን ጊዜ በፍጹም አታጣም።

ለኢየሱስ ክርስቶስ ብለህ የምታደርጋቸውን ሌሎች መሥዋዕትነቶች ሁሉ መመዘን ትችላለህ። የእግዚአብሔርን ጥሪ ለመታዘዝ ስትል ከአንዳንድ ሰዎች ጋር ጓደኝነትን የመተው መሥዋዕትነት ትከፍል ይሆናል። እግዚአብሔርን ለማገልገል ወደ ሩቅ ስፍራ ለመሄድ ስትል ከቤተሰቦችህ ጋር ያለህን ኅብረት



ልታቋርጥ ትችል ይሆናል። ስሌሎች ለመመስከር ስትል ወይም ለቤተ ክርስቲያንህ ለመጸለይ ስትል ማልደህ በመነሣት የዕረፍት ጊዜህን ልትሠዋ ትችላለህ። አንድን ሰው ስለኀጢአቱ በማስጠንቀቅህ ከሰውዬው ጋር የነበረህን መልካም ግንኙነት ልታጣው ትችላለህ።

በእግዚአብሔር ዐይኖች ፊት መልካም የሆነውን ለማድረግ በመቆምህ ምክንያት የሥራ እድገትህን መሥዋዕት ታደርግ ይሆናል። የእግዚአብሔር ፈቃድ ለማድረግ ስትል የራስህን እቅድ መሥዋዕት ታደርግም ይሆናል። ከፍተኛ ደመወዝህን ከእግዚአብሔር ጥሪ የተነሣ ጥለህ በመውጣት መሥዋዕት ትከፍል ይሆናል። ለኢየሱስ ክርስቶስና ለመንግስቱ ቅድሚያ ለመስጠት ስትል መዝናናትንና ልታደርጋቸው የምትፈልጋቸውን ሌሎች ነገሮች በመተው መሥዋዕትነት ልትከፍልም ትችላለህ። እያንዳንዱ ምርጫህ ለመሥዋዕት የመልካም አጋጣሚን በር የሚከፍትልህ ሲሆን፣ የምታደርገው ምርጫም ሕይወትህን ለመመዘን የሚያገለግል ነው።

ሕይወትህን፣ እግዚአብሔርን ለማስደሰት ስትል ያለማቋረጥ ራስህን በመካድህ መዝነው። ሕይወትህን፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ስትል የራስህን ፈቃድ ምን ያህል ጠቅልለህ በመተውህ መዝነው። ሕይወትህን፣ ራስህን መሥዋዕት አድርገህ ባቀረብክ ጊዜ ራስህን በመካድህ በሚሰማህ ደስታ መጠን መዝነው። መሥዋዕትነት የሕይወትህ መለያ ሆኗልን? በእግዚአብሔር ፈቃድ ሥር መዋል ተለማምደሃልን? የእግዚአብሔርን ፍላጎት ከፍላጎትህ በፊት፣ የእግዚብሔርን ፈቃድ ከፈቃድህ በፊት ማስቀደምን ያለማቋረጥ ምርጫህ አድርገሃልን? በዚህ ምርጫህስ መላው

ሕይወትህ ለእግዚአብሔር ሕያው መሥዋዕት ሆኗልን? ይህ በእግዚአብሔር ዐይኖች ፊት የከበረ የሕይወትህ መመዘኛ ነው።

ሕይወትህን፣ በምታገኘው ልክ ሳይሆን በምትሰጠው ልክ መዝነው። ሕይወትህን እግዚአብሔርን አንደኛ፣ ሌሎችን ሁለተኛ፣ ራስህን ደግሞ የመጨረሻ ባደረክበት መጠን መዝነው። ሕይወትህን፣ የክርስቶስን መንግሥት አንደኛ አድርገህ ለማስቀደም መሥዋዕት በሆንክበት መጠን ልክ (ማቴ 6፥33)፣ ለክርስቶስም ብለህ መሥዋዕት በመሆንህ በሚሰማህ ደስታ መዝነው። ሕይወትህን መሥዋዕትነትን በመውደድህ መዝን።



## ምን ተጨማሪ ነገር ማድረግ ትችላለህ?

ለእግዚአብሔር እና ለነፍሳት ምን ተጨማሪ ነገር ማድረግ ትችላለህ? ምድራዊ በሆኑ ስጋዊ ዓላማዎችህ እንዳትደናቀፍ ተጠንቀቅ! ከፊሉን ብቻ ለእግዚአብሔር ሰጥተህ ቀሪውን ለራስህ አታድርግ፤ ያለህን ውድ ነገርና ሁለንተናህን ሁሉ ስጠው።

ወደጠፉት ልትደርስ ምን ተጨማሪ ነገር ማድረግ የምትችል ይመስልሃል? ዋጋ ከሚያስከፍልህ ነገር ወደ ኋላ ትሸሻለህን? ወደ ጠፋው ሰው ለመዝለቅ ምን ተጨማሪ ነገር ታደርጋለህ? ይህን ጥያቄ ደግመህ ደጋግመህ እግዚአብሔርን ጠይቀው!

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ምን ተጨማሪ ነገር ለማድረግ ትችላለህ? ዓላማው ይተገበር ዘንድ በሙሉ ኃይልህ ትንቀሳቀሳለህን? ለጥሪውስ ሙሉ ለሙሉ በመታዘዝ መልስ ትሰጣለህን? አ! ጌታ ፍጹም በሆነ መንገዱ ይምራህ!

በጸሎትህ ስለሌሎች ለመለመን ምን ተጨማሪ ነገር ማድረግ ትችላለህ? የሌሎችን ሸክም ለመሸከም ተጨማሪ ነገር ልትጫን አትችልምን? በእንባ እስክትጸልይ ድረስ ሌሎችን አብልጠህ መውደድ ያቅትሃልን? በሰማይ እስክትደመጥ ድረስ ትጸልያለህ፣ ትጾማለህ?

*መሥዋዕት ለመሆንስ ምን ተጨማሪ ነገር ማድረግ ትችላለህ? ለነፍሣት ዋጋ ለመክፈል ተጨማሪ የምትሰጠው ምን አለህ? የክርስቶስን መስቀል ለመሸከም ማድረግ የምትችለው ተጨማሪ ነገር ምንድን ነው?*

ኢየሱስ ለአንተ ያደረገልህ ተጨማሪ ነገር ምንድን ነው? ዐይኖችህን ወደ ሰማይ አቅና፤ ዓለም አዲስ አይታን ትሻለች። ከአዳኝህና ከእርሱ ታላቅ እቅድ ጋር እንዳትተላለፍ ተጠንቀቅ። ለእግዚአብሔርና ለሰዎች ምን ተጨማሪ ነገር ማድረግ ትችላለህ?

ዊስሌይ ዱዌል



# 18

# እግዚአብሔርን ባከበርከበት መጠን ሕይወትህን መዝን

ትልቁ የሕይወትህ ዓላማ እግዚአብሔርን ማክበርና ፈቃዱንም ማድረግ ሊሆን ይገባል። በሕይወትህ ውስጥ የሚከናወኑ ማናቸውም ነገሮች ተጨማሪ ክብር ለእግዚአብሔር ያመጡ ዘንድ ታቅደው ሊከናወኑ ይችላሉ። በሕይወት ምርጫዎችህ ሁሉ ውስጥ ሊሰመርበት የሚገባ መርሕ ሆኖ ሊቀመጥ የሚያስፈልገው፣ "ለእግዚአብሔር እጅግ በላጭ የሆነውን ክብር የሚያመጣው የትኛው ነው?" የሚለው ነው። በጥቅሉ የተመለከትነው እንደሆነ፣ ብዙ ነገሮች ከእግዚአብሔር ክብር ጋር የተያያዘ ጉዳይ ያላቸው አይመስሉም። ነገር ግን ሁሉ ጊዜም፣ ቢያንስ ቢያንስ በተዘዋዋሪ መንገድ ለእግዚአብሔር ክብርን ይጨምራሉ ወይም ክብሩን ያጎድላሉ።

የነፍስህ ትልቁ መሻት ሊሆን የሚችለው እግዚአብሔር ወይም እኔነት ነው። ምን ጊዜም ቢሆን ጥያቄው ቀዳሚው እግዚአብሔር ወይስ እኔ የሚለው ነው። ጉዳዩ "እግዚአብሔር እጅግ አብልጦ የሚሻው ነገር ምንድነው?" የሚለው እንጂ "እኔ የምሻው ወይም ለእኔ ጥቅም ያለው ምንድን ነው?" የሚለው አይደለም። በሕይወትህ ውስጥ እንቅስቃሴህን የሚመራ ገዥ አቋም የሌለ መስሎ ከተሰማህ፣ እኔነት በዙፋንህ ላይ ተቀምጧል። ነገር ግን መላውን የሕይወት እንቅስቃሴህን የሚመራ አቋምህ ለእግዚአብሔር በላጭ ክብርን ማምጣት ከሆነ፣ የሕይወትህ የትኛ

ውም ዘርፍ፣ ዕለታዊ ሕይወትህ ለእግዚአብሔር ክብርን ማምጣት የሚችል አቅም ያለው ይሆናል።

የእግዚአብሔር ክብር በማንኛውም ሕይወት ላይ ሥነ ምግባራዊ ግጼታን ያመጣል ነው። ለእግዚአብሔር እጅግ በላጭ የሆነውን ክብር የሚያመጣው የትኛው ነው? የሚለው ጥያቄ ያለማቋረጥ ራስህን ልትጠይቅ የሚገባህ ጥያቄ ነው። ራስህንና ልብሶችህን በንጽሕና መጠበቅ፣ የጸጉርህን አበጣጠር በወጉ ማድረግ፣ ቤትህንና መኪናህን በአግባቡ በመያዝ ንጹሕ፣ አስደሳችና ምቹ ማድረግ፣ እነኝህ ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር መደረግ የሚገባቸው ናቸው።

ለእግዚአብሔር ተጨማሪ ክብር የሚያመጡ በርካታ መንገዶች አሉ። እነዚህ፣ መጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ መርሕ ይሆኑህ ዘንድ የገለጸልህ የታወቁ መንገዶች ብቻ ሳይሆኑ፣ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ለእግዚአብሔር ክብር ታመጣ ዘንድ በየዕለቱ የሚሰጥህ መመሪያዎች ጭምር ናቸው። ለእግዚአብሔር ክብር ታመጣ ዘንድ ሁልጊዜም በጉባኤ ወይም በሕዝብ መካከል ልትሆን የግድ አያስፈልግህም። በሁለንተናዊ መሰጠት ለጌታ ክብርን በማምጣት በቤትህና በቤተሰቦችህ፣ በሥራ ቦታህና በሥራ ባልደረቦችህ፣ በቤተ ክርስቲያንህ ወይም በምትኖርበት ማህበረሰብ መካከል፤ ምሳሌያዊ ተጽእኖ ማሳደር ትችላለህ። በመላው ማንነትህና በምትሠራው ነገር ሁሉ ሊንጸባረቅ ይችላል።

ኤርል ሬኒይ በሚዙሪ ግዛት በምትገኘው በትሮይ ውስጥ በሚገኝ አንድ ዋና የሸቀጣሸቀጥ መሸጫ ሱቅ ውስጥ በገንዘብ ተቀባይነት የሚያገለግል ሰው ነበር። በመንፈስ ቅዱስ የተሞላው የዚህ ወጣት ሰው ሕይወት ለሰዎች ሁሉ ደስተኛና ፈገግታ



የማይለየው ገጽታ እንዲኖረው አስችሎታል። ሁልጊዜም ወንድማዊ የሆነ አቀራረብና ትብብርን ለማድረግ ዝግጁ ነበር። የሞተው ገና በወጣትነቱ ሲሆን የሚሠራበት የንግድ ድርጅት በአንድ የከተማቸው ጋዜጣ ላይ የሚከተለውን ትልቅ ማስታወሻ (ማስታወቂያ) አሳተመ። በጽሑፉ አናት ላይ በጉልህ እንዲህ የሚል ቃል ሰፍሯል፤ "ኤርል ሬኒይ ወደ መንግስተ ሰማይ ሄደ" ከዚያም ጽሑፉ እንዲህ በማለት ይቀጥላል፤ "መንግስተ ሰማይ መግባቱን እንዴት እንዳወቅን ትጠይቁ ይሆናል። ለእኛ የሚሠራ ሰው ነበር። በ __________ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤዎችን ሲካፈል የነበረ ከመሆኑም በላይ ጌታን እንደተቀበለ ተናግሯል። የምናውቀው ነገር ቢኖር . . ." በማለት ወጣቱ ምን ዐይነት ውብ ሕይወት እንደኖረ ዘግበዋል። ኤርል ሬኒይ የኖረው ለእግዚአብሔር ክብር ነበር።

የጆን ኒውተን እናት የሆኑት መልካሚቱ መበለት የዕለት ምግባቸውን ለማዘጋጀት የሚያስፈልጋቸውን ገንዘብ ለማግኘት ለእግዚአብሔር ክብር ልብሶችን ያጥቡ ነበር። ጆን የአባቱን ፈለግ ተከትሎ መርከበኛ ለመሆን ወደ ባሕር ቢሄድም ችግሩ ግን እየከፋ ሄደ። ከአንድ መርከብ ወደ ሌላው መርከብ ተዘዋወረ፤ በመጨረሻውም በአፍሪካ የባሕር ዳርቻ ለምትኖር አንዲት ጥቁር ወይዘሮ በባርነት ተሸጠ። ምግቡም ከሴትዮዋ ገበታ የሚተራረፍ ምግብና ሌሊት ሌሊት እየሰረቀ የሚመገበው ፍራፍሬ ሆነ። የነበረው ንብረትም አንድ ሸሚዝ ብቻ ነበር። ከዚያም ከባርነት አምልጦ እንደገና ወደ ባህሩ ተመለሰና ባሪያ ፈንጋይና ባሪያ ነጋዴ ሆነ።

በዚህ ሁሉ ጊዜ ውስጥ እናቱ ልብስ ማጠቧን ቀጥላለች። እግዚአብሔር የባዘነውን ልጇን እንዲያድንላት በየሰዓቱ ስትጸልይ እንባዋ በጉንጮቿ እየወረደ ከምታጥብበት ውሃ ጋር ይደባለቃል።

ከዓመት ዓመት ይሄው ጸሎቷ ቀጠለ። በመጨረሻውም ጌታን ተቀበለና ለንደን ከተማ ውስጥ እጅግ የተወደደና የታወቀ አገልጋይ ለመሆን በቃ። ዛሬ መላው የክርስቲያኑ ዓለም የሚዘምረው በግል የሕይወት ታሪክ ላይ የተመሰረተው "አስደናቂ ጸጋ፣ እንዴት መልካም ቢሆን ነው እንደ እኔ ያለውን ምናምንቴ ሰው ያዳነው" የሚለውን መዝሙር የዘመረው እርሱ ነው። እኚህ ትሁትና ስማቸው እንኳን ያልታወቀ የኒውተን እናት፤ ለእግዚአብሔር ክብር ከኖሩት ሕይወት የበለጠ እስከዛሬም ድረስ የትኛውም ክርስቲያናዊ መሪ አልኖረም። በመንግስተ ሰማይ ትልቁን ሽልማት የሚያገኘው ማነው፤ ጆን ኒውተን ወይስ እናቱ? ማንም ሰው ቢሆን ለእግዚአብሔር ክብር መኖር ይችላል። አንተም ትችላለህ።

ኢየሱስ በነፍሱ ውስጥ ይቃጠል የነበረውን መሻት፣ "አባት ሆይ ስምህን አክብረው!" (ዮሐ 12፥28) በማለት ገልጾታል። ኢየሱስ ይህንን ጸሎት የጸለየው መቼ ነበር? የስንዴ ዘር በምድር ላይ ካልወደቀችና ካልሞተች ፍሬ ልታፈራ እንደማትችል፣ ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ እንደምታፈራ በምሳሌ ካስተማረ በኋላ ነበር። ነፍሱን የሚወድ ሰው እንደሚያጠፋት፣ ነፍሱን በዚህ ዓለም የሚጠላት ሰው ግን እንደሚያገኛት የተናገረበትም ቅጽበት ናት። ጨምሮም እንዲህ አለ፤ "የሚያገለግለኝ ቢኖር ይከተለኝ"። ከዚያ በኋላ ደግሞ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይፈጽም ዘንድ በፊቱ ያለው በግል



የሚከፍለው ታላቅ ዋጋ ትውስ አለውና እንዲህ አለ፤ "አሁን ነፍሴ ታውካለች፤ እንግዲህ ምን እላለሁ? 'አባት ሆይ ከዚች የጭንቅ ሰዓት አድነኝ። ስለዚች ሰዓት ወደዚህ ምድር መጥቻለሁና"። ከዚያም "አባት ሆይ ስምህን አክብረው" ሲል ጮኸ፤ ወዲያውኑ እግዚአብሔር ጸሎቱን መለሰ፤ "አከበርሁት ደግሞም አከብረዋለሁ!"

ኢየሱስ ክርስቶስን በመከተል በምትታዘዘው መታዘዝ ውስጥ እግዚአብሔር ስሙን ያከብራል። ወደ ምድር ወድቃ፣ የምትሞተውንና እጅግ ብዙ ፍሬ የምታፈራውን ዘር ለመሆን ፈቃደኛ በመሆንህ እግዚአብሔር ስሙን በዚህ ያከብራል (ዮሐ 12፥23-24)። የእግዚአብሔር ፈቃድ ተከናውኖ ይታይ ዘንድ መከፈል የሚገባውን ዋጋ ሁሉ ለመክፈል ባለህ ፈቃደኝነት ስሙን ያከብራል። ሕይወትህን እንዲህ ባለው መልካም ዝንባሌህ፤ ለኢየሱስ ክርስቶስ ስትል ዋጋ ለመክፈልና በማንኛውም ነገር የእግዚአብሔርን ክብር ለማስቀደም ባለህ ፈቃደኝነት መዝን።

እግዚአብሔርን ለማክበር ብዙ እድሎች ስለነበሩህ ብቻ እግዚአብሔር ሽልማትን አይሰጥህም፤ ነገር ግን ባገኘሃቸው አጋጣሚዎች ተጠቅመህ ማድረግ የምትችለውን ሁሉ ስታደርግ ያን ጊዜ ለሽልማቶቹ ትበቃለህ። እግዚአብሔር ሰፊ እድል ሰጥቶህ ከሆነ ከአንተ የሚጠብቅውም ነገር ይሆናል (ሉቃ 12፥48)። ያገኘሃቸውን መልካም አጋጣሚዎች ተጠቀምባቸው፤ ያን ጊዜ እግዚአብሔር ለበለጠ ነገር ያምንሃል (ሉቃ 19፥24-26)።

አንድ ክርስቲያን አገልጋይ አሁን በምንነጋገርበት ሙሉ ለሙሉ ራስን ለእግዚአብሔር መስጠትና የተቀደሰ ኑሮን መኖር ስለሚቻልበት ሁኔታ ንግግር ያደርግ ነበር። ሁሉም ሰው እንደ

መጽሐፍ ቅዱስ ቃል ቢኖር በቤት ውስጥ ሊኖር የሚችለውን የተቀደሰ ሕይወት የሚያሳይ አንድ ሥዕል ሳለ፡፡ ንግግሩንም ሲጨርስ እዚያ ለነበሩ ሰዎች ይህን ለእግዚአብሔር መለጠት ሙሉ ለሙሉ ተቀብለው በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ይፈልጉ እንደሆነ ጠየቀ፡፡ በጉባኤው መካከል የነበረች አንዲት ሴት አጠገቧ ወደነበረች ሌላ ሴት ዞወር ብላ፣ "እንዴት ያለ አስደናቂ ስብከት ነው፤ ነገር ግን እንዲህ ዐይነቱን ሕይወት በእውነት መኖር ከታቻለ እገረማለሁ" አለች፡፡ ሌላኛዋም ሴት አንገቷን ቀለስ አድርጋ ፈገግ አለችና፤ "ሰባኪው እንዲህ ዐይነቱን ኑሮ እንደሚኖር አውቃለሁ" አለች፡፡ "እኔ ሚስቱ ነኝ!፡፡"

በሙሉ ልብህና በሙሉ ነፍስህ የሕይወትህን ትኩረት በእግዚአብሔር ላይ ብታደርግ የተለመዱና ተራ የሚባሉ የሕይወት ልምምዶችህ እንኳን ለእግዚአብሔር ክብር ሊደረጉ ይችላሉ፡፡ በአግባቡ መመገብህ፣ ለጤናህ ተስማሚ በሆነ ሁኔታ መጠጣትህ፣ በቂ እንቅልፍ ማግኘትህና በታማኝነት የሰውነት እንቅስቃሴዎችን ማድረግህ እንኳን ለእግዚአብሔር ክብር ሊደረጉ ይችላሉ (1ቆሮ 10፥31)፡፡ ብዙዎች ሰውነታቸው የእነርሱ የራሳቸው እንዳልሆነ ረስተውታል፡፡ ከረዥም ጊዜ በፊት ታማኝ ለሆነ አገልግሎት ለእግዚአብሔር አደራ ሰጥተውታል፡፡ አካላችን መልካም በሆነ ጤንነት ላይ መገኘት ይችል ዘንድ እግዚአብሔር አስፈላጊውን ሁሉ ሊያደርግለት አደራ አሰበት፡፡ በሰውነታችን እግዚአብሔርን እንድናከብር ታዘናል (1ቆሮ 6፥20)፡፡

ሕይወትህን፣ በአንተ ምክንያት ወደ ሌሎች ሰዎች ልብ ውስጥ በፈሰሰው ምስጋና መዝን (2ቆሮ 4፥15)፡፡ ከሕይወትህ



እየመነጨ ያሰማቋረጥ ወደ እግዚአብሔር እና ወደ ሌሎች እንዲፈስ መንፈስ ቅዱስ የሚፈልገው ምስጋና ለእግዚአብሔር አክብሮትንና ክብርን ሊያመጣ የሚችል ነው፡፡ በሚፍለቀለቅ ሀሴትና ውዳሴ በምስጋና የተሞላ ልብ፣ ለእግዚአብሔር መልካምነትና ታማኝነት ሕያው ምስክር ሊያመጣ ይችላል፡፡

ገና የስድስት ሳምንት ሕፃን ሳለች የዐይኖቿን ብርሃን ያጣችው ፋኒ ክሮስቢ፣ በሄደችበት ስፍራ ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብርን የምታመጣ ነች፡፡ ከልጃገረድነቷ ጊዜ ጀምሮ ከሌሎች መጻሕፍት ይልቅ መጽሐፍ ቅዱስን አጣርታ ታውቅ ነበረ፡፡ በዚህ የዕድሜ ክልል ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስን የመጀመሪያዎቹን አምስት መጻሕፍት፣ መጽሐፈ ሩትን፣ ብዙዎቹን የመዝሙር ዳዊትንና የመጽሐፉ ምሳሌ ምዕራፎች፣ መኀልየ መኀልይ ዘሰሎሞንና ከሞላ ጐደል ሁሉንም የአዲስ ኪዳንን መጻሕፍት ማለት ይቻላል በአእምሮዋ እያስታወሰች በቃሏ ትደግማቸው ነበር፡፡

ዐይነስውሯ ፋኒ የእግዚአብሔርን መልካምነት በሁሉ ነገር ውስጥ ትረዳለች በምትደሰላቸው አበቦች፣ ዛፎችና ሣሮች፣ በምታደምጣቸው የአእዋፍ ዝማሬዎች፣ ኩልል ብለው በሚወርዱ የውሃ ምንጮች ድምጽ ሁሉ ውስጥ ይሄ መረዳት አላት፡፡ በምትጽፋቸው ግጥሟቿ ውስጥም ሁሉንም ገልጻቸዋለች፡፡

ዐይነስውርነት ሕይወቷን እንዲያጨልም ወይም አጉረምራሚ እንዲያደርጋት ላትፈቅድለት ራሷን አዘጋጅታ ነበር፡፡ ደስተኛ የሆነ ልብ ነበራት፤ በደረሰችበት ስፍራ ሁሉ ይህን እንደ ፀሐይ ብርሃን ትረጨው ስለነበር እግዚአብሔር ይከብርበት ነበር፡፡ ምንም ነገር ቢሆን እንዲረብሻት፣ እንዲያናድዳትና እንዲበጠብጣት አትፈቅድም፤ ትቃወመዋለችም፡፡ ፋኒ በሄደችበት በየትኛውም ቤት

የሞቀ አቀባበል የሚጠብቃት ሴት ነበረች። ለእግዚአብሔር ክብር የጻፈቻቸውን ስምንት ሺህ የሚያህሉ ቅኔዎች ታስታውሳቸዋለች። እንዲህ የተባረከች ስለነበረች በብዙ ታላላቅ ጉባኤዎች ላይ ንግግር እንድታደርግ ትጋበዛለች። የካቲት 11 ቀን 1915 በ94 ዓመት ዕድሜዋ ሙሉ ጤነኛ ሴት ትመስል ነበር። በዚያ ምሽት በቃሏ እየተናገረች ደብዳቤ እና አዲስ ግጥምም ከጻፈች በኋላ ወደ አልጋዋ ሄደች። ሌሊቱ ከመንጋቱ በፊት ግን ወደ መንግስተ ሰማይ በሰላም ሄዳለች።

ፋኒ ክሮስቢ የጻፈቻቸውን፤ "የተባረከ ዋስትና"፣ "በጸጋ ድነናል"፣ "በኢየሱስ ክንዶች ላይ ማረፍ"፣ "ክብሩ ለእግዚአብሔር ይሁን"፣ "የኢየሱስን ታሪክ ንገሩኝ" የሚሉትንና እጅግ ብዙ ብዙ ዝማሬዎቿን በመዘመር ከእርሷ ጋር እግዚአብሔርን ለማክበር ያልተባበረ ክርስቲያን ማን ነው? "ከመጥፋት ድኛለሁ"፣ "ትሁቱ አዳኝ ሆይ አትለፈኝ"፣ "ኢየሱስ በፍቅር ድምፅ ይጠራሃል" የሚሉትን ግጥሞቿን በመስማት ሕይወታቸውን ፈጽመው ለኢየሱስ ያስረከቡ ምን ያህል ሺህ ሰዎች ይኖሩ ይሆን? ምናልባትም በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች፣ "ተስፋ አትቁረጥ"፣ "ነፍሴን ለውሯታል"፣ "በመንገዶ ሁሉ አዳኜ ይመራኛል"፣ "በመስቀሉ አጠገብ"፣ "ወዳንተ ሣበኝ" እና "እመስግኑት እመስግኑት" የሚሉ ዝማሬዎቹን በመዘመር የሕይወት ምስክርነቷን ተጋርተዋል። ዐይነስውሪቷ ፋኒ ክሮስቢ ለእግዚአብሔር ባመጣችው ክብር ምክንያት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ነፍሳት ታንጸዋል።

ሕይወትህን፣ ያለ ማቋረጥ ከሌሎች ጋር ስለሌሎች የጸለይኸቸውን ጸሎቶች መልስ በመቀበልህ መዝን። ያለማቋረጥ



የሌሎችን ሸክም እንሸከም ዘንድ የተገባ ነው (ገላ 6፥2)። የጸሎት መልሶች ለእግዚአብሔር ክብርን ያመጣሉ (መዝ 50፥15)። የእግዚአብሔርን ታላቅነት፣ ሉዐላዊነት፣ ኃያልነት፣ ጥበብና ፍቅሩን ይመሰክራሉ። እግዚአብሔር ሕያው እንደሆነ፣ በዙፋኑ ላይ እንዳለ፣ ፍቅር እንደሆነ፣ ሕይወታችንን እትኩሮ እንደሚመለከት ለዓለሙ ሁሉ ይመሰክራሉ። አ! በጸሎት መልሶች ለእግዚአብሔር ማምጣት የሚቻለው ክብር ምንኛ ታላቅ ነው! ይህም ለሕይወትህ የሚከፍተው አቅጣጫ ሰፊ ነው! ከእግዚብሔር ጋር አብረህ መሥራት እንድትችልም ጸሎት ያመቻችልሃል። ለሕይወትህም ዘላለማዊውን ትርጉም ይጨምርልሃል። የዕለት ተዕለት ተግባርህን እያከናወንክ ምልጃ ጸሎትህን ወደ እግዚአብሔር ማቅረብና ለኢየሱስ በግል ያለህን ፍቅር ልትገልጽ ትችላለህ። ለእግዚአብሔር ክብርን ከማምጣት የተሻለ ለአንተ ሌላ ምን መንገድ አለ?

ሕይወትህን፣ ለእግዚአብሔር ክብርን በሚያመጡ መልካም ሥራዎችህ መዝን። በመልካም ተግባራትህ ለእግዚአብሔር ክብርን ለማምጣት ታመነታ ይሆናል። ነገር ግን እነዚህ ለእግዚአብሔር ክብርን ለማምጣት የሚያስችል ታላቅ ችሎታ አላቸው። ኢየሱስ ይህን ያረጋግጥልናል፤ "መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ" (ማቴ 5፥16)። ጴጥሮስም እንዲህ ሲል ይመክረናል፤ "ስለሚመለከቱት ስለ መልካም ሥራችሁ . . . እግዚአብሔርን ያከብሩት ዘንድ በአሕዛብ መካከል ኑሯችሁ መልካም ይሁን" (1ጴጥ 2፥12)።

ይህ አንድ ጠቃሚ የሆነ እውነት ይጠቁመናል:: የምትጸልያቸው ጸሎቶች፣ ወደ ሌሎች ሕይወት የምታመጣው በረከትና የሕይወትህ ምስክርነቶች ወዲያውኑ በአደባባይ ለእግዚአብሔር ክብር ላያመጡ ይችላሉ:: ነገር ግን እነኚህ ሁሉ ነገሮች እፍ አውጥተው በተቃወሙህ ሰዎች ልብና አእምሮ ሳይቀር ተመዝግበው የሚቀመጡ ናቸው:: ልክ ሐዋርያው ጳውሎስ፣ እስጢፋኖስ በድንጋይ እየተወገረ ሳለ የሚያበራ ፊቱንና የይቅርታ መንፈሱን ሲመለከት፣ ይህ ድርጊት እንዲፈጸም ቀስቃሽ በመሆኑ ምክንያት ከህሊናው ወቀሳ ሊያመልጥ እንዳልቻለ ሁሉ ማለት ነው (ሐዋ 7፥59-60፤ 1ቆሮ 15፥9):: የተቃወሙህ ያልዳኑ ሰዎች ፈጥኖም ሆነ ዘግይቶ ከፍርድ ቀን በፊት ላይሆን ቢችል እንኳን በፍርድ ቀን፣ በታማኝነትህ ያሳደርክባቸውን ተጽእኖና ለእግዚአብሔር ያመጣኸውን ክብር ይናዘዛሉ:: ሕይወትህን በመልካም ሥራህና ለሌሎች ሕይወት ባመጣኸው ባርከት መዝን::

አንተ የተፈጠርከው ለእግዚአብሔር ክብርን ታመጣ ዘንድ ነው (ኢሳ 43፥7):: መንፈስ ቅዱስ በአንተ ውስጥ ይኖራል፣ ሞልቶሃል፤ ኃይልን አልብሶሃል፤ አትሞሃልም፤ በዚህም ምክንያት በአንተ ዘንድ ያለው ህልውናው ለእግዚአብሔር ታላቅ ክብርን እንድታመጣ ያስችልሃል (ኤፌ 1፥13-15):: የመንፈስ ቅዱስ ሐሣብ አንተ ለእግዚአብሔር የማያቋርጥ ክብር እንድትሆን ነው:: የእግዚአብሔር ብቸኛ ንብረት ሆነህ የታተምክ ስለሆነ አስገራሚ በሆነ ሁኔታ ከዓለም የተለየህ እንድትሆን ይፈልጋል:: ያልዳኑት ሰዎች በአንተ ላይ ያረፈውን የእግዚአብሔር ይሁንታ መረዳት ችለው ይሆን? የእግዚአብሔርን የፍቅር ማህተምስ ለማስተዋል በቅተዋልን?



ሕይወትህን፣ ለእግዚአብሔር ክብር ያመጣ ዘንድ በባሕርይህ በሚገለጠው መንፈሳዊ ፍሬ መዝን:: ኢየሱስን እንድትመስል የሚያደርጉ ፍሬዎች እነዚህ ናቸው (ፊልጵ 1፥11):: እዚህ ላይ የቲ.ኤም. ጆንስን ዝማሬ አብረን መዘመር እንወዳለን:-

ይታይ በእኔ የኢየሱስ ውበቱ
ንጽህናው የሚቀጣጠል ስሜቱ
ቁንጅናው በእኔ ሕይወት እንዲያበራ
አ! መንፈስ ቅዱስ ባሕርዬን አንተው አጥራ::

ሕይወትህን፣ ጌታ ክርስቶስ ኢየሱስን በለበስክበት መጠን መዝነው (ሮሜ 13፥14):: ከኢየሱስ ጋር ተጠጋግተህ መራመድ በቀጠልክ ልክ፣ መላው ማንነትህ በመንፈሱ ይሞላል፤ እናም ይበልጥ ክርስቶስን ወደመምሰል እየተጠጋህ ትመጣለህ:: ጳውሎስ እንዲህ ሲል ይመክረናል፤ "ምሕረትን ፣ ርኅራኄን፣ ቸርነትን፣ ትህትናን፣ የዋህነትንና ትዕግሥትን ልበሱ" (ቆላ 3፥12):: እንደ ክርስቶስ ያለ ርኅራኄ፣ እንደ ክርስቶስ ያለ ቸርነት፣ እንደ ክርስቶስ ያለ ትህትና፣ እንደ ክርስቶስ ያለ የዋህነትና ትዕግሥት ታላቅ ክብርን ለእግዚአብሔር የሚያመጡ የተቀደሱ መንገዶች ናቸው::

እነዚህም ብቃቶች ናቸው የኢየሱስ ክርስቶስ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ለእግዚአብሔር ታላቅ ክብርን እንዲያመጣ የሚያስችሏት (ኤፌ 3፥21):: በክርስቲያኖች ሁሉ ዘንድ እነዚህ ጠንካራ የሕይወት ብቃቶች ሲገለጡ፣ ቤተ ክርስቲያን ጉልበታም ትሆናለች፤ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚመስሉ ሰዎችም በጋራ የሚያሳዩት የሕይወት ምስክርነት በሚኖሩበት ማኅበረሰብ መካከል በየግላቸው ለሚያደርጉት ምስክርነት ክብደትና ውጤታማ ተጽዕኖ ያሳድራል::

እያንዳንዱ ክርስቲያን እግዚአብሔርን በምታከብር አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ንቁ ተሳታፊ ሊሆን ከሚያስፈልግባቸው ምክንያቶች አንዱ ይህ ነው። ሕይወትህን፣ በአማኞች ኅብረት መካከል ባለህ የግል ተሳትፎ፣ እንደ ቡድን የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንህ ባላት መልካም ምስክርነት ላይ በጨመርከው አስተዋጽኦህ መዝን።

ቅድስና የተሞላው ባሕርይህ፣ ጠባይህ፣ ለሌሎች የምታሳየው ትዕግሥትህ፣ ክርስቶስ ሌሎችን ይቅር እንዳለ ለሌሎች የምትሰጠው ይቅርታ፤ ሌሎች ስምህን ባጠፉ፣ በተቃወሙህ፣ አንተንና ክርስቶስን የሚቃወሙ ባሳደዱህ ጊዜ ሥጋዊ መልስ ባለመስጠት የምታሰየው የሕይወት ምስክርነት የተለየ ክብርን ለእግዚአብሔር ያመጣል።

እንዲህ ባለ ጊዜ፣ "ስለ ክርስቶስ ስም ብትነቀፉ፣ የክብር መንፈስ የእግዚአብሔርም መንፈስ በእናንተ ላይ ያርፋልና ብፁዓን ናችሁ" (1ጴጥ 4፥14) የሚለው ቃል በሕይወታችን ይፈጸማል። በሚያጋጥምህ ጥላቻ፣ ስም ማጥፋት፣ ተቃውሞና ኢፍትሐዊነት መካከል እግዚአብሔር ሲባርክህ የእርሱ ውበቱ በአንተ ላይ ይታያል። እናም ብርሃንህ ከሌላው ጊዜ ይልቅ እብዝቶ የሚያንጸባርቅና ሩቅ ስፍራ ድረስ የሚያታይ ይሆናል። አዎን ቀድሞ ከሆነው ይልቅ የእግዚብሔር ክብር በአንተ ይገለጣል፣ በአንተም ውስጥ ዐልፎ ለሌሎች ሁሉ ይታያል። ያን ጊዜም የእግዚአብሔር ክብር ከአንተ ላይ እየተነሣ ሌሎች ሁሉ እንዲያዩት ከፍ ብሎ ይገለጣል (ኢሳ 60፥2)።

ሕይወትህን፤ የሕይወት ጫና ከየአቅጣጫው በቀጠቀጠህ ጊዜ ለእግዚአብሔር ባመጣኸው ክብር መዝነው። ሕይወትህን፣ በሥራ በተጨናነቅህ፣ ጤና በጎደለህ፣ ነገሮች ሁሉ ያልተሳኩልህ



በመሰለህ፣ በፈተና በተናወጥክና የማያቋርጥ ችግር ባጋጠመህ ጊዜ ክርስቶስን በመሰልከበት ሁኔታ መዝነው። እንደዚህ ባሉት ጊዜያት ነው እግዚአብሔር መንፈሳዊነትህ ከፊት ይልቅ ክርስቶስንም የሚመስል እንዲሆን የሚፈልገው። እንዲህ ባሉ ሁኔታዎች ውስጥ ነው ትዕግሥትንና ጽኑ እምነትን እንድትሰብስ የሚፈልገው። በዚህ ጊዜ ውስጥም ነው እግዚአብሔር በምስጋና የዝማሬ ዜማ እንድታከብረው የሚሻው። እንዲህ በሆነ ጊዜ፤ ዓለም ዝማሬህን ከሰማች፣ ኢየሱስን መምሰልህን ከተመለከተች መንፈሳዊ ሕይወትህ ከእግዚአብሔር የመነጨ መሆኑን ትገነዘባለች።

## ለክርስቶስ ክብር አምጣ

ለእግዚአብሔር ልጅ ክብር አምጣ፤ እርሱ ሁለንተናውን ለአንተ ሰጥቷል። እስከ ምድር ጫፍ ያሉትን ሰዎች ሁሉ በመርዳት ኢየሱስ ክርስቶስን በአዲስ እይታ ተመልከተው። በእንደበትህ ቃላት ከፍ ከፍ አድርገው፤ ከዚህ በላይ ታደርግ ዘንድ ግን ይጠበቅብሃል። ፈልገህ ያገኘኸውን ያህል ግለጠው፤ ለፍጥረት ሁሉ ደስታ ይሁን።

ሌሎችን በመውደድ በተገለጠ ፍቅርህ፣ ለፍቅር ልጅ ክብርን አምጣ። ሰዎች በዙፋኑ ላይ የተቀመጠውን ሊያዩት ባይችሉም፣ ወዳጄ ሆይ የአንተን ሕይወት ግን ያውቃሉ። የክርስቶስ ርኅራኄ፣ ትህትናና ምሕረት ሕይወትህን ያጥለቅልቃት። የእርሱ ራስን አሳልፎ የመስጠት ጸጋ በአንተ አልፎ ጥላቻንና ምሬትን ሁሉ ይፈውስ።

በነፍስህ መረጋጋት፤ ለነገሥታት ንጉሥ ክብርን አምጣ። ድነትን ያስገኘልህን ጸጋ ግለጠው፤ በእርሱ ቁጥጥር ውስጥ ሆነህ እያንዳንዱን ሐሣብ አብራው። የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆንክ ልብ በል፤ እናም ደስታ የተሞላውን ሕይወት በዚህ ኑር። የፍርሃትና የጥርጥር ባሪያ ሆነህ በቀላሉ የምትንገላታና የምትደክም ልትሆን ከቶውን አይገባህም።



የከበረ ሕይወቱን በመኖር፣ እሁን ለኢየሱስ ክርስቶስ ስም ክብርን አምጣ። የምታደርገው ሁሉ ስሙን ያግንን፣ ከምድር ጫፍ እስከ ምድር ጫፍ ክብር ይጨምር። በእያንዳንዱ ቀን የምታደርገው ሁሉ፣ የምትወደውን ኢየሱስን የሚያከብር ይሁን። ማለቂያ በሌለው ምስጋና እግዚአብሔርን የሚያከብር ከሰማይ መላእክት ጋር እምላኩን የሚያከብር ነው።

ዊስሌይ ዱዌል

# 19
# ባለፍክበት የመስቀሉ መንገድ ህይወትህን መዝን

ምናልባትም እስከ አሁን ድረስ ባለፍክበት የመስቀሉ መንገድ ሕይወትህን መዝነህ አታውቅ ይሆናል። እንዲህ ስላለው ቃል ጥቂትም ቢሆን ግንዛቤ የሚኖረው ክርስቲያን ብቻ ነው። በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ክርስቲያን ብቻ የመስቀሉ ሕይወት የሚያመጣውን ሙሉ ክብር ያያል፤ በዚህ ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ልምምድም መንፈሳዊ እውነታውን በመረዳት ደስ ይሰኛል።

ኢየሱስ ክርስቶስ በስቅለቱ፣ በትንሣኤው፣ በእርገቱና በአባቱ ዘንድ በክብር በመቀመጡ ለእኛ ባደረገልን ተጨባጭ እውነት ላይ ተመሥርተን፣ እግባብ ባለው እምነታችን መንገዱን ልንከተል የተገባ ነው። እርሱ ለእኛ ያደረገልንን እኛ ደግሞ በተቀደሰ እውነታ በመንፈስ ልንለማመደው ያስፈልጋል። የክርስቶስ ሞት በእምነት የእኔ ሞት ሆኗል። መንፈሳዊ በሆነው እይታ፣ ክርስቶስ በእኔ ምትክ እስቃቂ በሆነ መንገድ ሲሞት እኔም በእምነት ከእርሱ ጋር ሞቻለሁ።

"ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ" (ይህ ኀላፊ ጊዜን የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ፣ በመስቀሉ ተሠርቶ የተጠናቀቀው ድርጊት በእኔ ሕይወት ላይ ዘላቂ የሆነ ውጤት እንዳለው ያመለክታል)። እኔም አሁን ሆኖም ከክርስቶስ ጋር ተነሥቻለሁ፤ ስለዚህ በክርስቶስ ውስጥ አዲስን ሕይወት በእምነት እየኖርኩ ነው (ገላ 2፥20)።

ኢየሱስ ለአንተ ያደረገውን ነገር መንፈስ ቅዱስ በአንተ ሕይወት እውን ሊያደርገው ይፈልጋል። ሙሉ የሆነው የመስቀሉ ሥራ ውጤት ለሰላምንና እርቅን (ቆላ 1፥20፣ 22)፣ የቀደመው



የኀጢአት ባሕርይህ መስቀሉን (ገላ 5፥24) እና ዓለም ለአንተ አንተም ለዓለም መስቀልህን የሚያካትት ነው።

ያ ሕይወትም፤ ለኀጢአት፣ ለእኔነት፣ ለዓለም ነገር የሞተ፤ ለሥላሴ - ለአብ፣ ወልድና ለመንፈስ ቅዱስ - እጅግ ሕያው የሆነ፣ በእግዚአብሔር ዐይኖች ፊትም ታላቅ የሆነ ሕይወት ነው። ቤተ ክርስቲያን በአስገራሚ ሁኔታ መንፈሳዊ ለሆነው ነገር በሞቱ፣ በአስገራሚ ሁኔታም ለእኔነታቸውና ለዓለም ሕያዋን በሆኑ ብዙ ሥጋውያን ክርስቲያኖች ተሞልታለች። ለእነርሱ የመስቀሉ ሕይወት መንገድ በጣም ጥቂት ፋይዳ ነው ያለው።

ለውጤታማና እውነተኛ መንፈሳዊ የክርስትና ሕይወት ታላቅ ተገዳዳሪ ጠላት የሆነው ሥጋዊ የሆነ የእኔነት ሕይወት ነው። በእኔነት የተሞላ ክርስቲያን በመንፈስ የተሞላ ክርስቲያን ተቃራኒ ነው። በመንፈስ መሞላት የመንፈሳዊ ሕይወት ስኬትና እድገት ሚስጥር ነው። በእኔነት መሞላት ደግሞ የመንፈሳዊ ሕይወት ውድቀት ምክንያት ነው። የእኔነት ሕይወት ወደ መስቀሉ ወጥቶ እስካልተሰቀለ ድረስ በመንፈሳዊው ሕይወት እድገት ብሎ ነገር አይታሰብም። ክርስቲያኖች፣ "ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ" የሚለውን የጳውሎስን ቃል በግል የሕይወት ልምምዳቸው እስካልተረዱት ድረስ፣ " እኔም አሁ ን ሕያው ሆኜ አልኖርም፤ ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል" የሚለውን እውነታ ሊያውቁት አይችሉም (ገላ 2፥20)።

በእኔነት የተሞላ ሕይወት በጭራሽ በእግዚአብሔር የተሞላ ሕይወት አይደለም። ከኀጢአትና ከእኔነት ነጻ እስክትሆን ድረስ የእግዚአብሔር መንፈስ አይሞላህም፤ ሊሞላህም አይችልም። ብዙ

ሰዎች ዓለማዊ በሆነው ነገርና በግል ብቃት ትምክህትም እጅግ አብዝተው ተሞልተዋልና ለእግዚአብሔር ብዙም አይጠቀሙም።

እግዚአብሔር የሚሠራው፣ ከክርስቶስ ጋር በተሰቀሉትና በመንፈስ በተሞሉት ነው። ዶ/ር ኢውግን ኧርኒን፣ የኢ.ኤም.ኤስ ዓለም አቀፍ ፕሬዝዳንት የነበሩትን ወ/ሮ ቻርልስ ክውማንን እ.ኤ.አ በ1949 በመተካት በፕሬዝዳንትነት ያገለገሉ ሲሆን፣ እኚህን ሰው ላለፉት አርባ ስድስት ዓመታት አውቃቸዋለሁ፤ አብሬያቸውም ሠርቻለሁ። በሀሩር ንዳድ፣ ጭንቀት በሞላበት የሕንድ ምድር ድርጅቱን ስንመሠርት ከሰይጣን ታላቅ ተግዳሮት በደረሰብን ጊዜ ሁሉ እጅ ለእጅ ተያይዘን አብረን ሠርተናል። እኚህን ሰው በጤንነታቸውና በህመማቸው፣ በሥራ መሪነት እያሉና ጡረታ ከወጡ በኋላም አውቃቸዋለሁ። ባልተለመደ ሁኔታ በመንፈስ ቅዱስ የሚመሩ፣ በመንፈስ የተቀቡ፣ የውሳኔ ሰውና በአመራራቸው ወደር የማይገኝላቸው ናቸው። ከዚህ ሁሉ በላይም በእውነት ከክርስቶስ ጋር የተሰቀሉ፤ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉና በሕይወታቸው የተቀደሱ ናቸው።

ኢውግን በሥራ አመራር ለጭነታቸው የተወደዱና የሚደነቁም ሰው ነበሩ። አንዳንድ አከራካሪ ጉዳዮችን ገሸሽ እያደርጓቸውም፤ ይልቁንም በትህትና ነገር ግን በአቋማቸው ጠንክረው፣ በተለሳለሰ የክርክር እግባብና ይቅርታን በተሞላ ባሕርያቸው ይጋፈጣሉ። ጠንካራ መሪ ነገር ግን ከክርስቶስ ጋር የተሰቀሉ ነበሩ።

ለንቀት፣ ለዘለፋና ለሚጠሏቸውም ፈጽመው የሞቱ ሰው ነበሩ። በሥጋ ተገልጦ መቋቋም የሚባል ነገር የለም። በራሳቸው የሚወስዱት ግላዊ ተቃውሞ አይኖርም። ተሰቅለዋል። ተጠራጣሪም አልነበሩም። በነገሮች ላይ አሉታዊ አይታ የላቸውም። ሁልጊዜም



ንቁ ነበሩ። አዎ ተሰቅለው ነበር። ግላዊ ለሆነ ፍላጎታቸው፣ ለእኔነት መሻታቸው ወይም ሌሎችን በቁጥጥራቸው ሥር ለማዋል ፍላጎት የሞቱ ነበሩ። የሌላው የሆነውን ነገር ለመውሰድ፣ ጠባብ ለሆነ አመለካከትና ለቅናት ፈጽመው ሞተዋል። በባሕርያቸውና በግል ሕይወታቸው በነበራቸው መንፈሳዊ ሙላት፣ በጥንካሬያቸው ሁሉ መልካምነት የሚታይባቸው ናቸው። በእርግጥ ተሰቅለው ነበር።

ከዓመት ወደ ዓመት፣ በኢ.ኤም.ኤስ ዓለም አቀፍ ዓመታዊ ጉባኤ ላይ የዶ/ር ኢውግን ኧርኒ መልዕክት የአገልግሎቱ ትኩረት ነበር። ብዙውን ጊዜ የመጀመሪያዎቹ አገልግሎቶች ከተገመተው በላይ ረዥም ጊዜ ይወስዱ ነበር። አገልግሎቱ ረዥም ጊዜ እንዲወስድ ዶክተሩ ባለመፈለጋቸው ግማሽ ሰዓት የነበረውን መልዕክታቸውን ወደ ሃያ ደቂቃና ከዚያም በታች አወረዱት። ዐሥራ ሁለት ደቂቃና ሌላ ጊዜም ስምንት ደቂቃ ብቻ ሲወስድባቸውም ተመልክቻለሁ። ነገር ግን አንዳችም ተቃውሞ ወይም ቅሬታ አይፈጠርም። በቀሪዎቹ ጊዜያት፤ የመጀመሪያዎቹን በርካታ አሳቦች በጥቂት አረፍተነገሮች በመናገር በቀጥታ ወደ ነጥቡ ያልፋሉ፤ ብዙውን ጊዜም የመንፈስ ቅዱስ ቅባትና ኃይል በእርሳቸው ላይ በብርቱ ስለሚሆን እደማጮቻቸው ፈጥነው በመልዕክቱ ይያዛሉ። እያንዳንዷ ቅጽበት በጉዳዩ ላይ ጠቃሚ ነገር ትጨምራለች፤ ማንም ባልገመተበት ሁኔታ የመንፈስ ቅዱስ ቅባት፣ ውበትና ለዛ በተላበሰ መንገድ ንግግራቸውን ይቋጫሉ። በተደጋጋሚ ሁኔታ ከመድረኩ በታች ያለው ስፍራ ጌታን ለመቀበል በሚወስኑ አዳዲስ ሰዎች ይሞላል። እኝህ ሰው የተሰቀሉ ነበሩና መንፈስ ቅዱስ በአስደናቂ ሁኔታ ይገለግልባቸው ነበር።

ሕይወትህን፤ ለጌታ ባለህ ቅናት ሳይሆን ከክርስቶስ ጋር በመሰቀልህ መዝን። ቀናኢነት የግድ የመንፈሳዊነት መገለጫ ነው ማለት አይደለም። ምናልባትም የእኔነት መገለጫ ማስረጃው ሊሆን ይችላል። ስህተት ባለበት ትምህርት ከተያዘ ጀብደኛ ሰው ይበልጥ ማንም ቀናኢ ሊሆን አይችልም። ኀጢአተኛ ከሆነ ባሕርይ በሚመነጭ ቅናትና በመንፈስ ቅዱስ በሚፈጠር የሚቀጣጠል መሻት መካከል ያለው ልዩነት ሰፊ ነው። በራስ አነሳሽነት የሚፈጠር ቀናተኝነት ከገዛ ልቡና የሚመነጭ ነው። ለኢየሱስ ክርስቶስና ለነፍሳት መዳን የሆነ የሚቀጣጠል መሻት ግን በመንፈስ ቅዱስ የተሞላውን ክርስቲያን እንኳ ሳያውቀው እንደሚበላ እሳት የሚወር ነው። ይህ የራስ ጥረት ውጤት አይደለም፤ ይልቁን ከነፍስ ጥልቅ ውስጥ የሚመነጭ መንፈስ ነው። እንዳለመታደል ሆኖ እንዲህ ዐይነቱ የሚቀጣጠል መሻት የሚገለጠው ዐልፎ ዐልፎ ብቻ ነው፤ ምክንያቱም የሚገኘውም ዐልፍ ዐልፎ በመሆኑ ነው። አልፎ አልፎ ብቻ የሚገኝበት ምክንያትም እኔነት የተሰቀለው በጥቂቱ ብቻ በመሆኑ ነው። ይሁን እንጂ ክርስቲያን በዚህ የሚቀጣጠል እሳት በተበላ ጊዜ ከቶ ሊደበቅ አይችልም።

ሕይወትህን፣ ከክርስቶስ ጋር በመሰቀልህ፣ ማለትም በእኔነትህ መሞት መዝን። እኔነት ራሱን የሚገልጠው በብዙ መንገድ ነው። የራሱ የሆነ መሻትም አለው። የራሱን ፈቃድም ይፈልጋል። ሙሉ ለሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ከመታመን ይልቅ በራስ ብቃት የሚተማመን ነው። መድፈር በሚገባው ጊዜ ይፈራል። መበርታት ባለበት ወቅት ይደክማል። በማገርም ሁኔታ ተለዋዋጭ ነው። በራስ ጥረት በቁጥጥር ሥር ሊውል የሚችል አይደለም (ሮሜ 8፥7)። መጽሐፍ ቅዱስ በእኔነት ላይ ድልን



ስመቀዳጀት አንድ መንገድ ብቻ ያመላክተናል፤ ሞት። ዛሬ ወንጌላውያን ከሆኑት መሪዎች መካከል እለቃ መሪዎች በዝተው አገልጋይ መሪዎች ጥቂት የሆኑት ለምንድን ነው? ምክንያቱም የተሰቀሉት ጥቂቶቹ ብቻ በመሆናቸው ነው። ባላቸው ተጽዕኖ ወይም ሥልጣን ምክንያት ለምንድን ነው ብዙ ሰዎች ፈጥነው በሙስና መረብ የሚጠመዱት? ምክንያቱ ባለመሰቀላቸው ነው። የመንፈስ ቅዱስ ምልክት በጥቂቱ ብቻ የሚታይባቸው አገልግሎቶች የበዙት ለምንድን ነው? ምክንያቱ በጭራሽ በእውነት ያለመስቀላቸው ነው።

እኔነት በጥቂቱ ለይስሙላ ብቻ ሳይሆን አግባብነት ባለው የሕይወት ልምምዳችን ሙሉ ለሙሉ እስካልተሰቀለ ድረስ የትንሣኤ ኀይል ብሎ ነገር የሚታሰብ አይደለም። አዎን እኔነት እስካልተሰቀለ ድረስ አንድ ሰው የመንፈስን ሙላት በሕይወቱ ሊለማመድ አይችልም። እኔነት እስኪሰቀል ድረስ ፍቅርም ፍጹም አይሆንም (1ዮሐ 4፥18)። እኔነት እስኪሰቀል ድረስ የተትረፈረፈ መንፈሳዊ ሕይወት ሊመጣ አይችልም። በክርስቶስ ያለ የማያቋርጥ ድልና ኢየሱስ ኢየሱስን የሚሸት ዘላቂ የሕይወት መዓዛ ለተሰቀሉት ብቻ ነው (2ቆሮ 2፥14-15)።

በብሪስቶል የሚገኘው የሙታን ልጆች ማሳደጊያ ድርጅት መሥራች የሆነውና ብዙውን ጊዜ የእምነት ሐዋርያ እንደሆነ የሚነገርለት ጆርጅ ሙለር፤ እግዚአብሔር በእርሱ ሕይወት በኀይል የተጠቀመበት ምስጢር ምን እንደሆነ ተጠይቆ ሲመልስ፣ “የሞትኩባት አንዲት ቀን ነበረች” ብሏል። ሙለር ይህንን የተናገረው መሬቱን እስኪነካ ድረስ ዝቅ ብሎ በማጎንበስ ነበር። እንዲህም ሲል ቀጠለ፤ “ለጆርጅ ሙለር ሞት ማለት የግላዊ

አመለካከቶቹ፣ የምርጫዎቹ፣ የሚወዳቸው ነገሮች እና የፈቃዱ ሞት ማለት ነው። ለዓለም መሞት ማለት ደግሞ በዓለም ዘንድ ያለው ተቀባይነት ወይም የአለም ቁጥጥር፣ ለወንድሞችና ለጓደኞቹ ድጋፍና ተቃውሞ መሞት ማለት ነው። ከዚያች ቀን ጀምሮ እያጠናሁ ያለሁት 'በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት' የማገኝበትን መንገድ ብቻ ነው" (2ጢሞ 2፥15) ብሏል።

ጆርጅ ሙለር በድርጅቱ ለሚያሳድጋቸው ሁለት ሺህ ወላጅ አልባ ልጆች አስፈላጊ የሆነውን ምግብና ሌሎች ወጭዎችን ያለ ምንም ማስታወቂያ፣ አንድም ጊዜ የገንዘብ ድጋፍ ሳይጠይቅ ወይም ምን እንደሚያስፈልገው ሰዎች በጠየቁት ጊዜ ለማናቸውም መልስ ሳይሰጥ ዕለት ዕለት እግዚአብሔርን ሊታመን የቻለው እንዴት ነው? እንዲህ ያለውን ውጥረት ያለ ምንም መጨናነቅና ፍርሃት እንዴት መሸከም ቻለ? ብዙውን ጊዜ የዕለት ወጭዎቹን የሚያገኘው በዚያው ዕለት ነው። በመጠባበቂያነት የሚቀመጥ ነገር በጭራሽ ኖሮት አያውቅም። እንዲህም በመሆኑ "መዝሙር ሀያ ሦስት በሕይወቱ ተጽፏል" እየተባለ ይነገርለታል። ሚስጥሩ ጆርጅ ሙለር የተሰቀለ መሆኑ ነው። በእውነት ከተሰቀለባት ቀን ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ ያለምንም መቆጠብ ይሞላውና ይጠቀምበትም ጀመር።

ሕይወትህን፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 13ን እየጸለይክ በመሰቀልህ እርግጠኛ በመሆንህ መዝን። ያልተሰቀለ ሕይወት እንግዳ የሆኑ ነገሮችን የመላእክትንም ልሳን የሚመስል ነገር ሊናገር ይችላል። ይሁን እንጂ ሁልጊዜም በፍቅር አይናገርም፤ ይልቁንም እንደሚንሿሿ ጽናጽል ይደጋግማል፤ ጣፋጭና የሚቀጣጠል የፍቅር ኃይል የለውም። ያልተሰቀለ ሕይወት ትንቢት ሊናገር፣ አስደናቂ መንፈሳዊ እውቀት ሊኖረውም ይችላል። ነገር ግን ፍቅር አልባ



መሆኑን ያረጋግጣል። ምናልባትም ተአምራታዊ የእምነት ሥራዎችንም ይሠራ ይሆናል። ነገር ግን እኔነትንም ጨምሮ ይገልጣል። ያልተሰቀለ ሕይወት በችግርና በመከራ ውስጥ ጸንቶ መቆም ባለመቻሉ፣ በቀናተኝነት፣ በኩራት፣ በስሜታዊነት፣ ለክርስቶስ ስም በማይመች ሁኔታ ቃላትን በመጠቀም፣ የራሱን በመፈለግ፣ ሌሎችን በመጠርጠርና በተጉጂነት ስሜት ፍቅር አልባነቱን ይገልጻል። ፍቅርህን፣ በመሰቀልህ መዝነው፤ ከዚያም መሰቀልህን ደግሞ በ1ኛ ቆሮንቶስ 13 ላይ በተገለጸው ፍቅር መዝነው።

ፒኮክ በሕይወት እስካለች ድረስ ኩራት ሊሰማት ይችላል፤ የሞተች ፒኮክ ግን ልትኩራ አትችልም። አንበሳ በሕይወት ሳለ በቁጣ እያገሳ ሊጮህ ይችላል። የሞተ አንበሳ ግን የሚያውክ ድምፁና ቁጠኝነቱን ከቶ ሊያሳይ አይችልም። በቅሎ በራሷ መንገድ ለመሄድ እልኸኛ ትሆን ይሆናል። የሞተች በቅሎ ግን የራሷን መንገድ ለመምረጥ አትችልም። ድመት ሳታቋርጥ በመጮህ ብሶቷን መግለጥ ትችላለች፤ የሞተች ድመት ግን እንዲህ ማድረግ አትችልም። ያልተሰቀለ ሕይወት በርካታ ሥጋዊ ባሕርያት ሊያሳይ ይችላል። የተሰቀለ ሕይወት ግን የኢየሱስ ክርስቶስንና የቅድስናን ውበት ያሳያል።

ሄንሪ ሱሶ የተባለው ጀርመናዊ ኃያል ሰው የተወለደው እ.ኤ.አ በ1300 ከክርስቶስ ልደት በኋላ ነበር። በዐስራ ስምንት ዓመት ዕድሜው ሀይል በተሞላበት መንገድ ጌታን አገኘ። እናም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ። ከጻፋቸው መጽሐፍ አንዱ "የአገልጋይ ሕይወት" የሚል ነው። አንድ ቀን የቤቱ በር ተንኳኳ። የማያውቃት አንዲት ሴት ልጇን ይዛ ቆማለች። "የኀጢያትህ ፍሬ

ይሄውልህ" በማለት ልጇን በአቅፉ ውስጥ ጣለችለትና፤ ሄደች። ሴትዮዋ ጥላው መንገዷን ስትቀጥል ሉሶ ድዳ የሆነ ያህል አንዳች ሳይናገር እንደቆመ ቀረ። ያችን ሴት ከዚያ ቀደም አይቷት አያውቅም። ከእርሷ ክስ ፍጹም ነጻ ነበር። ሰዎች እንደሚገምቱት ሉሶ ቅዱስ ሰው እንዳልሆነ ወዲያውኑ በከተማው ውስጥ ወሬው ተሰራጨ። የተናገረውን የማይኖር ፈሪሳዊ እጭበርባሪ! የሚል ርግማን ወረደበት። ልክ እየሞተ እንዳለ ሰው የጣር ድምፅ ያሰማ ጀመር።

ንጽሕናውን እንዴት ማስረዳት ይችላል? ምን ማድረግ አሰበት? ሁኔታው መታገስ ከሚችለው በላይ ሆነበት፤ ነገር ግን ብርታት እንዲሰጠው ወደ ጌታ ይጮህ ነበር። ደግሞ ደጋግሞ፣ "እኔ ንጹህ እንደሆንኩ ታውቃለህ" እያለ ወደ ጌታ ጮኸ። "እኔ አድርጌው እንደነበር አድርግ፤ ስለ ሌሎች ኀጢአት ተሠቃይ፤ ዝም በል" የሚል መልስ ከእግዚአብሔር ዘንድ መጣለት።

ሉሶ መስቀሉን አነሣና ኢየሱስን ተከተለ። የተቀበለውን ልጅ ራሱን ለመከላከል አንዳችም ቃል ሳይናገር በፍቅርና በትህትና ተንከባከበው። ከዓመታት በኋላ ያች የማትታወቅ ሴት ተመልሳ መጣችና ሉሶ ምንም ጥፋት የሌለበት ሰው መሆኑን ለትማ ለሰው ሁሉ አሳወቀች። ምናልባትም እግዚአብሔር በሉሶ ሕይወት አብዝቶ የተጠቀመው ከክርስቶስ ጋር ፈጽሞ የተሰቀለ በመሆኑና እርሱ በሕይወት የሌለ፣ ክርስቶስ ግን በእርሱ የሚኖር በመሆኑ ነው።

ሕይወትህን፣ ከኀጢአተኛው ባሕሪህ የሚመነጩ የሚቀጣጠሉ መሻቶችህና እቅዶችህ (በግሪክ ቋንቋ ጠንካራ መሻቶችህ) በመስቀላቸው መዝን (ገላ 5፥24)። የሚቀጣጠሉ መሻቶችና እቅዶች የተቀደሱ ወይም ኀጢአትን የተሞሉ ሊሆኑ



ይችላሉ። መስቀልህን፣ በተቀደሱ መሻቶችህና እቅዶችህ መዝን። እግዚአብሔርን አብልጠህ በመፈለግህ፣ ለእግዚአብሔር ቃል ባለህ ረሃብና ቃሉን ስታነብና ስታሰላስል በውስጥህ በሚሰማህ ደስታ መዝን (መዝ 119፥47-48፣ 72፣ 97፣ 103፣ 162)። መስቀልህንም፣ ከኢየሱስ ጋር በጸሎት ኅብረት ለማድረግ ጊዜን ለመውሰድ ባለህ ርሃብ፤ ወደ ጸሎት ስፍራህ ስትሄድ በሚሰማህ ደስታ እንዲሁም በጸሎትህ ወቅት በምታደርገው ብርቱ ልመና መዝን።

መስቀልህን፤ ለክርስቶስ ኢየሱስ ባለህ የተቀደሰ ፍቅር፣ ለጽድቅና ለቅድስና ባለህ የሚቀጣጠል መሻትህና ከኀጢአትም ፈጽመህ ለመራቅ ባለህ ፈቃድ መዝን። መስቀልህን የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያንና በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉ ወንድሞች እንዲሁም እህቶች ባለህ ልባዊ መውደድ መዝን (1ጴጥ 1፥22)። መስቀልህን፣ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመመስከርና ነፍሳትን ለክርስቶስ ለመማረክ ባለህ የሚቀጣጠል መሻትህ መዝነው። ከክርስቶስ ጋር በተሰቀሉ ሰዎች ሕይወት ውስጥ የሚገለጹ የተቀደሱ ዓላማዎችና የሚቀጣጠሉ መሻቶች እነዚህ ናቸው።

መስቀልህን፤ ያልተቀደሱ ፍላጐቶችና ሥጋዊ መሻቶች ከሕይወትህ በመወገዳቸው መጠን መዝን። መቼም ቢሆን የትኛ ውም ያልተቀደሰ ፍላጐት ከክርስቶስ ጋር ያለህን አርምጃ እንዲበክል አትፍቀድ። መራርነት፣ ተቃዋሚነትና የትችት መንፈስ (ዕብ 12፥15) በልብህ ውስጥ ተቀብረው፤ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር ያለህን ጣፋጭ ኅብረትና ከቅዱሳን ክርስቲያኖች ጋር ያለህን ደስተኛ ግንኙነት እንዲያበላሹ አታድርግ። እንደነዚህ ዐይነት የባሕርይ ዝንባሌዎች ሙሉ የሆነውን ስቅላት ላለማወቅህ እርግጠኛ የሆኑ ማስረጃዎች ናቸው።

መስቀልህን፣ ንዴትና ቁጣ ከሕይወትህ በመወገዳቸው መጠን መዝን:: ሌሎች ሰዎች የሚያሳዩህ ያልተገባ ድርጊትና የሚናገሩህ ንግግር በልብህ ውስጥ ያልተቀደሰ እሳት እንዲጭር አትፍቀድ:: ሰይጣንን እንጂ ማንንም አትቆጣ፣ በኀጢአት ላይ እንጂ በማንም ላይ አትናደድ:: የተቀደሰ ቁጣ የሚባለውን እንኳን ለሰዓታት ያህል እንዲቆይ የምትፈቅድ ከሆነ እግዚአብሔርን መምሰልህንና የተቀደሰውን ጣፋጭነትህን ሊያደበዝዝና ሊያጠፋው ይችላል (ኤፌ 4፥26):: መስቀልህን፤ በሁሉም ጊዜ ባለህ ፍቅር፣ ፍሬ በማፍራትህና ባለህ የይቅርታ ልብ መዝን::

መስቀልህን፣ ዓለም ለአንተ እንዴት እንደተሰቀለና አንተ ለዓለም እንዴት እንደተሰቀልክ በማወቅ መዝን (ገላ 6፥14):: የዓለም መንፈስ በአንተ ላይ የነበረውን ሥልጣን ለቋልን? በልብህስ ላይ የነበረውን ተጽዕኖ አጥቷልን? ዓለማዊ የሆነ ባህሪ፣ መዝናናትና ደስታን የሚሰጡህ ክርስቶስን የማያስከብሩ ነገሮች እንዲሁም ዓለማውያን ሰዎች በአንተ ላይ ካላቸው ተፅእኖዎች ሁሉ አሁን ነጻ ነህን? እንደ ፈቃድህ እግዚአብሔርን ለመውደድና ለማገልገል በእውነት ነጻ ነህን?

መስቀልህን፤ በዚህ ዓለማዊ በሆነ ዘመን ከሚለነዘሩብህ አስተያየቶች፣ ፋሽንና ልማድ አስራት ነጻ በመሆንህ መዝን:: መስቀልህን፣ ወዳጆችህና ባልንጀሮችህ በቁሳዊ ነገሮች፣ ተድላን በመውደድ ባላቸው መሻት፣ በፋሽንና በገንዘብ አጠቃቀማቸው ከሚያሳድሩብህ ተጽዕኖ ነጻ በመሆንህ መዝን:: መስቀልህን፣ እግባብ የሌላቸውን፣ ጊዜ የሚገድሉና ብዙውን ጊዜም ሥነምግባር የጎደላቸውን የቴሌቭዥን ፕሮግራሞች በማስወገድህ መዝን::



"አመንዝሮች ሆይ፤ ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንዲሆን አታውቁምን? እንግዲህ የዓለም ወዳጅ እንዲሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኗል" (ያዕ 4፥4):: ሕይወትህን፣ የሕይወት እንቅስቃሴህ ዓለማዊ ወይም የተሰቀለ በመሆኑ መዝን:: "ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዐይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፣ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም" (1ዮሐ 2፥15-16):: አንተ ለዓለም፣ ዓለም ደግሞ ለአንተ ተሰቅላችኋልን? (ገላ 6፥14)::

ሕይወትህን በመስቀልህ መዝን:: ሕይወትህን፣ ለምስጋናና ለነቀፌታ ጆሮህን በመድፈንህ፣ የሌሎችን ጉድለት ላለማየት ዓይንህን በመጨፈንህ ለተጉጂነት ስሜት፣ ኀጢአተኛ ለሆነው ሥጋዊ መሻትህ፣ ለዓይንህም አምሮትና ኩሩ ለሆነ ሕይወት ምውት በመሆንህ መዝን (1ዮሐ 2፥15-16):: ሕይወትህን፣ ለራስህ የፍላጎት ድምፅ ጆሮህን በመድፈንህና በእግዚአብሔር ፈቃድ ደስ በመሰኘትህ፣ ለግል ክብርና ፍላጎት ምውት በመሆንህና ጌታን ግን በማክበርህ፣ ለዓለም ፍቅር በመሞትህ ነገር ግን ለእግዚአብሔር እና ለመንግሥቱ ያለማቋረጥ በምትሰጠው ፍቅር መዝን:: ሕይወትህን ራስህን ቸል ብለህ ለእግዚአብሔር መንግሥትና ለእግዚአብሔር ጽድቅ ቅድሚያ በመስጠትህ መዝን::

በእርግጥ ሕይወትህን እየመዘንክ ነውን? ለራስ ማንነት ምን ያህል እንደሞትህ፣ ጆሮህ እንደተደፈነ፣ ዐይኖችህ እንደታወሩና መንፈሳዊ ላልሆኑት ነገሮች ፍላጎት በማጣትህ መዝን:: በአንጻሩም

መንፈሳዊ ለሆነው ራእይ፣ የእግዚአብሔርን የሹክሹክታ ድምፅ ለመስማትና የመንፈስ ቅዱስን ዳሰሳ ያስማቋረጥ ልብ ለማለት ንቁ በሆንክበት መጠን መዝን:: ሕይወትህን ለእግዚአብሔር ምን ያህል ሕያው በመሆንህና ከዚህ ውጭ ላሉ ነገሮች ምን ያህል ምውት በመሆንህ መዝን:: ሕይወትህን በመስቀልህ መዝን::



# የተሰቀለ ልብ ስጠኝ

የተሰቀለ ልብ ስጠኝ፤ አንተ የሞትክለትን ልብ አድለኝ:: በክበረው ደምህ የነጻ የእግዚእብሔርን የሚመስል ሕይወት ስጠኝ::.

ለራሱ ማንነት የሞተ ልብ ስጠኝ:: ለዓለም፣ ለራስ ክብርና ለህብት የሞተ ልብ አድለኝ:: ለትእቢት፣ ለራስ ዝናና ስሙን ከፍ ከፍ ለማድረግ ከመፈለግ የሞተ ልብ ስጠኝ::

ምድራዊ የሆነው ስኬት ለእኔ ኪሣራ እንደሆነ እስክቆጥር ድረስ፣ እሮጌውን ፍጥረታዊ ሰው በመስቀልህ ላይ ስቀለው:: እኔ ለዓለም፣ ዓለምም ለእኔ ፈጽሞ እስክንሞት በዚያው ተወው::

ትሁት፣ ሩህሩህና በጎ የሆነ የተሰቀለ ህሊና ስጠኝ:: ማንኛውንም ጥሪህን ተቀብሎ የሚዘጋጅ የተሰቀለ ፈቃድ ስጠኝ::

እባክህ ማንኛውም ስሜታዊነቴ የተሰቀለ ይሁን፤ እጅጉን አብዝቶ በተፈተነ ሕይወት ፍቅሬን ፍጹም አድርግልኝ:: መላውን እኔነቴን፤ አዎ ሁለንተናዬን በመስቀልህ ላይ፣ በቀራንዮ መስቀልህ ላይ ቸንክረው.:

ጌታ ሆይ፤ ሞትህ ሁልጊዜም በሕይወቴ ይገለጽ፤ ከተቸነከርኩበት እንዳልወርድ እባክህ እርዳኝ:: በየእንዳንዷ ደቂቃ እንደተሰቀልኩ አንድቆይ አግዘኝ:: በጦር በተወጋው ጎንህ አጠገብ በመስቀልህ ላይ ቸንክረኝ::

ዊስሌይ ዱዌል

ነው:: በጸጥታ ውስጥ እንደሚያረሰርስ ጠል ያረካሃል:: እንደ ምንጭ ወይም እንደ ወንዝ ውሃ ያለማቋረጥ እየፈሰሰ ውስጥህን ይባርካል:: እንደሚባርክ የወንዝ ውሃም ከአንተ ውስጥ ወጥቶ ይፈሳል:: በብሉይ ኪዳን ዘመን ነቢያት ተሰይተው ይቀመጡ እንደነበር፣ በቅባቱ አንተን ለይቶ ያስቀምጥሃል:: ቅዱስ በሆነው እሳቱ አሁንም አሁንም ውስጥህን ያነጻል (1ኛ ተሰ 5፥23)፤ የተቀደሰ ፍቅርንና ቅንአትን ያቀጣጥላል:: ይህንን ሁሉ የሚያደርገው ውብት ባለውና ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ ነው::

ከእነዚህ ነገሮች ሁሉ በላይ በላጭ የሆነው ግን በውስጥህ የሚኖር የተቀደሰ ባልንጀራ፣ አማካሪ፣ መሪ፣ ረዳትና ጌታ የመሆኑ እውነታ ነው:: የክርስቶስን የመቤዠት ጸጋ ሁሉ በልብህ ይተገብራል፤ ለተቀደሰ ሕይወትና አገልግሎት ብቁ ያደርግሃል፤ የተቀደሰ ሕይወት፣ ጉልበታም አገልግሎት እንዲኖርህና፣ ለእግዚአብሔር በምትዋጋው መንፈሳዊ ጦርነትም ኀይልን እንድትሰብስ ያስችልሃል::

መንፈስህ በማይታይ ሁኔታ በውስጥህ እየኖረ አካልህን በመጠቀም በሚያስደንቅ ሁኔታ ራሱን እንደሚገልጥ፣ መንፈስ ቅዱስም እንዲሁ በመንፈስህ ውስጥ ይኖራል፤ መንፈስህን ያነጻል፣ መንፈስህን ያበረታል፤ መንፈሳዊ የሆነውን ሕይወትህንም ፍሬያማ ያደርጋል:: ባሕርይህ ለማነጽ የውስጥ ሰብእናህ የመንፈስን ፍሬ ያፈራ ዘንድ ያስችለዋል (ገላ 5፥22-23):: እነዚህ ነገሮች ቅዱስ በሆነው መለኮታዊ ሥራው አስቀድሞ በአንተ ውስጥ ከዚያም ለሌሎች የሚተርፉ መልካም የሆኑ ብቃቶች ናቸው::

መንፈስ ቅዱስ ወደ ሕይወትህ ዘልቆ በገባ ጊዜ፣ ዳግም ልደትን፣ መንፈሳዊ ሕይወትን ይሰጥሃል:: ወደ እግዚአብሔር



ቤተሰብ ይቀላቅልሃል (ሮሜ 8፥15)፤ የክርስቶስ አካል በሆነች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይከትሃል (1ቆሮ 12፥13):: ከዚያ በኋላም መዳንህን ይመሰክርልሃል (ሮሜ 8፥16፤ 1ዮሐ 5፥6፣10)::

አንተ እንደ አማኝ ሁለንተናህን በፍቅር ሙሉ ለሙሉ ስትሰጠው መንፈስ ቅዱስ ያነጻሃል፤ ይቀድስሃል (ዮሐ 17፥17፤ ሐዋ 15፥8-9፤ 2ተሰ 2፥13)፣ ይሞላሃማል (ሐዋ 2፥4፣ 39፤ ኤፌ 5፥18):: በዚህ ጊዜ መንፈስ በመላው ማንነትህ ጌትነቱን ያሰለጥናል፤ የድል ሰው ያደርግሃል፣ ክርስቶስንም ማገልገል እንድትችል ኀይልን ያለብስሃል፤ ይጠቀምብሃል (ሉቃ 24፥49፣ ሐዋ 1፥8)::

ከዚህ በኋላ ከእርሱ ጋር በሚኖርህ የተቀደሰ ኅብረት፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ሕይወት የሚመስል ውብት ያለው ተብሎ የተገለጸውን የመንፈስ ፍሬ በአንተ ውስጥ ለማብዛት ይመቸዋል (ሮሜ 8፥23፣ ገላ 5፥22-23):: ይህን የሚያደርገው አብዝተህ ኢየሱስን እንድትመስል ነው:: ሙሉ ለሙሉ ለእርሱ የተሰቀቀ ማንነትህን በመውረስ በአንተ መለኮታዊ የሆነ ተግባሩን ያከናውናል:: መካሪህ ነውና (ዮሐ 14፥26)፤ ይመራሃል (ሮሜ 8፥14፣ ኢሳ 58፥11):: ጸሎትህን የሚመራና ኀይል የሚያላብስም ነው (ሮሜ 8፥26-27) ኀያል ረዳትህም ነው (ዮሐ 14፥26):: ጰራቅሊጦስ የሚለው የግሪክ ቃል አንደኛው ትርጉም ረዳት የሚል ነው:: የሚቀባህም እርሱ ነው (2ቆሮ 1፥21-22፣ 1ዮሐ 2፥20፣27)::

የእርሱ ማደሪያ መሆንህ፣ በእርሱ መሞላትህና በራሱ በመንፈስ ቅዱስ ኀይልን መልበስህ፣ ታላቅ የእግዚአብሔር ልጅነትህ

ያገኘኸው መታደል ነው። አንድ ጊዜ ያነጻህና ይሞላህ ዘንድ ሙሉ በሙሉ ራስህን ከሰጠኸው፣ በጌትነቱ አመራር ሥር እስከኖርክና እስካገለገልከው ድረስ ደግመህ ደጋግመህ መሞላት ትችላለህ (ሉቃ 11፥13)።

ሕይወትህን መዝን፤ ገምግመው። እንደ ተጠራህበት መጠራት በሙላት የምትኖረው ምን ያህል ነው? ኢየሱስ ያለማቋረጥ ይቀድስህ ዘንድ መንፈሱን ሰጥቶሃል (1ተሰ 5፥23-24)። እርሱ ያነጻህ ዘንድ ምን ያህል ሙሉ በሙሉ ራስህን አዘጋጅተሃል?

ብዙ መንፈሳዊ ቅኔዎች ይህንን መንፈሳዊ እውነታ ሊገልጡት ሞክረዋል፤ ቻርልስ ዌስሌይ እንዲህ ሲል ጽፎ ነበር።

የከንቱ መሻቴን ገለባ ሊያቃጥለው
ተራራውን ነቅሎ ሊጥለው።
አ! በውስጤ ያለ ይህ የተቀደሰ እሳት
መንደድ መንቦግቦግ ጀምሯል በኀይል ሙላት
የሚያጠራ እሳት በልቤ ይቀጣጠላል
የነፍሴን የውስጠኛ ውስጥ ያጸዳል
በሕይወቴ ጓዳ ጎድጓዳ ሁሉ ተዛምቷል
መላውን እኔነቴን ቀድሷል።

ሕይወትህን፣ በአንተ የሚኖረው የሚያቃጥለው የመንፈስ ቅዱስ እሳት ሕይወትህን ባነጻበት ማንጻት መጠን መዝነው። ይሞላህና ይቀድስህ ዘንድ እንዲችል ራስህን ሙሉ ለሙሉ ሰጥተሃልን? ሕይወትህን በውስጥህ ባለው የመንፈስ ቅዱስ ሙላት መዝነው። በሕይወትህ ያለው የመንፈሱ ህልውናና መገለጥ በጥቂቱ ብቻ ነውን? እርሱ ሕይወትህን በተቀደሰ ህልውናው እንደሞላውና እንዳጥለቀለቀው ለመመስከር በሚያስችል እውነታ ውስጥ ነህን?



በእርግጥም ከእግዚአብሔር የተወለደ ማንም ቢሆን፣ በመንፈስ መሞላት ይችላል፤ አዎ ማንም ወጣት ይሁን ሽማግሌ፣ ወንድ ይሁን ሴት፣ የቤትም ሆነ የጉልበት (የቀን) ሠራተኛ የቢሮ ሰው ወይም ክርስቲያን አገልጋይ ሊሆን ይችላል። ሕይወትህን በመንፈስ ቅዱስ ሙላት መዝነው።

የደኅንነት አርበኞች በመባል የሚታወቀው የወንጌል ምስክርነት ቡድን መሥራቾች የሆኑት የዊልያምና የካትሪን ቡዝ ልጅ የሆነችው ካትሪን ቡዝ፣ በወጣትነቷ ካቲ ተብላ ትጠራ ነበር። ገና ከልጅነቷ ጀምሮ ጌታን ትወድ ነበርና የአሻንጉሊቶቿን አሻንጉሊቶቿን ሰብስባ ስለ ኢየሱስ ፍቅር ትተርክላቸዋለች። ዕድሜዋ ዐሥራ አንድ አመት በሞላ ጊዜ የሰንበት ትምህርት ማስተማር ጀመረች። አስራ ሁለት ዓመት ሲሞላት ደግሞ በቤቷ ውስጥ የሕፃናት ኅብረት ጉባኤ ማድረግ ጀመረች። ልጆቹ በእንባ ኀጢአተኛነታቸውን እየተናዘዙ ውብ በሆነ ሁኔታ ድነትን ተቀበሉ። በዐሥራ ሦስት ዓመቷ በሰራዊቱ የአደባባይ ጉባኤ ላይ ንቁ የሆነ የምስክርነት አገልግሎት መስጠት ጀመረች።

ዕድሜዋ ዐሥራ ስድስት ዓመት በሞላ ጊዜ ደግሞ፤ በለንደን ከተማ የተለያዩ ክፍሎች የወንጌል ዘመቻ ፕሮግራሞችን አደረገች። በዐሥራ ሰባት ዓመቷ ከለንደን ከተማ እየወጣች ከሦስት እስከ አራት ሳምንት የሚወስዱ የወንጌል ዘመቻዎችን ከከተማ ከተማ በመዘዋወር አካሄደች። ብዙውን ጊዜም የጉባኤ አዳራሾቹ በሰው ይጥለቀለቁ ነበር። በመቶዎች የሚቆጠሩ ኀጢአተኞች ለጌታ እጆቻቸውን ሰጡ። በተደጋጋሚ ጊዜ በአገልግሎቷ ባልተለመደ ሁኔታ የእግዚአብሔር ህልውናና ኀይል ይገለጥ ነበር። በተለያየ የሕይወት ዘርፍ የተሰማሩ እጅግ ብዛት ያላቸው ኀጢአተኞች

ድነትን ተቀበሉ። በመቶዎች የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች ሕይወታቸውን ሙሉ ለሙሉ ከእንባ ጋር ለእግዚአብሔር አስረከቡ፤ በመንፈስ ቅዱስም ተሞሉ።

አጅግ ብዙዎች በዚች ታናሽና በመንፈስ ቅዱስ በተሞላች፣ ጣፋጭና ለስላሳ ግን ደግሞ ኀያል ድምፅ ባላት ወጣት ልጃገረድ ይማረኩ ነበር። አንዳንዶች እንዲያውም መላእክትን ትመስል ነበር ይላሉ። ምንም እንኳን ገና ወጣት ብትሆንም፣ በኋለኛው ዘመኗ በመላው አውሮፓ "የድነት አርበኞች" የወንጌል ምስክርነት ጓድ መሪ በመሆን "ማርሻል" የሚል የቅጽል ስም የተቀዳጀች ዝነኛ ሴት በሆነችበት ጊዜ እንደተጠቀመባት ሁሉ በትንሽነቷም፣ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላችና የሚገለገልባት ልጅ ነበረች።

ሕይወትህን የመንፈስ ፍሬ በሕይወትህ በመትረፍረፉ መዝን። በመንፈሳዊ ሕይወትህ ውስጥ እነዚያ ፍሬዎች ሁሉ ያለማቋረጥ ይታያሉ? ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት (ገላ 5፥22-23)፤ ከእነዚህ መካከል በሚታይ ሁኔታ ክሰብእናህ የጎደለ ይኖራልን?

ሐዋርያው ጳውሎስ በቀጣዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፤ ይህ ጉዳይ የተሰቀለን ሕይወት በደንብ የሚገልጽ መሆኑን እንዲህ ሲል ያብራራዋል፤ "የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ" (ቁ. 24)። የተሰቀለ ማንነት ብቻ ነው ባልተቆጠበ ሁኔታ የመንፈስ ፍሬን ማፍራት የሚችለው፤ አንተስ ተሰቅለሃልን? ከዚያም ጳውሎስ እንዲህ ሲል ሐሣቡን ይጠቀልላል፤ "በመንፈስ ብንኖር፣ በመንፈስ ደግሞ እንመላለስ" (ቁ. 25)። አዎ የተሰቀለውን ሕይወት እውን የሚያደርገው መንፈስ ቅዱስ



በመሆኑ፣ መልካም የሆነው የመንፈስ ፍሬ በሕይወትህ ሲገለጥና አረማመድህም ከእርሱ ጋር ሲስተካከል ይችላል።

የመንፈሱ ሙላት ማለት፣ መንፈስ ቅዱስ በአንተ ውስጥ ራሱን የገለጸበት ሙላት፣ አንተን ሙሉ ለሙሉ የወረሰበት መጠንና አንተን በሙላት የተጠቀመበት ሁኔታ ማለት ነው። የመንፈስ ፍሬ ማለት ደግሞ፣ የቅድስናውና የሕይወቱ ሙላት በአንተ ውስጥና በአንተም ውስጥ ዐልፎ የተገለጠበት ሁኔታ ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ በአንተ ውስጥ ባለ ደስታን ሊቀበል በሚችል ማንነትህ ውስጥ የደስታን ሙላት አያፈስልህም። ይልቁን ራሱ የደስታ መንፈስ በመሆኑ በአንተ ውስጥ ሆኖ ይደሰታል፤ በአንተም ውስጥ ዐልፎ ደስታው ይገለጻል። የፍቅርንም ሙላት አይሰጥህም፤ ነገር ግን እርሱ ራሱ በአንተ ውስጥ ፍቅር ነው። በእርሱ ሙላት ውስጥ እስካለህ ድረስ በአንተ ውስጥ ሆኖ ይወዳል፤ በአንተም ውስጥ ዐልፎ ይወዳል። የኀይሉን ሙላት በአንተ ውስጥ አያከማችም፤ ይልቁንም እርሱ ሁሉን ቻይ በመሆኑ በማንነትህ ውስጥ የተቀደሰ ኀይሉን ይገልጻል። በዚህም የተቀደሰ ሕይወት እንድትኖር ያበረታታሃል፤ ውጤታማ የሆነ አገልግሎት እንዲኖርህም ያደርጋል። የቅድስናን ሙላት አይሰጥህም። እርሱ የተቀደሰ ነው፤ በመሆኑም በሕይወትህ የተገለጠው ቅድስና ብቸኛው ምንጭ እርሱ በአንተ ውስጥ በመኖሩና በአንተም ውስጥ የተቀደሰ ባሕርይውን የመግለጡ ውጤት ነው።

ነገሩ እንዲህ ከሆነ፤ በመንፈስ ቅዱስ በሙላት ወይም በመጠኑ መሞላት ታዲያ ምን ማለት ነው? አንተ አብልጠህ ወይም በመጠኑ ራስህን በመስጠትህ ምክንያት በአንተ ውስጥ ራሱን ለመግለጥ መንፈስ ቅዱስ አብልጦ ወይም በመጠኑ ያገኘው ነጻነት

ማለት ነው፡፡ ይህም ማለት አብልጠህና አሣንሰህ ልብህን በሙላት ለእርሱ በመክፈትህና በመታዘዝህ ምክንያት፣ የእርሱ ሕይወት በውስጥህ በልጦና አንሶ የመገለጡ እውነት ነው፡፡ እርሱ ሕይወቱን በአንተ ውስጥ የሚኖረው ራስህን ለእርሱ አሳልፈህ በሰጠህበት መጠንና ከእርሱ ጋር በምታደርገው መተባበር ነው፡፡ በአንተ ውስጥ ያለውን ህልውናውን በሁለት መንገዶች ልትመዝን ትችላለህ አንድም ለእርሱ በምትሰጠው ምላሽ ወይም እርሱ ራሱን በአንተ ውስጥ በመግለጡ ነው፡፡

ፍራንሲዝ ሪድሌይ ሃቨርጃል የተወለደችው በጸሎት፣ በእግዚአብሔር ቃል ምንባብ፣ መጽናናት ባለበት ፍቅርና ሰዓትን በማክበር ምሳሌነት እያሳዩ ካሳደጓት መልካም ወላጆች ነበር፡፡ ከዕድሜዋ ቀድማ የበሰለች ልጅ በመሆኗ በአራት ዓመት ዕድሜዋ መጻፍ እና መጽሐፍ ቅዱስን በትክክል ማንበብ ቻለች፡፡ በሰባት ዓመት ዕድሜዋ ግጥም መጻፍ ጀመረች፡፡ ዕድሜዋ ዐሥራ አራት ዓመት በሞላት ጊዜ ስለመዳኗ ግልጽ የሆነ ማስተማመኛ ተቀበለች፡፡ "ከዚያች ቅጽበት ጀምሮ ሰማይና ምድር ከቀደመው ጊዜ ይልቅ ብሩህ ሆነው ታዩዋት"፡፡

ፍራንሲዝ ሀያ ሁለት ዓመት ሲሞላት አዲስ ኪዳንን፣ መዝሙረ ዳዊትንና ለእርሷ ተመራጭ የሆነውን የትንቢተ ኢሳይያስን መጽሐፍ በቃሏ ለመያዝ ቻለች፡፡ ቀጥላ ደግሞ የደቂቀ ነቢያትን መጻሕፍት በማስታወስ በቃሏ ለመውጣት በቃች፡፡ ገና ከሕፃንነቷ ጀምሮ እስደናቂ የሆነ የሙዚቃ ችሎታ ነበራት፡፡ የሀንድልን፣ የቤትሆቨንንና የሜንድልስሾውን ሙዚቃዎች ያለኖታ መጽሐፍ መጫወት ትችል ነበር፡፡ ሙዚቃን ከሚያቀርቡ የሙዚቃ ቡድኖች ጋር የምትጫወት ቢሆንም የምትጫወተው ግን መንፈሳዊ



ሙዚቃዎችን ብቻ ነበር፡፡ ብዙውን ጊዜዋን የሰጠችው መጽሐፍ ቅዱስ ለማንበብና ለማስታወስ ነው፡፡

ፍራንሲዝ በጥልቀትና ያለማቋረጥ ኢየሱስን ትወዳለች፣ በዕድሜዋ ዘመን ሁሉ ግን ለውስጣዊ የቅድስና ልምምድ ትልቅ መሻት ነበራት፡፡ "አ፤ በእርግጥ ያነጥረኛል፤ በማንኛውም ዋጋ ቢሆን ያነጻኛል" "አ፤ እርሱ የተቀደሰ ሽክላ ያደርገኛል እናም ለጌታ መገልገያነት ይጠቀምብኛል!" በሚሉ ግጥሞቿ ይህን መገንዘብ ይቻላል፡፡ አንድ ቀን በድንገት በአዕምሮዋ ውስጥ "የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኀጢአት ሁሉ ያነጻናል" የሚለው የተስፋ ቃል ታወሳት፡፡ እናም "አዎ ቀኑ እ.ኤ.አ . . . ታህሳስ 2፤ 1873 ነበር፤ እውነተኛ የሆነውን የተቀደሰ ባርኮት ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁበት ዕለት ነው፡፡ አንድ ጊዜ አይታችሁ ዳግመኛ እንደማትዘነጉት ነበር፤ ያየሁት ልክ እንደ ኤሌክትሪክ የብርሃን ብልጭታ ነበር፡፡ ሙሉ የሆኑ ባርኮቶች ለመቀበል አስቀድሞ ሙሉ የሆነ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ እግዚአብሔር በአንደኛው መንገድ ወደሌላኛው ይቀበላችኋል፡፡ እጅግ ግልጽ በሆነ ሁኔታ እግዚአብሔር ራሱ ነው ያሳየኝ" ስትል ጻፈች፡፡

ከዚያች ቀን ጀምሮ የነበራትን የሕይወት ልምምድ፣ የዊቶን ኮሌጅ ቻንስለር የሆኑት ቪ.ሬይሞንድ ኢድማን እንዲህ ሲሉ ይገልጹታል፤ "በማያቋርጥ ሁኔታ የመንፈስ ፍሬ በሕይወቷ ይገለጥ ነበር፡፡ ለአዳኟና ለሌሎችም ሰዎች የማይጠፋና የማይለወጥ ፍቅር ነበራት፡፡ ሕይወቷን ሁሉ እንደ ፀሐይ ያበራ ደስታ በውስጧ ነበር፤ አስቀድማ በነበራት የሕይወት ልምምዷ የምታውቀው በክረምቱ ደመና መሀል ብቅ የምትል ደብዛዛ ብርሃን ያላትን ጸሐይ ዐይነት

ብርሃን ሲሆን አሁን በሕይወቷ የበራው ብርሃን ግን በበጋ ወራት ከምትገለጥ ፀሐይ እንደሚረጭ አብረቅራቂ ብርሃን ያስ ነበር"::

መንፈስ ቅዱስ ከእርሷ ውስጥ እየፈለቀ እንደሚፈስ ወንዝ የማታቋርጥ ባርኮት አደረጋት (ዮሐ 7፥38):: "ሁሉም ነገር ለክርስቶስ" የሕይወቷ ዋነኛ መርሕ ነበር:: ጽሑፎቿም "የማይነገር ጣእም" "እንዲህ ያለ የከበረ ሕይወት" "ምልዐት" "ወሰን የሌለው ባርኮት" "ይህ ትልቅ ነገር አይደለምን?" "ልገልጸው ቃላት የሉኝም" "የእግዚአብሔር ፈቃድ ጣፋጭ ነው" በሚሉ ሐሣቦች የተሞሉ ነበሩ::

ምንም እንኳን ደካማና ብዙውን ጊዜም በትላላቅ ጉባኤዎች ላይ መገኘት የማትችል ብትሆንም በማያቋርጥ ሁኔታ ለሌሎች ባርኮት ነበረች:: ሁልጊዜም ባገኘችው አጋጣሚ ሁሉ ስለ ክርስቶስ ለቤተሰቦቿ፣ ለጓደኞቿ፣ ለማታውቃቸው ሰዎች፣ ለሠራተኛ ልጃገረዶች፣ በሴቶች ት/ቤት ውስጥ ላሉ ልጃገረዶች፣ በመንደር ውስጥ ባሉ ቤቶች፣ በልብስ ንጽሕና ቤቶች፣ በቤት ውስጥ ስብሰባዎችና በተመረጡ ሰዎች መካከል ትመስክራለች፤ በቤተ ክርስቲያን ኳየር ውስጥ በዝማሬ መሪነት ታገለግላለች፤ በድንኳን ውስጥ በሚደረጉ ጉባኤዎች ንግግር ታደርጋለች:: ይች ሴት "አዳኙ በፊትህ ያቀረበልህን ያልተለመደና ሩቅ ርቀት የሚያስኬድ ሥራ ለመሥራት ፈቃደኛ ሁን" ስትል ጽፋለች::

የሰንበት ትምህርት ማስተማር ትወዳለች:: አዘውትራም በቤተ ክርስቲያን፣ በሆስፒታሎችና በልዩ ልዩ ቦታዎች ትዘምራለች:: በአንድ ደብዳቤዋ ላይ እንዲህ ስትል ጽፋለች፤ "በየዕለቱ ማለዳ ከዐሥራ አምስት እስከ ሃያ የሚሆኑ ደብዳቤዎችን



ለመጻፍ፤ የተጻፋትንም ለማረም፣ የእርትእት ሥራ የሚፈልጉ መጣጥፎች፣ ልካቸው ያልቻልኳቸው ግጥሞችና ሙዚቃዎች፣ አራት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ምንባቦች ወይም ሳምንታዊ የትምህርት ክፍለ ጊዜዎች፣ በብዙ ተስፋ በጉጉት እርዳታ የሚጠብቁ ብዙ ሰዎች፣ እየቀረበ የመጣው የወንጌል አገልግሎት ግዳጅ ሳምንት፣ ከዚያ በኋላም የሚጠብቁኝ ሌሎች ሥራዎች - የዐሥር ደቂቃ የእፎይታ ጊዜ እንኳን የለኝም:: ዶክተሬ ደግሞ የአካል ብቃትሽ እየወረደ ነው ብሎኛል"::

የሞተችው በአርባ ሁለት ዓመት ዕድሜዋ ሲሆን፣ በዓለም ላይ ለእግዚአብሔር ታላቅ የሆነ በጎ ተጽዕኖን አምጥታለች:: በመንፈስ ከተቀባው ብዕሯም የጸሎት መጻሕፍት፣ "ሕይወቴን ለአንተ ሰጥቻለሁ" "ሕይወቴን ተቀበል፤ እንደወደድከም ይሁን" "እንደ ከበረ ወንዝ" የመሳሰሉ ግጥሞችና ቅኔዎች ፈልቀዋል::

ሕይወትህን፤ በቀስታ ሽው ለሚል ነገር ግን ኃያል ለሆነ የእግዚአብሔር መንፈስ በምትሰጠው ምላሽ መዝን:: ሕይወትህን ለእርሱ ባለህ ረሃብ መዝን:: በልባቸው የሚራቡ ብጹዐን ናቸው ይጠግባሉና (ማቴ 5፥6፣ ኢሳ 55፥1-2):: እብዝተህ በተራብክ መጠን ነው እርሱ አብዝቶ የሚሞላህ:: ሕይወትህን፣ ለመንፈስ ቅዱስ መገኘትና ሥራ ምን ያህል እንደተጠማህ፣ ምን ያህልስ ራስህን እንደሰጠህ፣ ለሁሉም ፈቃዶቹና ለሁለንታናዊ መገኘቱ፣ በጥልቀትና ያለማቋረጥ በተራብክበት መጠን መዝነው:: ሕይወትህን፣ ልብህ በምን ያህል ጥልቀት ለእርሱ መሻት እንዳለው በማወቅ መዝን (መዝ 42፥1)::

ሕይወትህን፣ ለመንፈስ ቅዱስ ምን ያህል በሙላት እንደሰጠህ በመተመን መዝን። እርሱ የሚወርስህ አንተ ፈቅደህ ራስህን በሰጠኸው መጠን ነው። አብልጠህ በተሰጠህበት መጠን አብልጦ በአንተ ውስጥ ይኖራል። ሕይወትህን፣ ሙሉ ከሆነው መገኘቱ ጋር ተስማምተህ እንዴት እንደቀጠልክ፣ በመላው ነፍስህ ሙሉ ለሙሉና ያለማቋረጥ ቅድስናህን ጠብቀህ በመቆየትህ መዝን። ሕይወትህን፤ ፈቃዱን ሁሉ ለመቀበል በሚሰማህ ደስታ፣ ከራስህ ፈቃድ ይልቅ የእርሱን ፈቃድ በማድረግ ባለህ ጥልቅ ረሃብ መዝን። ሕይወትህን፣ ለእርሱ በግል ሙሉ በሙሉ በመሰጠትህ መዝን።

ሕይወትህን፣ ጥቃቅን የሚመስሉ ነገሮችን ጭምር ያለማቋረጥ ለእርሱ በመታዘዝህ፣ ፈጥነህ በመታዘዝህና ስትታዘዝም በሚሰማህ ደስታ መዝን። መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ለሚታዘዙ ሰዎች ነው (ሐዋ 5፥32)። አብዝተህ በታዘዝክ መጠንም በአንተ ውስጥ በሙላት ይኖራል፤ ይሠራልም።

ሕይወትህን፣ መንፈሱ በአንተ ውስጥና በአንተም በኩል በተገለጠበት መጠን መዝን። ይህንንም ትህትናውን በተጋራህበት ሙላት መዝን። በእውነት የራስህ ባዶነት ይታወቅሃል? ወይስ ብዙውን ጊዜ በራስ የመተማመን ስሜት ይሰማሃል? ይህንን በእርሱ ቅድስና መዝን - በእውነት ሥጋዊ የሆኑ መሻቶችና ብርቱ ስሜቶች ከአንተ ተወግደዋል? ይህንን በእርሱ ፍቅር መዝነው - በእውነት የእርሱን ፍቅር ተለማምደሃልን ወይስ እንደማንኛውም ተራ ነገር ሆኖብሃል? ሕይወትህን፣ መንፈስ ቅዱስ ያለማቋረጥ በአንተ ውስጥ በሚደሰተው ደስታ፣ ርኅራኄው በአንተ ውስጥ ጥልቀት ባገኘበት መጠንና በአንተ ውስጥ ትዕግሥቱን ባጸናበት ልክ መዝን።



ሕይወትህን በንግግርህ፣ በጸሎትህ፣ በምስክርነትህና ነፍሳትን ለመማረክ በምታደርገው ጥረት፣ ዕለታዊ በሆነው ኑሮህ በትናንሽና ከበድ ባሉ ጉዳዮች ከመንፈስ ቅዱስ ምሪት በምታገኝበት ሁኔታ መዝን። ሕይወትህን፤ አገልግሎትህን ያለማቋረጥ በቀባበት፣ በጸሎትሁ ውስጥ በተገለጸው ኀይል፣ በንግግርህና በጽሑፍህ በተገለጸው ትኩስ ቅባት፣ በምስክርነትህና በስብከትህ የሰዎችን ሕይወት ወደ ንስሐ በማምጣቱና በእንቅስቃሴዎችህ ሁሉ እርሱ በባረከህ ባርኮት መዝን።

ሕይወትህን፣ መንፈስ ቅዱስ በአንተ ውስጥ በመኖሩና ሕይወቱንም በገለጠበት መጠን፣ በፍቅሩ፣ በንጽሕናው፣ በብሩህነቱና በአንተ ውስጥ ባለው ኀይሉ መዝን። ሕይወትህን፤ ኀያል የሆነ እጁን በአንተ ላይ ባኖረበትና ኀይሉንም በውስጥህ በተደጋጋሚ በገለጠበት መጠን መዝን። ሕይወትህን፣ አንተን በሞላበትና በተጠቀመበት መጠን መዝን።

ጉዳዩ አንተ ምን ያህል ጥረት ማሳየትህ አይደለም፤ ይልቁንም እርሱ በአንተ ውስጥና በአንተም በኩል ምን ያህል ሠራ የሚለው ነው። የተፈጠርክበትም ምክንያት ይህ ነው፤ ለዚህም ነገር ተዋጅተሃል፤ እግዚአብሔር ራሱ በመንፈሱ በመንፈስህ ውስጥ ይኖራል። ሕይወትህን ተራና ጥቃቅን በሆኑ ምድራዊ ነገሮች አትመዝን፤ ይልቁንም በአንተ ውስጥ በሚኖረው መንፈሱ መዝን።

## መንፈስ ቅዱስ ሆይ ጨምር

መንፈስ ቅዱስ ሆይ፣ ጨምር፣ አሁንም ከሙላትህ ጨምርልኝ፤ ሁልጊዜም ገና እንደአዲስ የልቤ ጩኸት ይሄው ነው። የበዛ ህልውናህ ሁሉም ሊያየው የሚችል የተትረፈረፈ ውበት በእኔ ሕይወት ይገለጽ። በማንኛውም መንገድ የበለጠ በረከት፣ በየዕለቱ የላቀ ምሪትህ ያግኘኝ።

የበዛ፤ አዎን እጅግ የበዛ የተቀደሰ ኀይልህ፣ በሰዓታትና በቀናት ውስጥ የሚጨምር የአምላክ ክብርህ፣ ደስታህና ታላቅ ኀይልህ፤ በቀን በሌሊት የሚጨምር ሙሉ ብቃትህ የማያቋርጥ ምልዐት ስጠኝ።

ከመንፈስህ እሳት ብዙ ጨምረህ አድለኝ፤ አ! ጌታ ሆይ የልቤን ጥማት አንተ ታውቃለህ! አዎ ብዙ ብዙ ሞገስ ብዙ ብዙ ክብርህን ማወቅ እሻለሁ። አገልግሎቴን ታትመው ዘንድ እጸልያለሁ፤ እባክህ ዛሬ ሕይወቴን ሁሉ በአንተ ክብር አትመው።

የተባረከን መንፈስ አብዛ፤ እጅግ እፈልግሃለሁ ጌታዬ። እየደጋገመ በውስጤ የሚያስተጋባ የልቤ ጩኸት ይሄው ነው። አ! መንፈስ ቅዱስ ሆይ ዛሬ ሙላኝ፤ በጸሎት ስፍራዬ ላይ በእኔ ላይ ውረድ። ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ሙላትህን እሻዋለሁ። የተባረከው መንፈስ ሆይ፤ ሙላኝ እባክህ ጨምረህ ሙላኝ።

ዊስሌይ ዱዌል



# 21
## በራእይህ ሕይወትህን መዝን

ሕይወትህ ከራእይህ ሊበልጥ አይችልም። የተኛውን ኀይልህንና አስደናቂ እውነቶችን ተግዳሮት ወዳለበት እንቅስቃሴ የሚያሸጋግር ራእይ ነው። ያለህን እምቅ ክህሎት በተግባር እንድታውለው የሚያነሳሳ፣ ካለህበት ስፍራ እንድትንቀሳቀስ የሚያበረታታ፣ ለእግዚአብሔር ጠቃሚ የሆንክ ሰው እንድትሆን ወደ ተባረከ ሕይወት የሚገፋህ ራእይ ነው።

ያለ ራእይ ከሆንክ በጊዜያዊ ሁኔታዎች በመወሰድ አደጋ ላይ ነህ። ያለ ራእይ ውስጣዊ ተስጥኦህን በማነሣሳት ቅዱስ ለሆነ የእግዚአብሔር ሥራና ለሌሎችም መትረፍ አትችልም። በምትኖርበት ዓለም ላይ ያለ ራእይ ሕይወትህ ተጽእኖ ሊያመጣ አይችልም። እግዚአብሔር አንተን ለፈጠረበትና አንተን ላዳነበት ዓላማ ጭራሽ ብቁ አትሆንም።

ዊልያም ቡዝ ድነትን የተቀበለው በዐሥራ አምስት ዓመት ዕድሜው ሲሆን፣ ከዚያም ከስድስት ሰዓት በኋላ እጅግ የተጨናነቁ የመኖሪያ ቤቶች ባሉባቸው መንደሮች ውስጥ እየወጣና እየገባ ለድሆች ኢየሱስን ይመሰክር ነበር። ከማለዳው አንድ ሰዓት የጀመረ እስከ ምሽቱ አንድ ሰዓት ድረስ በሥራ ተጠምዶ ይውላል፤ ከዚያ በኋላ ደግሞ ለሌሎች ባርኮት ይሆን ዘንድ ጊዜውን ይጠቀማል። ኀጢአተኞች እጅግ በበዙባት በኢንግላንድ ውስጥ በምትገኘው ኖቲንግሃም ተብላ በምትጠራው የከተማዋ ክፍል ሳጥን ላይ ቆሞ በዚያ ለተሰበሰቡ ልዩ ልዩ ዓይነት ሰዎች የኢየሱስን ታሪክ በቀላሉ ይነግራቸዋል። ከዚህ የተረፈውን ጊዜ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስንና

ስለዊስሌ፣ ዋይት ፊልድ፣ ቻርልስ ፊኒ የተጻፉና በእነርሱም የተጻፉ መጻሕፍትን ያነባል።

ቡዝ ዕድሜው ሃያ ዓመት በሞላ ጊዜ፣ በተናቁ የሎንዶን መንደሮች ለሚገኙ ከማኅበረሰቡ ለተገለሉ ሰዎች መስበክ ጀመረ። ለሰካራሞችና በኀጢአት ታስረው ለተያዙ ያስቅስላቸው ነበር። እግዚአብሔር እንዲህ ባለው ራእይ ለድሆችና ለችግረኞች ሸክም የሰጠው በመሆኑ ትዳር ከያዘ በኋላ እርሱ፣ ሚስቱና ልጆቹ ሁሉ ራሳቸውን ለዚህ ተግባር አሳልፈው ሰጡ። ዊልያም ቡዝ በቅድስናና ሌሎችን በመርዳት የሚያምን ሰው ነበረ። እርሱና ተባባሪዎቹ በየእሁድ ጠዋት የቅድስና አገልግሎት የነበራቸው ሲሆን፣ ምሽቱን ደግሞ የወንጌል ስርጭት አገልግሎት ይሰጣሉ፤ ሳምንቱን ሁሉም ችግረኞችን በመርዳት አገልግሎት ይሠማራሉ። ገና በልጅነቱ በልቡ ውስጥ ይቀጣጠል የነበረው ራእያዊ ሸክም፣ ዕድሜው ሰማንያ ሦስት ዓመት ሆኖ እስከሚሞትበት ጊዜ ድረስ ይነድ ነበር። በመጨረሻው ሰዓት ልጁን እንዲህ አለው፤ "ቤት የለሽ የሆኑቱን ትንከባከብ ዘንድ ቃል ግባልኝ . . . የማስበው በዚች አገር ያሉትን ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን በየትኛውም ምድር ያሉትን ድሆች ጭምር ነው"።

ቡዝ በራዕዩ አልተሳሳተም ነበር፤ ዛሬ የድነት እርበኞች የወንጌል ምስክርነት ጓድ በመላው ዓለም በ91 አገራት የድነት አገልግሎትና አገልጋዮችን የማሳደግ ተግባር እያከናወነ ይገኛል። ከ25,000 በላይ የሚሆኑ ለአገልግሎት የተሾሙ የድነት አርበኞች ጓድ ሠራተኞች በ125 ቋንቋዎች በማገልገል ላይ ይገኛሉ። ከ500,000 በላይ ሕፃናት በእሁድ የሰንበት ትምህርት ክፍሎቻቸው



ታቅፈዋል። በዓመታት መካከል በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ለክርስቶስ ተማርከዋል፤ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ደግሞ በችግራቸው ጊዜ እርዳታን አግኝተዋል።

ራእይ በእውነት ወደ ውስጥህ ጠልቆ ከገባ፣ ፈጽሞ እንደ ቀድሞው አትሆንም። በሚቀጥለው ዓመት ምን እንደምትሆን እግዚአብሔር ለአንተ ያለው ራእይ በጨረፍታ የታየህ እንደሆነ፣ በሕይወትህ አዲስ ትርጉም ማየት ትጀምራለህ። አዲስ በሆነ አቅጣጫ ለመዘርጋት አዲስ የጥሪ ድምፅ ታደምጣለህ። እግዚአብሔር አዲስ በሆነ አቅጣጫ ሕይወትህን በመምራት መንገዱን ይገልጥልሃል። ከዚህ በፊት ያልተገነዘብካቸውን ነገሮች አጥርተህ ማየት ትጀምራለህ። በየዕለቱ ሕይወትህ ለዘላለማዊው ሕይወት ታላቅ ቁም ነገር አስተዋጽኦ የምታበረክትበትን የጠራ መንገድ ታያለህ።

እግዚአብሔር ለአንተ እጅግ ጠቃሚ የሆነ ራእይ አለው። አዲስ የሆነ ገናም ያልተገለጠ እቅድ ለአንተ አለው። አሁን ያለህበትን ሁኔታ አትመልከት። እግዚአብሔር ነገ ትሆንለት ዘንድ ያቀደውን ራእይ ጨብጥ። ዛሬ ካለህበት ሁኔታ መለወጥ እንዳትችል የሚከለክሉ፣ ዙሪያህን የከበቡህን ሁኔታዎች በጭራሽ አትመልከት። እግዚአብሔር ለአንተ ያለውን ራእይ አጥብቀህ ያዝ።

እግዚአብሔር ለአንተ ያለው ራእይ ለአንተ ታስቦ የታቀደ እንጂ ለሌላው የሚሆን አይደለም። አንተ በእግዚአብሔር የተወደድክ ነህ! በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ ያለህ ሰው ነህ። ለእግዚአብሔር ጠቃሚ የሆንክም ነህ። እግዚአብሔር አሁን እየተጋፈጥካቸው ያሉትን ችግሮች ያያል። አንተ ከምታውቀው

በላይ አሁን ያለህበትን ሁኔታ በሙላትና በዝርዝር ያውቃል። ይህም ብቻ ሳይሆን አንተ የማታውቃቸውን ነገሮች ያውቃል - እርሱ መጭ ዘመንህን ያውቃል። ነገህ ምን እንደሚሆን ጭምር ያውቃል። ለአንተ ምቹ የሆነውን የሕይወትህን አዲስ ምዕራፍ እቅድ ያዘጋጃል። የአንተን ሕይወት በመጠቀም ሌሎችን ለመባረክ፣ ለአንተ ያለውንም የተለየ ተልዕኮ ለመፈጸም ያስባል። እርሱ ለአንተ ያለውን ራእይ በጨረፍታ ብትመለከት፤ እግዚአብሔር ለአንተ አዲስ ነገር እንዳለው ታውቃለህ።

እርሱ የሚያየውን ትመለከት ዘንድ ዐይኖችህን እንዲከፍትልህ ጠይቀው። የጠላት ሠራዊት፣ ነቢዩ ኤልሳዕ የተቀመጠባትን ከተማ ዶታንን በሌሊት በከበባት ጊዜ የኤልሳዕ አገልጋይ የነበረው ግያዝ በማለዳ ተነሥቶ በፍርሀት እየተንቀጠቀጠ፣ "እንግዲህ ምን ማድረግ እንችላለን?" እያለ ጮኸ። ኤልሳዕ፣ "ከእኛ ጋር ያለው ከእነርሱ ጋር ካለው ይበልጣል" ሲል እንዳይፈራ ነገረው።

ኤልሳዕ እንዲህ ሲል ጸለየ፤ "አቤቱ ያይ ዘንድ ዐይኖቹን እባክህ ክፈት፣ እናም እግዚአብሔርም የብላቴናውን ዐይኖች ገለጠ አየም እነሆም በኤልሣዕ ዙሪያ ያሉት የእሳት ፈረሶችና ሰረገሎች ተራራውን ሞልተውት ነበር" (2ነገ 6፥17-18)። አገልጋዩ የነበረው ግያዝ የሚታዩ ነገሮችን ብቻ የሚያዩ ዐይኖች ነበሩት። እግዚአብሔር ግን የማይታየውን ምንጭ፣ ጥበቃውንና በፊቱ ላለው ዘመን ያለውን እቅድ ያስተውል ዘንድ ዐይኖቹን ከፈተለት። ገና ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት እግዚአብሔር ነጻ አወጣቸው።



ከሚታየው ነገር ባሻገር አርቀህ እንድትመለከት እግዚአብሔር ይፈልጋል። ከፊት ለፊትህ የተጋረደው የማይነቃነቅ ሁኔታ ምናልባትም ልብህን በፍርሃት ሞልቶት ይሆናል። ነገር ግን ታላቅ እውነታ አለ - እግዚአብሔር። የሚታየው ምናልባትም የሕይወትህን አድማስ ከባድ በሆኑ የኀላፊነት ጭነቶች፣ እጥረቶችና ችግሮች ሞልቶት ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር የሕይወትህን አድማስ ከፍ ሊያደርግና ለአንተ ማድረግ የሚችለውን አዲስ አቅጣጫ ሊያመለክትህ ይፈልጋል። አሁን ያለህበትን የሚታዩ ሁነቶች እግዚአብሔር አይከድም። ነገር ግን እርሱ ወዳቀደልህ ነገ ያመጣህ ዘንድ አዳዲስ የሆኑ ታላላቅ እውነታዎችን በሕይወትህ ይጨምራል።

እግዚአብሔር ከእኛ ቀድሞ ለእኛ ያየልንን ለማወቅ ማናችንም ብንሆን ሙሉ ራእይ የለንም። በመሠረቱ ነገሮችን ሁሉ በዝርዝር ማየት አያስፈልግህም። ማየት የሚያስፈልግህ በሉአላዊ ኀይሉ ያለውን፣ ስለ ዛሬና ስለነገ ሕይወትህ ፍጹም የሆነ እውቀት ያለውን፣ እግዚአብሔርን ነው። አዎን ማየት የሚያስፈልግህ፣ ዛሬ አንተን ከከበበህና ከተገዳደረህ ነገር ውስጥ መልካም ነገርን ለማውጣት የተዘጋጀውን እግዚአብሔር ነው። ማየት የሚያስፈልግህ እግዚአብሔር አንተን ለመባረክ፣ በአንተ ለመገልገልና መንገዱን በፊትህ ለመክፈት በሺህ የሚቆጠሩ አቅጣጫዎች ያሉት መሆኑን ነው።

ሰማያዊው አባታችን ነገሮች የሚያስደንቁት አይደለም። መቼም ይሁን መቼ የደረቀ ምንጭ ሆኖ አያውቅም። ደግሞም ችግር አጋጥሞት የሚያውቅበት ጊዜ የለም። ተሸንፎም አያውቅም።

ሙሉ ለሙሉ ራስህን ለእርሱ አሳልፈህ የምትሰጥ ከሆን፣ ሙሉ በሙሉ በእርሱ የምትታመን ከሆንና ያለማለሳለስም የምትታዘዘው ከሆነ ለአንተ ያለውን እቅድ ሊተገብረው ይችላል።

የአምላክህን ራእይ ተቀበል። እግዚአብሔር እግዚአብሔር ነው። በችግሮችህ መጠን እግዚአብሔርን አትመዝነው። ይልቁን ችግሮችህን በእግዚአብሔር መዝናቸው። በጊዜያዊው ሁኔታዎችህ እግዚአብሔርን አትመዝነው፤ የጊዜውን ሁኔታህን እውነታ በእግዚአብሔር መዝነው።

ጆርጅ ሙለር እግዚአብሔርን የሕይወቱ የመጀመሪያና አንገብጋቢው ጉዳይ አድርጎ ክብር ይሰጥ ዘንድ በመንፈስ ምሪትን ተቀበለ። ከድነቱ ጥቂት ጊዜያት በኋላ በሃያ አንድ ዓመት ዕድሜው፣ ገንዘብ ነክ በሆኑ ፍላጎቶቹ ሁሉ በእግዚአብሔር መታመንን ተማረ። ሊታይ በሚችል መንገድ እግዚአብሔር የማይለወጥ፣ የታመነና ለማንኛውም ዐይነት ችግር መልስ መስጠት የሚችል መሆኑን ለዓለም ለማሳየት ይመኝ ነበር።

እ.ኤ.አ. በ1835 ይህንን ለማድረግ ተመራጭ የሆነው መንገድ ወላጅ አልባ የሆኑ ሕፃናትን የመንከባከቢያ ማዕከል መመሥረትና ከማንኛውም ሰው ለሥራው ማስኬጃ ገንዘብ ያለመጠየቅ እንዲሁም ምን እንደሚያስፈልገው ለሕዝቡ በይፋ ያለማሳወቅ እንደሆነ ተሰማው። በሚታይ መንገድ እግዚአብሔር ጸሎትን እንደሚመልስ ማረጋገጫ ለመስጠት አሰበ። የእርሱ ራእይ ይህ ነበር።

ቀስ በቀስ የሙለር እምነት እየጨመረ መጣ፣ እግዚአብሔር የራእዮን ስኬት እየጨመረለት ሄደ። እጅግ በብዙ መንገድ



ለእግዚአብሔር ክብርን የሚያመጣ ሰው ሆነ። ከመሞቱ በፊት ከአስር ሺህ የሚበልጡ ወላጅ አልባ ሕፃናትን ይንከባከብ ነበር። ብዙውን ጊዜ በአንድ ጊዜ ለአንድ ቀን የሚሆነውን ምግብ ብቻ ነበር በዕለቱ የሚቀበለው። አንዳንድ ጊዜ አብረው የሚያገለግሉትን በመጥራት ለሚቀጥለው የምግብ ጊዜ አስፈላጊ የሆነው ምግብ እንዲሰጣቸው በቀን ሁለት ጊዜ ይጸልዩ ነበር። ወላጅ አልባዎቹ ሕፃናት ሁልጊዜም የተመጣጠነ ምግብ ያገኙ ነበር። በመቶዎቹ ለሚቆጠሩ ጊዜያት ለሚቀጥለው የምግብ ጊዜ ገንዘብም ሆነ ምግብ ያልነበሩባቸው ጊዜያት ነበሩ፤ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በሆነ አስደናቂ መንገድ ፍላጎታቸውን ያሟላ ነበር። በእነዚህ ሁሉ ጊዜያት ምግብ ዘግይቶ የሚያውቀው ለሁለት ጊዜ ብቻ ነው፤ ለዚያውም ለሠላሳ ደቂቃዎች ያህል ብቻ።

ኤ.ቲ. ፒርሰን ከሚስተር ሙለር ጋር አንድ ምሽት አሳልፎ ነበር። እናም ወደ መኝታቸው ከመሄዳቸው በፊት፣ በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ልጆቹ የሚመገቡት ምግብ ስለሌለ አብረው በመጸለይ እንዲተባበሯቸው ሚስተር ሙለር ዶ/ር ፒርሰንን ጠየቃቸው። በዚያ ምሽት የምግብ መጋዘኖች ሁሉ ዝግ ነበሩ። በሌሊቱ አጋማሽ ላይ እግዚአብሔር በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ምግብ ለማቅረብ ሁኔታዎችን የሚያመቻች አንድ ሰው አስነሣ። በዚህ ምክንያት ሁለት ሺህ የሚሆኑ አሳዳጊ የሌላቸው ሕፃናት ቁርሳቸውን በሰዓቱ ተመገቡ። ጆርጅ ሙለርም ይሁን አብረውት ከሚሠሩት ባልደረቦቹ መካከል ምግብ እንደሚያስፈልጋቸው ለማንም ሰው አልተናገሩም ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ በዚያ ማለዳ የመጣላቸው ምግብ ለአንድ ወር ያህል ልጆቹን ለመመገብ የሚበቃ ነው።

በሕይወቱ የመጨረሻዎቹ ዐሥራ ስባት ዓመታት፣ ዕድሜው 65 ዓመት ከሆነው በኋላ፣ ሙለር ዓለም አቀፍ የሆነ የአገልግሎት ጥሪ እንደተሰጠው አሰበ:: ከ200,000 ማይሎች ርቀት በላይ ተጓዘ፤ በ42 አገራት አገለገለ፤ 6,000 ጊዜ ያህል ንግግር አደረገ፤ 3 ሚሊዮን ለሚያህሉ ሰዎች ሰበከ:: ሙለር 2 ሚሊዮን የሚደርሱ መጽሐፍ ቅዱሶችን ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን፣ 3 ሚሊዮን ሌሎች መጻሕፍትንና ትራክቶችን አሰራጨ፤ በመላው ዓለም የሚገኙ 115 ሚስዮናውያንን ጨምሮ ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን ለመደገፍ 1,300,000 ዶላር ሰጠ:: በዚህ ሁሉ ግን የሚያስፈልገውን ነገር ይናገር የነበረው ለእግዚአብሔር ብቻ እንጂ ለማንም አልነበረም:: ለእግዚአብሔር ሥራ እንዲሆነው ለ7,500,000 ዶላር ጸለየ፤ 400,000 ዶላር ለራሱ የግል ጉዳይ እንዲያውለው ተጨምሮ ተሰጠው፤ ለግሉ የተሰጠውንም ገንዘብ ጨምሮ በእግዚአብሔር ሥራ ላይ አዋለው:: የኖረው ትሁትና የተሞላ ቀላል የሆነ ህይወት ነው፤ በሞተበት ጊዜ መጻሕፍቱን ጨምሮ የነበረው ንብረት ከ800 ዶላር የሚያንስ ነበር::

የሙለር መላው ሕይወት፣ "እግዚአብሔር ሕያው እንደሆነ በግልጽ በማሳየት እግዚአብሔርን ማክበር" የሚለውን አንድ ራእይ ወደ ፍጻሜ ለማምጣት በፍጹም የተሰጠ ነበር:: "ማንኛውም አዲስ የሆነ መረዳት ወደ አእምሮህ በመጣ ጊዜ፣ ይህ ከእግዚአብሔር ሐሳብ ጋር የሚስማማ ነውን? ለክብሩስ የሚሆን ነውን?" ብለህ ጠይቅ፤ ለክብሩ የማይሆን ከሆነ፤ ለአንተም መልካም አይደለምና በዚያ ጉዳይ ላይ እንዳች ልታደርግ አትችልም:: አንድ የተወሰነ ተግባር ለእግዚአብሔር ክብር እንደሚሆን ካረጋገጥክ በስሙ



መጀመርህን አትዘንጋ፤ እስከ ፍጻሜውም ሂድበት:: በጸሎትና በእምነት ተያያዘው፤ ፈጽመህ ተስፋ አትቁረጥ" ሲል ተናግሯል::

እግዚአብሔር ለአንተ ከሆነ፤ ከባድ ጉዳት ሊያደርስብህ ማን ይችላል? እግዚአብሔር ለአንተ ያለውን እቅድ የሚያሰናክለውስ ማነው? ለእግዚአብሔር ምላሽ መስጠት ሲያቅትህና ሙሉ ለሙሉ እግዚአብሔርን ለመከተል ቸል ስትል ራስህ ታደናቅፈው እንደ ሆነ እንጂ ማንም ሊያቆመው አይችልም:: መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ በግልጽ እንደሚናገር፤ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ከሆነ የሚቃወምህ ከቶ ማን ነው (ሮሜ 8፥31)? እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ከሆነ ከምትፈልገው፣ ከችግሮችህና ከሚቃወሙህም በላይ የሆነ አቅርቦት እግዚአብሔር ለአንተ ያዘጋጃል::

ከእግዚአብሔር የሆነ አዲስ ራእይ ተቀበል:: እግዚአብሔር እርሱ ራሱ ከፈጠረው ጽንፈ ዓለም ይልቅ ትልቅ ነው:: ሁሉን የፈጠረው እግዚአብሔር ነው:: እግዚአብሔር ከማናቸውም አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች፣ ከማናቸውም ሁኔታዎች በላይ ነው፤ በኃይል ላይ ተደርበው ከሚመጡ ኃይላት፣ በሁኔታዎች ላይ ተጨምረው ከሚመጡ ሁኔታዎች ሁሉ በላይ ነው:: ለይጣን ሁኔታዎችን ዐልፎ መሄድ እንዳይችል እግዚአብሔር ለነገሮች መቁረጫ ያበጅላቸዋል:: ባልተረዳኸው መንገድ እንኳ አንተን ይረዱህ ዘንድ መላእክቱን ይጠቀማል (ዕብ 1፥14):: የተፈጥሮ ኃይላትን ሁሉ እግዚአብሔር ሊቆጣጠር ይችላል፤ ምክንያቱም እርሱ የተፈጥሮ ሁሉ ፈጣሪ ነው::

እግዚአብሔር ላንተ ስላለው ፍቅር አዲስ ራእይ ተቀበል:: ምንም እንኳን እግዚአብሔር ዓለምን ሁሉ የሚወድ ቢሆንም፣

አንተን በግል ይወድሃል። እርሱ አከ እምላክህ ነው። ከዚህ በፊት ከምታውቀው እውነታ በላይ እግዚአብሔር አምላክህ እንዲሆን ይፈልጋል። እግዚአብሔር እያሳየህ ያለው አከ ገና የጥበቡን፣ የፍቅሩንና የኃይሉን ታላቅነት ጅማሬ ነው። አዳኝህ ብቻ መሆንን አይፈልግም፤ ነገ ከሚሆነው ነገርህ ጋር ሁሉ አብሮ መሆንን ይፈልጋል። ለኑሮህና ለዘላለም ሕይወትህ እቅድ አለው። ልክ አሁን ባለህበት ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሔር ሊገለገልብህ ይፈልጋል።

ሁለንተናህ ለእግዚአብሔር ፈጽሞ የተሰጠ ነውን? በሕይወትህ እንዲሆኑ የፈቀዳቸውን ነገሮችን ሙሉ በሙሉ ባትረዳቸውም፣ ከራስህ ፈቃድ ይልቅ የእርሱን ፈቃድ ትቀበላለህን? ፈቃድህን፣ ሕይወትህን፣ ቤተሰብህን፣ ቀጣይ ሕይወትህን፣ እቅድህንና መላውን ማንነትህን በፍቅር እጆቹ ላይ ፈጽመህ አስቀምጠሃልን? እናስ በመንፈስ ቅዱስ ሊሞላህ እንደሚችል ትታመነዋለህን? እንዲህ ከሆነ፤ በመንፈስ የተሞላ ሕይወትህ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ አሸናፊ ነው።

እግዚአብሔር በመንፈሱ የሚሞላህ ሊያነጻህ፣ ኀይልን ሊያለብስህ፣ ሊባርክህ፣ ሊመራህና ሊጠቀምብህ ነው። በፊትህ ፈገግታ፣ ከአንደበትህ በሚወጣ ቃል፣ በበጎነትህ፣ ለተቸገሩት በመድረስህ፣ በምስክርነትህና በፍቅርህ ለብዙዎች ባርከት ያደርግህ ዘንድ ራስህን ለእግዚአብሔር ስጥ። እመቺ በሆነ መንገድ ሁሉ እንዲባርክህና እንዲጠቀምብህ እግዚአብሔርን ጠይቀው። ዛሬ ስለሰጠህ ትናንሽ ምቹ ሁኔታዎች ልብ ብለህ አስተውል። ለጌታና ለሌሎች ያለህን ፍቅር ለማሳየት ተጠቀምባቸው።



ከዚህ ቀደም ያላስተዋልካቸውን እመቺ ሁኔታዎችን ታይ ዘንድ እግዚአብሔር ዐይኖችህን ሊከፍት ይችላል። ለተጎዱትም በዚህም አንተ ፈጽመህ ባላስተዋልከው መንገድ ታላቅ ባርከት ልትሆን የምትችልበትን ሁኔታ ማየት ትጀምራለህ። ምንም ዐይነት ምስጋናን ከማንም አትጠብቅ። ኢየሱስ ክርስቶስ አከ የተመለገነው በተወሰኑ ሁኔታዎች ብቻ ነበር። ነገር ግን ስለ ክርስቶስ ብለህ ሰዎችን ውደድ። እርሱ በአንተ ሆኖ እንዲወድ ፍቀድ። የፈጠረውን ዓለም በአንተ ሆኖ እንዴት እንደሚወድ አዲስ ራእይ ተቀበል።

ጌታችን ጸሎትህ የአንተ ለሆኑት፣ ለሁኔታቸው ለሰማኸውና በችግር ውስጥ ላሉ ሁሉ ባርከት የሚሆንበትን ራእያዊ መንገዶች ያመላክትሃል። በጸሎት የምትዘራውን ዘር በየዕለቱ ጊዜውን እየጨመርክ ሂድ፤ ትዝናናባቸው ለነበሩ ሁኔታዎች የሰጠኸውን ጊዜ ለሌሎች መጸለይ ትችል ዘንድ መሥዋዕት አድርጋቸው። ስለ ችግሮቻቸው ሁሉ ንገረው።

ለምትኖርበት ማኅበረሰብና ለመላው ዓለም የጸሎትህን ዘር መዝራት ትችላለህ። በጸሎት ዘር የምትዘራበት የትኛዋም ቅጽበት ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የጸሎት አጋር በመሆን የምትተባበርባት ቅጽበት ናት፤ ምክንያቱም እርሱ በሰማያዊው ዙፋኑ ላይ ሆኖ ያለማቋረጥ ስለሌሎች ይማልዳል (ሮሜ 8፥34)።

በጸሎት ዘርን የምትዘራባት የትኛይቱም ቅጽበት ወደ ዘላለም ሕይወት ሽልማትህ ፈትህን መለስ ያደረክባት ደቂቃ ናት። ደቂቃዎችንና ሰዓታትን እውነተኛ ጥቅም ለሌላቸው፣ የጊዜ ኪሳራ ለሆኑ ነገሮች አታውላቸው። ተግተህ በመጸለይ ለምታሳልፋቸው ጊዜዎች በዘላለም መንግሥቱ ሲሸልምህ ደስ የሚሰኝባቸውን

ዘላለማዊ ሽልማቶች እንድታገኝ የሚያደርጉ ጊዜያትን በከንቱ አታባክናቸው:: ጊዜዎችህ ለዘላለም ሕይወትህ ነጥብ የምታስቆጥርባቸው የሚሆኑበትን መንገድ ተማር::

እዚህ ላይ ሙሉ ክብ ሰርተን ይህን መጽሐፍ ስንጀምር ወደተነሣንበት እንመለስ:: እግዚአብሔር በማያቋርጥ ሁኔታ ሕይወትህን እየመዘነ ነው:: እግዚአብሔር ዘላለማዊ የሆነውን ሽልማት አሁን አንተ አለኝ ብለህ ለምታስበው ብቃትህ ሳይሆን ራስህን በዘራህበት ብቃትህ ላይ የተመሠረተ ሽልማት ሊሸልምህ አቅዶ አለው:: ሕይወትህን፣ እግዚአብሔር ራሱ ጊዜዎችህን፣ ድርጊቶችህን፣ ፍቅርህን፣ ጸሎትህን ታዛዥነትህን በተለየ መንገድ የሚለውጥበትን ራእይ በተቀበልክበት መጠን መዝን:: ሕይወትህን፣ ዘላለማዊነት ማለት ማብቂያና ማለቂያ ጫፍ የሌለው መሆኑን፣ ከዚህ ጊዜ ጋር ሲነጻጸር የዘላለም ሕይወት ምን ያህል ታላቅ መሆኑንና መንግስተ ሰማይ ከምድር ይልቅ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ በተረዳህበት ራእይ መዝን::

ሕይወትህን ለሰዎች ለእግዚአብሔር ምን ያህል ጠቃሚዎች እንደሆኑና እነዚህንም፤ በምድር ላይ ያሉ ሰዎችን ሁሉ ሊባርካቸውና ሲያድናቸው እንደሚወድ ባለህ ራእይ መዝን:: እግዚአብሔር የአንተን ሕይወት በመጠቀም እንዴት አድርጎ የአንተንና የእርሱ የሆነውን ዓለም በፍቅርህና በጸሎትህ መድረስ እንደሚችል አዲስ ራእይ ተቀበል::

ሕይወትህ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠህ እንደሚዘራ ዘር ሆኖ ነው:: ለዘላለም ሕይወት ዘርን መዝራት ለአንተ ታላቅ መታደል ነው:: አብዛኛው የሕይወትና የገንዘብ አጋጣሚዎችህ



ዐልፈው ሄደዋል:: ሕይወትህን፣ እያንዳንዱን ቀን ለእግዚአብሔር እና ለዘላለም ሕይወት ነጥብ እያስቆጠርክ እንዴት እንደምትጨርሰው ባለህ ራእይ መዝን:: ሕይወትህን በራእይህና ራእይህንም ተከትለህ እንዴት እንደምትራመድ እንዲሁም ራእይህን እንዴት አድርገህ ወደ ዘላለም ሕይወት እውነታና ሽልማት እንደምትቀይረው ባለህ ራእይ መዝን::

ቢል ብራይት ጌታን ካገኘ ከጥቂት ወራት በኋላ፣ ከሎስ አንጀለስ ወጣ ብሎ በሚገኝ ፎረስት ሆውስ በሚባል ስፍራ በአንድ ክርስቲያናዊ ጉባኤ ላይ ተካፈለ:: ሚስስ ሄንሪታ ሚርስ በሰኔ 24/1947 ምሽት የሰብከት አገልግሎቷን ጨርሳ የአገልግሎት ጥሪ ስታስተላልፍ አራት ወጣቶች ወደ እርሷ ወጡ:: እነዚህ ወጣቶች ሪቻርድ ሲ.ሀልቨርሰን (አሁን የአሜሪካ ምክር ቤት ካህን የሆነ)፣ ሉዊስ ኤች. ኢቫንስ (ከዚያ ክስተት አራት ዓመት በኋላ በሆሊወድ በምትገኝ የፕርስቢተሪያን ቤተ ክርስቲያን መጋቢ የሆነ)፤ ጆን ኤል. ፍራንክ (የሚስስ ሚርስ የረዥም ጊዜ የሥራ ተባባሪ የሆነ) እና ቢል ብራይት (ከዚያ በኋላ የታላቁ ተልዕኮ አገልግሎት መሥራች) ነበሩ::

እነዚህ ሰዎች በዚያ ሌሊት በጌታ ፊት ቆይታ አደረጉ፣ ኀጢአታቸውን እየተናዘዙ፣ የእግዚአብሔርን ምሪት እየጠየቁና የመንፈስ ቅዱስን መገኘትና ኀይሉን እየተጠባበቁ ቆዩ:: በምሽቱ በታላቅ ጩኸትና እንባ ወደ ጌታ ይጮኹ ነበር:: ጌታ እየተናገራቸው ሳለ ደግሞ ማናቸውም አይጸልዩም ነበር::

ከዚያ በኋላ እሳት ወረደ:: እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ራእይን በመስጠት መለሰ:: በዐይኖቻቸው ፊት በዓለም የሚገኙ

ኮሌጆችን ተመለከቱ፤ በዚያ ድነትን ያልተቀበሉ ነበሩ፤ ዓለምን መለወጥ የሚችል ኀይል ግን በእጃቸው ላይ ነበር። . . . ሚሲስ ሚርስና አራቱ ወጣቶች በሚቀጥለው ጠዋት ተለውጠው፣ አገልግሎትን ተቀብለውና ሰፊ ራእይን ሰንቀው ወጡ። ከፊታቸው ለኢየሱስ የምትማረክ ዓለም አለች!

እ.ኤ.አ በ1953 በህንድ ምድር ውስጥ ቢል ብራይትን አየሁና ያ ሰው ማን እንደሆነ ጓደኛዬን ጠየቅሁ። ያ ሰው በሎስ አንጀለስ ውስጥ በዚያ ምሽት ከሚስስ ሚርስ ጋር አብሮ የእግዚአብሔርን ምሪት ሲጠይቅ የነበረ ወጣት መሆኑ ተነገረኝ። በዚህ ጊዜ የአሜሪካንን ወጣቶች በወንጌል ለመድረስ እንደ መሸጋገሪያ ድልድይ የተጠቀመበት "የታላቁ ተልዕኮ አገልግሎት" የተባለውን አገልግሎት መሥርቶ ነበር። ዛሬ ይህንን ራእዩን እግዚአብሔር ወደ መላው ዓለም አስፋፍቶለታል። ከዚያ በኋላ ባሉት ዓመታት ቢል ብራይት የሚታወቀው፤ በየጊዜው እየሰፋ በሚሄደው ራዕይ ለእርሱና ለመሠረተው ድርጅት እግዚአብሔር ለሚሰጠው አዲስ እቅድ፣ ያለማቋረጥ በሚጨምረው እምነቱና ታዛዥነቱ ነው። መንፈስ ቅዱስ ከወረደ በኋላ ወጣቶች ራእይን እንደሚያዩ በነብዩ ኢዩኤል የተተነበየው ትንቢት በቢል ብራይት ሕይወት ተፈጽሟል። ብራይት፣ እግዚአብሔር በዚህ አገልግሎቱ ያከናውነውን ሲናገር፣ ዘገባዎቹ ሁሉ ዐይን የሚያስፈጥጡ ናቸው። ይሁን እንጂ ዝምተኛና ትሁት ከሆነ ባሕርይ የተነሣ ዘገባዎቹ የሚቀርቡት ጉራ ሳይቀላቀልባቸው ነበር። ብራይት የእግዚአብሔርን ክብር የማይነካ ሰው በመሆኑ ምክንያት አዳዲስ ተአምራታዊ መልሶችን ቢሰጠው የሚታመን ሰው ነው።



በ1960 የታላቁ ተልዕኮ አገልግሎት ተባባሪ ሠራተኞች ቁጥር 109 የደረሰ ሲሆን፣ ዘመቻውን የሚያካሂደው በአሜሪካ ብቻ ሳይሆን በኮሪያና በፓኪስታንም ጭምር ነበር። ተአምራዊ በሆነ መንገድ በካሊፎርኒያ አሮውሄድ ስፕሪንግስ ሰፊ አገልግሎት ያከናውኑ ዘንድ እግዚአብሔር ስፍራን ሰጥቷቸዋል። ነፍሳትን ይታደጉ ዘንድ በሺዎች ለሚቆጠሩ ወጣቶች ሥልጠና ሰጥተዋል። ስለዚህ ጉዳይ ቢል እንዲህ ሲል ይናገራል፤ "እግዚአብሔር የታላቁ ተልዕኮ አገልግሎትን የባረከበት ሦስት መሠረታዊ ምክንያቶች ያሉ ይመስለኛል። አንደኛ፤ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስንና የእርሱን ዓላማ ክፍ ለማድረግ ፍጹም የሆነ መሰጠት። ሁለተኛ፣ በአማኞች ሕይወት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስን አገልግሎት አጥብቆና ጠንቅቆ ማወቅ። ሦስተኛ፣ ለእያንዳንዱ የሥራ ተባባሪ፣ ተማሪና ለማንኛውም ሰው ቢሆን የተቀደሰን ኑሮ እንዴት መኖር እንደሚቻልና በክርስቶስ ያላቸውን እምነት እንዴት ለሌሎች እንደሚያካፍሉ፣ የተለየ፣ ጥልቀት ያለውና ተግባራዊ የሆነ ስልጠናን መስጠት ናቸው።" ለሥራ ተባባሪዎቻቸውና ለሚያገለግሏቸው ሌሎች ሰዎች ከሚሰጧቸው ዐሥር መሠረታዊ ኮርሶች መካከል፤ በመንፈስ ቅዱስ እንዴት መሞላት ይቻላል? በመንፈስ እንዴት መመላለስ ይቻላል? በመንፈስ እንዴት ስለ ጌታ መመስከር ይቻላል? ታላቁን ተልዕኮ አገልግሎት እንዴት ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል? የሚሉት ተጨምረውባቸዋል።

በራእይ ላይ በሚጨምር ሌላ ራእይ ላይ እየተረማመደ፣ አገልግሎቱ አስቀድሞ በአሜሪካ ምድር፣ ቀጥሎ ደግሞ በመላው ዓለም "እነሆ ሕይወት ተገልጧል" በሚለው የወንጌል ዘመቻ

ብዙዎችን ሲደርስ ችሏል። በኮሪያ ውስጥ በተካሄደው ኤክስፖ 74 በተሰኘ መሰል የወንጌል ዘመቻ 320,000 ሰዎች እንደተካፈሉ ተመዝግቧል።

ስመጥርና በተግባር የተፈተኑ አገልጋዮች አንድ በአንድ ወደ አገልግሎቱ እየተጨመሩ በመሄዳቸው የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የወንጌል አገልግሎት፣ የኮሌጅ የወንጌል አገልግሎት፣ የእስር ቤቶችና የወታደሮች የወንጌል ዘመቻ አገልግሎት፣ የአትሌቶች የወንጌል ዘመቻ አገልግሎትና በመላው ዓለም ለሚገኙ አማኞች የሚዳረሰው የአጋፔ (መለኮታዊ ፍቅር) አገልግሎት እየተስፋፋ ሄደ። በዋሽንግተን ዲ.ሲ. ውስጥ የክርስቲያን ኤምባሲ ተመሥርቶ ከመላው የዓለም ክፍል ወደ ዋሽንግተን ዲ.ሲና በኒዮርክ ወደሚገኘው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ለመጡ ዲፕሎማቶችና ለመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት አገልግሎት ይሰጣል። በሉቃስ ወንጌል ላይ ተመሥርቶ የተሠራውን፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ውጭ አንዳች ሌላ ነገር ያልተቀላቀለበትን፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች የተመለከቱትንና ከእነኝህም ተመልካቾች ውስጥ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ራሳቸውን ለጌታ እንዲሰጡ ያስቻላቸውን የኢየሱስን ፊልም አሳይተዋል። ይሄው ፊልም ከ200 በላይ በሚሆኑ ቋንቋዎች የተተረጎመ ሲሆን፣ አገልግሎቱ በተጨማሪ በሺህ በሚቆጠሩ ሌሎች ቋንቋዎች ለመተርጎም እቅድ አለው።

በመላው ዓለም የሚገኙ ከ16,000 በላይ የሆኑ አገልግሎቱን የሚደግፉ ሰዎች፣ በየጊዜው እየሰፉ የሚሄደውን የዚህን ራእይ ውጤታማነት በጉጉት ይጠባበቃሉ። እሁን እየተተገበረ ያለው



ትልቁ የአገልግሎት ግብ አዲስ ሕይወት በ2000 የተሰኘው ሲሆን በዚህም ዶክተር ብራይት 5000 የሚደርሱ የአዲስ ሕይወት የማሰልጠኛ ጣቢያዎች፣ በዓለም ዙሪያ በሚገኙ 8000 ኮሌጆች አገልግሎት የመስጠትና 5000 የሚሆኑ የፊልም ቡድኖች ኢየሱስ የተሰኘውን ፊልም ያለማቋረጥ እንዲያሳዩ እቅድ ይዟል። ከብዙ የክርስቲያን ድርጅቶች ጋር ተባብሮ በመሥራት በክፍለ ዘመኑ መጨረሻ ላይ በቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎችን ለክርስቶስ ለመማረክ በመጸለይ ላይ ይገኛል።

ይህ ራእይ የተጋነነ ይመስላልን? አንድ ነገር ልብ በል፤ የቢል ብራይት ራእይ እያደገ የሄደው ደረጃ በደረጃ ነው። እያንዳንዱ ታላቅ ራዕይ በአንጻራዊ መልኩ ሲታይ የሚጀምረው ከትናንሽ ራእዮች ሲሆን፣ ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ደረጃ በደረጃ እያሰፋው ይሄዳል። ዶ/ር ብራይት "1) ከተፈጥሮ ኀይል በላይ የሆነውን አስቡ፤ 2) ከተፈጥሮ ኀይል በላይ ጸልዩ፤ 3) ከተፈጥሮ ኀይል በላይ ዐቅዱ፤ 4) ከእግዚአብሔር ታላቅ የሆነውን ነገር ጠብቁ። " በማለት ምክሩን ያስተላልፋል።

እርግጥ ነው አንተ ቢል ብራይትን አይደለህም፤ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ለአንተ የተለየ ራእይ አለው። ሌሎች ሰፊ ለሆነ ራእይ ለእግዚአብሔር ታማኝ እንደሆኑ ሁሉ አንተስ ለእግዚአብሔር ታማኝ ትሆንለታለህን? ለቤተሰብህ፣ ለቤተ ክርስቲያንህና ለምትኖርበት ማኅበረሰብ የሚሆን ራእይ ተቀበል። ለመላው ዓለም የሚሆንን ራእይ ከእግዚአብሔር ተቀበል። መልካም አጋጣሚዎችህን እግዚአብሔር በሚያይበት እይታ ታያቸዋለህን? እግዚአብሔር ዓለምን በሚያይበት አይን አንተስ ትመለከታለህን?

እግዚአብሔር ለአንተ ያሰውን ራእይ ታስተውል ዘንድ አይንህን እንዲከፍትልህ ጸልይ፡፡

ደቂቃዎችን፣ ሰአታትን፣ ቀናትንና ዓመታትን በከንቱ አታባክን፡፡ የሕይወትህን ታላላቅ አጋጣሚዎች አታሳልፋቸው፡፡ ሕይወትህን እግዚአብሔር እንደሚመዝን መዝን፡፡ አሁን ወደ ኋላ ተመልሰህ ያለፈውን ነገር ልትሰውጥ አትችልም፡፡ ነገር ግን ከዚህ ቀን ጀምሮ እግዚአብሔርን በሙሉ ልብህ፣ በሙሉ ነፍስህና በሙሉ ሐሳብህ ውደድ (ማር 12፥30)፡፡ ከዚች ቀን ጀምሮ ባልንጀራህን እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ (ቁ.31)፡፡ ከዚች ቀን ጀምሮ እግዚአብሔር ዓለምን እንደሚወድ አንተም የምትኖርባትን ዓሰም ውደድ፡፡ ከዚች ቀን ጀምሮ በሕይወትህ ለመንግሥተ ሰማይ ነጥብ አስቆጥር፤ ሕይወትህንም በመንግሥተ ሰማይ አይታ ብርሃን መዝን፡፡ እናም ሽልማትህ ታላቅ ይሆናል፡፡ እርሱ ሕይወትህን በሚመዝንበት ሚዛን ራስህን መመዘን በመጀመርህ በዘላለም ዘመናትህ ሁሉ እግዚአብሔርን ታመሰግነዋለህ፡፡



## ራእይ ሰጠኝ

ራእይ ሰጠኝ፡፡ በኃጢአት ድቅድቅ ጨለማ ሰላሉት ራእይ ሰጠኝ፡፡ እስካሁን በሰይጣን ጨለማ የታሰሩትን ሚሊዮኖች አሳየኝ፡፡ የዓለምን መሸት ምንነት አብራልኝ፤ ምንም ብርሃን የማይበራበትን ጨለማ አሳየኝ፡፡ መሸት ያላቸውን ነፍሳት ሰጠኝ፡፡ ቃል የሚገቡ ልቦችንም አሳየኝ፡፡ ተሰጥቼ ለዓለም እስከመጨረሻው የመማለድ ሸክም ሰጠኝ፡፡

የጠፉትን ሁሉ ለመቀበል በተዘጋጀው ሲኦል ለመሠቃየት፣ ሚሊዮኖች ካለ ኢየሱስ መጨረሻ በሌለው ጥፋት ውስጥ ለመሆን መጣደፋቸውን አስገንዝበኝ፡፡ ያለ ክርስቶስ ሰላሉ፣ በሰይጣን ስለታጠሩ፣ በሩቅ አገሮች ስላሉ ሕዝቦች ራእይ ሰጠኝ፡፡ በመላው ዓለም እጆቻቸውን ዘርግተው ያሉ ሚሊዮኖችን አሳየኝ፡፡

ሕያው ክርስቶስን አሳየኝ፡፡ የጌቴሴማኒውን ሥቃዩን አስገንዝበኝ፡፡ የቀራኒዮውን ፍቅር፣ ዓለሙን ሁሉ የወደደበትን የእርሱን ፍቅር ሰጠኝ፡፡

ዌስሌይ ዱዌል

## ግድ እልሃለሁ

በዚህ አስቸጋሪ በሆነ ጊዜ በአዳኝህ ኀይል መስቀልህን እንድታነሣ ግድ እልሃለሁ። ኦ! አባክህ ለእግዚአብሔር እና ለሰዎች አንድ የከበረ ነገር አድርግ፤ እባክህ ወዳጄ ለአዳኝህ ዘላለማዊ አቅድ ሁሉን መሥዋዕት አድርገህ ና!

እጅግ በምታስፈልግበት በዚህ ጊዜ ግድ እልሃለሁ፤ ሰዓቱ እጅግ በመሸበት በዚህ ቅጽበት ግድ እልሃለሁ፤ የሕይወት ዘመንህ ምን ያህል አጭር እንደሆነች ልብ በል፤ ኦ! አባክህ ለእግዚአብሔር እና ለስዎች አንድ ነገር ታደርግ ዘንድ ተነሥ!

የእግዚአብሔርን ልጅ መስቀል ስታይ ደማቸውን ያፈሰሱ ሠማዕታትን ስታይ ጊዜ፣ የሕይወት ታሪክህን ወደ ኋላ ስታስተውል ለእግዚአብሔር እና ለሰዎች ስትል ያየኸው ያንተስ መከራ ምንድነው?

በአዳኝህ ልብ በውኑ ደስተኛ ነህን? ሸክሙን ልትካፈልና የራስህን ድርሻ ልትወጣስ ትፈቅዳለህን? ፍቅርህ እውነተኛ መሆኑን ልታረጋግጥለት ትሻለህን? ለመስጠትና ለማድረግ የከፈልከው ዋጋ ምንድን ነው?



እባክህ ና!አንድ የከበረ ነገር አሁን ለኢየሱስ አድርግ፤ እርሱ ስለ አንተ የእሾህ አክሊል ደፍቶ ራሱ በእሾህ ተወግቷል፤ አንተ ግን መጥተህ ሥራህን ጨርስና አክሊልን ጫን። እባክህ ከመስቀሉ አትሽሽ፤ ይልቁን አቅድን ፈጽም። ጊዜው አሁን ነው፤ ያ ካልሆነ ለእግዚአብሔር ያሁን ለሰዎች የሚጠቅም አይደለም።

ዊስሌይ ዱዌል።